«የምሰጥህ ጊዜ የለኝም ። ቢኖረኝ ደስ ይለኝ ነበር» አለች ።

«ምን ማለትሽ ነው? ለኔ እንዴት ጊዜ ታጭያለሽ? አብረን ያሳለፍነውን ውብ ጊዜና ጣፋጭ ትዝታ እንዲሁ ባንድ ጊዜ ከልብ አውጥቶ መወርወር አይቻልም ፡ ወይስ እንዲህ ለማድረግ የሚችል አንጀት አለሽ? እስቲ ንገሪኝ!» አልኳት ።

ምንም አልነገረችኝም ። ይልቅ ፡ «መቼ ነው የምትሔደው» ብላ ጠየቀችኝ ።

«የት?»
«ወደ ጦር ግንባር.....»
«አላውቅም ። ምናልባት ነገ ከነገ ወዲያ..........»
«ቶሎ ብትሔድ ጥሩ ነው ። ችግሬን ያቃልልልኛል.....»
«እኔ ነኝ ችግር የሆንኩብሽ?»
«ደደብ» አለችኝ ።

«ለኔም ጥሩ ነው ። ለማሰብ ጊዜ አገኛለሁ ። ለክፉም ሆነ ለደግ ከሚወዱት ሰው ትንሽ ራቅ ብሎ የማሰብ እድል ማግኘት ይጠቅማል ። ርቀት ፍቅራችንን ያጠናክራል ወይም እውነቱን ግልጽ አድርጎ ያሳየናል ። አይመስልሽም?» አልኳት ።

«ደደብ» አለችኝ ።

ብዙ ሙከራ አደረኩ ። ችግሯ ምን እንደሆነ ልትነግረኝ አልፈለገችም ። እና እንደገና ተቃቀፍን ። ጦርነትና ሠላም ። ምናልባት ወደፊት እንደዚሁ እንቀጥል ይሆናል — ሁልጊዜ..... ይህች ሕይወት.....



# ቀ ይ ት ር ኢ ት

## ና ቅ ፋ የ ደ ም ጎ ራ

### ምዕራፍ አራት

አርሚ አቪዬሽን ሜዳ እንድገኝ የተሰጠኝ ጊዜ በጣም አጭር ነበር ። ወታደራዊ ትእዛዝ ያለምንም ቅድሚያ ማስጠን ቀቂያ ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚሰጥበት ምክንያት አልገባህ እያለ ታንጾ ስላልተዘጋጀ ይሆናል ። ሀዋሳቴ ቶሎ እሺ ብለው አጭር ትእዛዝ አይቀበሉም ። ጊዜ አልነበረኝም ። የተሰጠኝ ጊዜ ልብስ ለመለወጥ ብቻ የሚበቃ ነበር ። «ወቴ» ቀልድ አያውቅም ። ለጦር ሜዳ ተብሎ የተሰጠኝን ትጥቅ እንደ ነገሩ ታጠቅሁና እግረ መንገዴን ፊያሜታ ጊላይን ደህና ሰንብች ለማለት ስልክ ደወል ኩላት ። አብረን ነበር ያደርነው ። ባለፉት ሦስት አራት ቀኖች ደግሞ አዲስ ጠባይ ማሳየት ጀምራለች ። እንደ በፊቱ አብረን የትም እንድንታይ አትፈልግም ። ቤቷም እንዳደርሳት ጨርሳ አትፈቅድልኝም ። «ላታዛልቀኝ ለምን ካንተ ጋር በየአደባባዩ እታያለሁ?» የሚል ምክንያት ልትሰጠኝ ትሞክራለች ። ግን ምክ ንያቷ ይህ እንዳልሆነ ይሰማኛል ፡ እሷ ደግሞ የእውነቱን ልትነግ ረኝ አትፈልግም ። የምትደብቀኝ ነገር ነበራት ። ካላመነችበት ወይም ካልመሰላት ያው እንደ ሐማሴን ዘሮቿ ግትር ናት ። በመኪና ስንሔድ ፡ ጠፍቶባት በየመንገዱ የምትፈልገው ሰው ያለ ይመስል አሥሬ ትገላመጣለች ። ሰው ወደ መኪናችን ሲጠጋ ባየች ቁጥር ፡ ጠፍቷት ስትፈልገው የቆየችውን ፍጡር ድንገት ያገኘችው ይመስል ሰውነቷ ድንገት ሽምቅቅ ይልና ትኩር ብላ ትመለከተዋለች ። ከዚያ በአካል አጠገቤ እያለች ባሳብ ጭልጥ ብላ ከአጠገቤ ትጠፋለች ። አይኖቿ ያዩኛል ። ግን በእውነት የሚ ያዩኝ አይመስሉም ።

«ሰው የጠፋብሽ ትመስያለሽ ። ማን ጠፋብሽ? እስቲ በ ሞቴ ንገሪኝ!» ስላት ፡ «እንጃ አባትህ ። ደደብ» የሚል መልስ ትሰጠኛለች ።

«ታዲያስ ፊያሜታ?» አልኳት ።
«ለምንድነው ደግሞ ዛሬ ወታደሩ ኋላውን ያዞረብን?» አለችኝ ።

ወታደሮች በየአውራ መንገዶች ተሰልፈው ነበር ። ወታደሮች «ኋላቸውን» ወደ መንገድ አዙረው ሲቆሙ ፤ የአሥመራ ሕዝብ አንድ ታላቅ እንግዳ ይሔዳል ወይም ይመጣል የሚል ግምት አስቀድሞ ያሳድራል ።

«ጸጋዬ ይሔዳል ሲሉ ሰምተው ይሆናል» በማለት ቀለድኩባትና ፤
«እውነት ፊያሜታ አሁን ወደ አፍአበት መሔዴ ነው ። አሁን ነው የተነገረኝ ። ልሰናበትሽ ነው የደወልኩት» አልኳት ። በመጀመሪያ አላመነችኝም ።

«እውነቱን ነው ፊያሜታ ሙች ። ያንቺ ውሸት የተጋባብኝ መሰለሽ እንዴ? መሔዴ ነው ። በወታደር ልብስ ብታይኝ ሌላ መሰያለሁ» አልኳት ። ዝም ብላ ቆየችና ፤ «በወታደር ልብስ ላይህ አልፈልግም — አባቴ ይሙት » አለች ።
«ለምን?»
«እነሱ ሁልጊዜ ደህና ሁኑ እንዳሉ ነው» አለች ።
«ብዙ ወታደር ወዳጆች ነበሩሽ መሰለኝ!» አልኳት ድንገት ብልጭ ብሎብኝ ። ቅንዓት በስለታም ጥርሱ ልቤን መብላት ጀምሮአል ። ቅንዓት — የፍቅር እሳት! የፍቅር ጢስ! «አንቴን ከማወቄ በፊት ለሆነው ምን ያገባሃል?» አለችኝ።ልክ ነበረች ። እኔን ከማወቋ በፊት ያደረገችው ነገር አያገባኝም ። ቢሆንም አንድ ወንድ ለክብሩ ያለውን ቀናኢነትና ለቤቱ ያለውን ቅናት ያለፈው ታሪክ መጋረጃ አብዛኛውን ጊዜ ሊጋርደው አይችልም ። ያለፈውም ነገር ያስቀናል ። መጀመሪያውኑ ለምን የግሌ አል ነበረችም! ከሌሎች ወንዶች ጋር ጨዋታዋ እንዴት ነበር ታስታውሳቸው ይሆን? ትዝታን በሰው ጭንቅላት ውስጥ መግደል አይቻልም ። ሁልጊዜ ይኖራል ። እና ቅናት ይፈጥራል ። ትክክለኛ አስተሳሰብ አይደለም ። ግን ቅናት አብዛኛውን ጊዜ ከትክክለኛ አስተሳሰብ ነው የሚመነጨው ያለው ማነው? ፍቅር ሁልጊዜ የትክክለኛ አስተሳሰብ ሕጋጋት ተከትሎ የሚሔድ ነገር ቢሆን ጣፋጭና ስቃይ ይሆን ነበር? አላውቅም.....



«ፊያሜታ፣ ስለችግርሽ በእውነት ልትነግሪኝ አትፈልጊም?» አልኳት ፤ መሔዴ ስለሆነ ምናልባት አሁን ትነግረኛለች በማለት ። ሆዴን እየቆረጠኝ መሔድ ደስ አላለኝም ።

«አንተም ወደ ጦር ግንባርህ ፤ እኔም ወደ ጦር ግንባሬ» አለችኝ ።
«ያንቺ ደግሞ የቱ ግንባር ነው?»
«የፍቅር ግንባር........»
«ደህና ፤ ፍቅር ግንባር ላይ በድል እንገናኝ »
«የምንገናኝ አይመስለኝም ጸጋዬ» አለችኝ ።
«ምን ማለትሽ ነው?»
ድንገት ደግሞ ድምጿን ወደ ቀልድ ለወጠችና ፤

«ድል ተገኘ ። ያሥመራ ቤቶች ተዳረሱ ። ሥጋ አለቀ ። ከዚያ በኋላ ቀይ ኮኮቦች ምን ይጠብቃሉ? እንዳልከው ፈትለክ ነው!» አለች ።
እምርሬ «ፊያሜታ ቀልዱን ተይና እውነቱን ንገሪኝ» አልኳት ።

«ስትመለስ ትደርስበታለህ» ብላ በኃይል ስልኩ ላይ ተነፈሰችና፣ «ከናቅፋ የምታመጣልኝ ነገር አለ አባቴ ይሙት» አለች።
«ምን?.....ንገሪኝ»
«ድል ።»
«ስለእሱ አትጠራጠሪ» ብያት ልቤ እንደ ድንጋይ እየከበደኝ ፤
«ፊያሜታ ፤ ልትነግሪኝ የማትፈልጊው ነገር እንዳለ አውቃለሁ ። ግን ምን ይሁን? ምንም የሚያሳዝነኝ ነገር እንደማታደርጊ ተስፋ አለኝ ። እንገናኛለን ። ደህና ሁኝ ማለት አልችልም ። አይትንአሲ እሺ እምባር.....?» ብያት ተነስቼ ወደ አርሚ አቪዬሽን በረርኩ ። ስለፊያሜታ ነበር የማስበው ። አንድ ወንድ ስለአንድ ሴት ሳያቋርጥ ማሰብ ሲጀምር ፍቅር ይዞታል ወይም ሞኝ ሆኗል ለማለት ይቻላል ። ሁለቱንም ነበርኩ ፤ ወይም መሰለኝ ። አሥመራዬን ፤ ውብ የዘምባባ ከተማዬን ፤ ናተይ ሰሜናዊት ጽብቕቲ ፤ ወደኋላ ትቻት ስሔድ ልቤ ኃዘን ተጭኖት እንደ ድንጋይ ይከብደኝ ጀመር ። ከአሥመራም ጋር ፍቅር ይዞኝ

ነበር ። የሚገርመው ነገር አሥመራንና ፊያሜታ ጊላይን ለይቼ አላያቸውም ። ባሳቤ አንድም ሁለትም ሆነው ይታዩኛል ።

የአርሚ አቪዬሽን ሜዳ ንቅናቄ በዝቶበታል ። በየደቂቃው ተዋጊ አይሮፕላኖች ተከታትለው ይነሳሉ ፣ ተከታትለው መጥ ተው ያርፋሉ ። አንቶኖቮች ይነሳሉ ፣ ይወርዳሉ ። መሣሪያዎችና ወታደሮች ይጫናሉ ። አይሮፕላን ጠጋኞች ይጣደፋሉ ፣ የአየር ኃይል ተዋጊዎች ከነሙሉ ትጥቃቸው ይሮጣሉ ፣ ይሔዳሉ ፣ ይመጣሉ ። ሜዳው ድብልቅልቁ ወጥቷል ። አንዳንድ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና የኃይል አዛዦችም ሜዳው ላይ ነበሩ ። ወደ አፍአበት የሚወስደኝ ልዩ አይሮፕላን እስኪዘጋጅ ነበር የም ጠብቀው ።

«የወታደር ልብስ ይቀበልሀል ጃል» የሚል ድምጽ ከበስተ ኋላዬ ሰማሁና ዞር አልኩ ። ኰሎኔል በትሩ ተሰማ ነበር ።

ሳየው ደስ አለኝ ።
«ሰሞኑን በጣም ስፈልግህ ነበር..........»
«አዲሳባ ነበርኩ ። አሁን ገና መግባቴ ነው» አለኝ ።

«እንኳን መጣህ.....»
«የት ልትሔድ ነው?»

«አፍአበት ። የታሸገ ኤንቭሎፕ ትቼልሀለሁ ። ወዴት እንደሚያመራህ ኣላውቅም ግን ጠቃሚ መረጃ ይመስለኛል ። ፓራዲዞ ስለሚባል አንድ ቡና ቤት ነው» አልኩት ። «ፓራ ዲዞ?» ብሎ ሲያስብ ቆየና ፣ «ኢሱማ መኖሪያ ቤቴ አካባቢ አይ ደለም እንዴ? ምንድነው እሱ?» አለኝ ።

«በጽሑፍ ትቼልሀለሁ ። ጊዜ የለኝም» አልኩት ።

ዓይኖቹ ከረጢት አብጅተዋል ። ድካም ይታይበታል ። ዕድሜውን መስሎአል ።

ጠጋ አለኝና ድምጹን ዝቅ አድርጎ ፣ «ቢሮክራሲ ስለሚ ባል ሰው ሰምተህ ታውቃለህ?» ብሎ ጠየቀኝ ።
«ምንድነው እሱ?»



«የኮድ ስም ነው ። ሰውዬው ግርማይ ፣ ጎይቶም ፣ ነራአዩ ፣ አፈወርቂ ሊሆን ይችላል ። ወይም በሁሉም ስም የሚጠቀም ሰው ሊሆን ይችላል ። እዚሁ አጠገባችን ያለ ሰው ሊሆን ይችላል። ብዙ ስምና መልክ ያለው ሰው ነው» አለኝ ።

«ምን የሚሠራ ሰው ነው?»
«በጣም አደገኛ ሰው ነው ካልኩህ ይበቃል..........»

ዕቁባይ ሲላ ትዝ አለኝ ። እሱ ይሆን? አልኩ በልቤ ወይስ ሥዕላይ? የአቦይ ተኽሌ ፍርሀት ሞት ፣ የሻለቃ ታደሰ ቆሪቾና የዕቁባይ አጠራጣሪ ግንኙነት ሁሉ ትዝ አለኝና ፤—

«ከዚህ በፊት ስለሻለቃ ታደሰ ቆሪቾ የሰጠሁህን መረጃ ምን አደረስከው?» ብዬ ጠየኩት ።

«በጥብቅ እየተከታተልነው ነው ። ክትትሉ ጥንቃቄ ያስፈ ልገዋል ። የጅብ ችኩል መሆን የለብንም ። ሙሉ ሥዕል የሚ ሰጠን መረጃ ካላገኘን አንድ ወይም ሁለት ሰው መያዝ ሌሎቹን ማስበርገግ ይሆናል ። አትስጋ ። እሱን ለኔ ተውልኝ» አለኝ ።

«አመራርህ ደስ ይለኛል.....»
«ፊያሜታ ጊላይ እንዴት ናት?»
«ደህና ነች ። ሰሞኑን ትንሽ ተለውጣብኛለች.....»
«እንዴት?»

«የሚያስጨንቃት አንድ ነገር አለ ። ግን ምን እንደሆነ ልትነግረኝ አልፈለገችም ። ክፉ ነገር እንደማይደርስባት ተስፋ አደርጋለሁ ። ከመደሰት ሌላ የምታውቀው ነገር የለም» አልኩት።

«አይዞህ ፣ ስለእሷ ደኅንነት፥አትስጋ» በማለት አጽናናኝና ፣ «ሥዕላይ በራኺስ እንዴት ነው?» ብሎ ጠየቀኝ ።

«ይህን ሰሞን አይቼው አላውቅም» አልኩት
«እሱ ቀበሮ ነው»
«እንዴት?»

«በጣም አስቸጋሪ ፍጡር ነው ። በጣም ብልጥ ነው ።
ጭራው አይያዝም» አለኝ ።

«በእሱ የቀረብክ ትጐስላለህ!»
«ምናልባት የሁሉም ነገር ቁልፍ እሱ ሳይሆን አይቀርም......
ምናልባት..... ምናልባት» ብሎ ሲያስብ ቆየና ፤
«ኦሮማይ ሲባል ሰምተሀል?» ብሎ ጠየቀኝ ።
«ምነው? እዎ ። ሁሉም የሚለው ነው ። የአሥመራ ሕዝብ
ቢያንስ አሥር ጊዜ ኦሮማይ ሳይል አይውልም» አልኩት ።

«ትርጉሙን ማለቴ ነው.....»
«ሆነ ፤ አበቃ ፤ አለቀ ፤ ማለት ነው ።»
«እሱን አውቃለሁ.....»
«ታዲያስ?»
«ሌላ ትርጉም እንዳለው ታውቅ እንደሆነ ብዬ ነው?»
አለኝ ።

«ማለቴ ፤ ለምሳሌ ‘ኦሮማይ’ የሚባል የሆነ ተልዕኮ መኖ
ሩን ታውቅ እንደሆነ ብዬ ነው.....»
«እንዴት ላውቅ እችላለሁ? ቢሮክራሲ! ኦሮማይ! ጓድ
መደበኛ ሥራዬኮ ስለላ አይደለም» አልኩት ።

ፈገግ ብሎ ፤ «እሱን አውቃለሁ» አለኝ ።
«እህሳ?»

«የመረጃ ሥራ የመረጃ ሰዎች ብቻ የሥራ ክልል አይደለም
ባሁኑ ጊዜ ። ሕዝባዊ ባሕርይና መሠረት ሊኖረው ይገባል ።
ሁሉም ለአብዮቱና ላገሩ አንድነት ሰላይ መሆን አለበት ። አብዮ
ተኛ ነኝ ማለት አይበቃም — ጓድ ፤ መለኪያው ተግባር ነው»
አለኝ ።

«ስለትምህርቱ አመሰግናለሁ» ካልኩት በኋላ ፤ ቀጠል
አደረኩና «የተውኩልህ ማስታወሻ ይጠቅምሀል ብዬ ተስፋ
አደርጋለሁ ። ፊያሜታን አደራ ። ቻው» ብዬው ወደ አይሮፕላን
ሔድኩ ።



ከሠላሳ ደቂቃዎች በረራ በኋላ አፍአበት ደረስን ። የእፍአ
ፀቄ አቧራና ግለት ተቀበሉን ። አቧራው በጥፊ ይማታል ።
አፍንጫ ቀዳዳዎች ውስጥ ገብቶ ስለሚጋገር ያፍናል ። ግለቱ
እያሳደደ ይጋረፋል ። የትም ቢገቡ ከአለንጋው ምላስ ለማምለጥ
አይቻልም ። ከሌሎች ሥፍራዎች ጋር ሲነጻጸር አፍአበት ገነት
አይደለም እንዴ? ሲሉ ሰምቼ ካሁኑ ሐሞቴ ይፈስ ጀመር ።

ያን ምሽት የናደው እዝ አዛዥ ከአሥመራ ለመጡ አንዳ
ንድ የበላይ አዛዦች የፖለቲካ መምሪያና የፖለቲካ ክፍል ኃላፊ
ዎችና የፖለቲካ ኮሚሳሮች ስለውጊያው ሁኔታ ገለጻ አድርጎልን
ነበር ። ሁሉም ስለውጊያው አካሔድ አስቀድመው የሚያውቁ
ቢሆኑም ሳይሰለቹ መስማት ነበረባቸው ። ለኔ ግን አዲስ ነበር ።
እዚያ በመገኘቴ ዕድለኛም ነበርኩ ። የውጊያው አጠቃላይ ዝግ
ጅት እንዲህ ነበር ። ሁለተኛው ነጻ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት
በሦስት ዋና ዋና ግንባሮች ፤ ማለትም በአፍአበት ፤ በከርከበትና
በአልጌና ግንባሮች ይሰለፋል ። በከርከበት ግንባር 21ኛና 24ኛ
ክፍለ ጦሮችን ከስንጥቅ ብረት ለበስ ብርጌድ ጋር አቅፎ የተ
ሰለፈው መብረቅ ዕዝ ይባላል ። 19ኛ ፤ 15ኛ እና 23ኛ ክፍለ
ጦሮችን ይዞ በአልጌና ግንባር የተሰለፈው ደግሞ ውቃው ዕዝ
ይባላል ። የመብረቅና የውቃው እዞች ዓይነተኛ ግዳጅ ወይም
«ሚሽን» ጠላት ከናቅፋ ሰብሮ እንዳይወጣ ወይም ወደ ናቅፋ
ሰብሮ ገብቶ ኃይሉን እንዳያጠናክር በደጀንነት የመከላከል ውጊያ
እያካሔዱ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ፤ ከሰሜን ወደ ደቡብ ማጥ
ቃት ነበር ። የጠላት ደጀንና ጠቅላይ ሠፈር ሆና የቆየችውን ናቅ
ፋን በግንባር ቀደምትነት ሰብሮ የመግባት «ሚሽን» የተሰጠው
3ኛ ፤ 17ኛ እና 22ኛ ተራራ ክፍለ ጦሮችን አቅፎ ለተደራጀው
ለናደው እዝ ነበር ። የማጥቃቱ ርምጃ የካቲት 8 ቀን 1974
በ24 መቶ ሰዓት እንዲጀመር ታቅዶ ነበር ። በዚሁ መሠረት
3ኛ ፤ 17ኛ እና 22ኛ ክፍለ ጦሮች ከአፍአበት ወደ ሰሜን መንቃ
ነቅ ጀምረዋል ። ንቅናቄው ከተጀመረ ሦስት ቀን ሆኖታል ።
እኔ የደረስኩት የ22ኛ ክፍለ ጦር የመጨረሻው ኃይል ሲንቃነቅ
ነበር ። አብዛኛዎቹ ሎጋ ወጣቶች ነበሩ ። እና ሁሉም ወደ ውጊያ
ወረዳዎች የሚሔዱ አይመስሉም ነበር ። ሲጫዋወቱና ሲስቁ
ነበር ። መልካቸው ትዝ አይለኝም ። ግን የሁሉም መልክ የኔኑ
ነበር የሚመስለው ። የኔ ፊት ነበር..... የኢትዮጵያ መልክ ነበር ።

ሁሉም ግዳጅ ነበራቸው ። 3ኛው ክፍለ ጦር ከአፍአበት ተነስቶ ጉዞውን ወደ ማማዶ በመቀጠል የማበላን ሸለቆ ይዞ ፣ ናቅፋንና አልጌናን የሚያገናኘውን መንገድ ከዘጋ በኋላ ፣ በዚሁ ግንባር ተከማችቶ የአብዮታዊውን ሠራዊት ንቅናቄ የሚገታውን የጠላት ኃይል ማጥቃት እርስ በእርሱ እንዳይረዳዳ ማድረግ ነበር ። ለ17ኛ ክፍለ ጦር የተሰጠው ግዳጅ ደግሞ ከማሚድ ጠቅላይ ሠፈር በመነሳት በከምጨዋ ጅረት አድርጎ ቲክሲንና የሀረዋ ተራራን ከፍታ ነጥብ 2059 በመከተል በከፍታ ነጥብ 1725 1755 1702 ላይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የማጥቃት ርምጃ ከወሰደ በኋላ ናቅፋን እንዲይዝ የሚል ሲሆን ፣ የ22ኛ ክፍለ ጦር ግዳጅ በበኩሉ ፣ አንደኛ ፣ አፍአበትን በደጀንነት መከላከል ፣ ሁለተኛ ፣ በኩበኩብ ፣ በኤላገርገር ፣ በሰስነብ ምንዳድ ሸለቆዎች በማድረግ የሚሆን ወንዝ ተከትሎ ሔዶ ናቅፋን ከደቡብ ምዕራብ ማጥቃትና መያዝ ነበር ። የወጣው እቅድ ናቅፋን...... በ270 ዲግሪ ከቦ ለማጥቃት የሚያስችል ዕቅድ ነበር ። እና ይገኛል ተብሎ የታሰበው ውጤት የተመሠረተው በሁሉም እዞች የተቀናጀና የተቀነባበረ የመከላከልና የማጥቃት ርምጃና ንቅናቄ ላይ ነበር ።

በሌላ በኩል የጠላት አሰላለፍ እንደሚከተለው ነበር ። አንደኛ ቀለበት ፣ በአፍአበት ዙሪያ የሰሰነብ ምንዳብ ሸለቆ ፣ ከፍታ ነጥብ 2001 ፣ የኩኩብንና የማሚዶን በር እና የመርሳ ጉልጉብን ወደብ ይዘው መሽገዋል ። አንደኛው ቀለበት ከተሰበረ በሁለተኛው ቀለበት ይከላከላሉ ። ሁለተኛው ቀለበት የባሻራ እምባን ፣ የራስ አርማስን ፣ የአንጋብን ፣ የሮሆረትንና የጋዱድን ከፍታ ነጥቦች — 1940 1627 1603 1541 1643 1290 1735 የመከላከያ ምሽጎች ያጠቃልላል ። ሁለተኛው ቀለበት ምናልባት ቢሰበር ፣ የናቅፋን በር ፣ የማሆን ወንዝ ፣ የደንደንን ተራራዎች የአልጌናና ናቅፋን መንገድ ተረተሮች ፣ የሀረዋን ተረተርና የአድሆባን ሸለቆ ይዘው መሽገዋል ። የአድሆባ ሸለቆ በተለይ የማምለጫ በራቸው ስለሆነ በተጠናከረ ኃይል እንደሚከላከሉት ታውቋል ።

የወገንና የጠላት ኃይል አሰላለፍ ከሞላ ጎደል እንዲህ ሆኖ ሳለ ፣ ለጠላት ኃይል የሚያደሉ አንዳንድ ሁኔታዎች ነበሩ ። የወገን ጦር በማጥቃት ስልት ላይ የሚያተኩር እንደመሆኑ መጠን ኃይሉ ከጠላት ሠራዊት ኃይል ቢያንስ ሦስት እጅ በልጦ



መገኘት ነበረበት ። ይህ ሦስት ለአንድ የሚባለው የኃይል ሚዛን የሚሠራው አመች በሆኑ የውጊያ ወረዳዎች ላይ ብቻ ነው ይባላል ። የሣሕል በረሀ መሬት አቀማመጥ ምናልባትም በጦርነት ታሪክ ውስጥ በአስቸጋሪነቱ ተወዳዳሪ የሌለው የመሬት ገጽታ እንደመሆኑ መጠን የወገን ጦር የማጥቃት ርምጃ በሚጀምርበት ጊዜ ከጠላት ጦር በምን ያህል በልጦ መሰለፍ እንዳለበት ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነበር ። ከአሥመራ ወደ አፍአበት በአይሮፕላን ስመጣ የሣሕልን የመሬት አቀማመጥ ከሰማይ በመጠኑም ቢሆን ቃኝቼዋለሁ ። ገዳይ መሬት ነው ።

ሣሕል እንደ ሰንሰለት ተያይዘው ከአድማስ እድማስ ከዓይን እየራቁ በሚነጉዱ ፣ እንደ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ከመሬት ወደ ኅዋው ቀጥ ብለው በሚወረወሩ ፣ ሹል ፣ ድንጋያማ ተራራዎች ፣ እንደ ገሀነብ አፋቸውን በከፈቱ ፣ እንደ ሲኦል በሚያዛጉ ተረተሮች ሸለቆዎች የተሞላ ፣ የተረገመ መሬት ይመስላል ። እውነት ርግማን ያለበት መሬት ሳይሆን አይቀርም! እግዜር ዓለምን ሲፈጥር ተናዶ በከርን እየደቀሰ የተማታበት መሬት ይመስላል ። ንዴቱ ከመሬቱ ገጽታ ላይ ተጽፎአል ። ተደራርበው የተቀመጡት ያገጠጡ ድንጋዮች ተፈጥሮ በዘመናት የቆለላቸው አይመስሉም ፣ እንድ ኃይል ለምጽአት ቀን በጥበብ ጠርቦ ያስቀመጣቸው የመቃብር ድንጋዮች እንጂ ። ተራሮች መረማመጃ ቀርቶ ለእግር መቆናጠጫ የሚሆን ቦታ የላቸውም ። ለሰው ቀርቶ ለዝንጀሮዎችም ቢሆን አያመቹም ። እንዱን የተረገመ ተራራ ሲያልፉ ፣ ከእሱ የባሰ የተራቆተ ፣ ያገጠጠ ሌላ ተራራ ብቅ ይላል — ደብረ እመን ፣ መግዛእቲ! ታምሩ ተራራ! ፤ ደንደን ፣ ጋልደንደን ፣ ካታር ፣ ጉዋ ፣ ሒልሚት ፣ ገረግር ፣ ሐጸይነት ፣ ሮራ ጸሊም ። እና ከሩቅ ሲመለከቷቸው ከል ለብሰው ኃዘን ላይ የተቀመጡ መስለው ይታያሉ ፣ የተራሮቹን ገጽታ እየሸረሸሩ የሚወርዱት ደረቅ ፣ ኖራ መሳይ ቦዮች ደግሞ የኃዘን እንባ ። አንዳንዶቹ ተራሮች እስከ ትከሻቸው ድረስ ጉም ለብሰው ሲታዩ ዓለምን በመናቅ የአመጽ ጋቢ ቈከናንቦ በእብሪት ተወጥሮ የቆመ ወንበዴ ይመስላሉ ። ጠላት የመረጠው እንዲህ ያለውን የተፈጥሮ ምሽግ የሆነ የውጊያ ወረዳ ነበር ። እና የወገን ጦር ጠላት በመረጠው የውጊያ ወረዳ መዋጋት ነበረበት ። ጠላት በተፈጥሮ ምሽጉ ብቻ ተማምኖ አልተቀመጠም ። ባለፉት ስባት ዓመታት ፣ መሬቱን እንደፍልፈል ፈልፍሎ ፣ ድንጋዩን ሰርስሮ ፣

እንኳን ከሰማይ ከቅርብ ሩቅም በዓይን የማይታዩ ሰው ሠራሽ
ምሽጎች ከዳር እስከዳር ገጥግጦበታል ። እያንዳንዱ ምሽግ በአር
ግጥም የሞት ወጥመድ ነበር ። በእንደዚህ ያለው የውጊያ ወረዳ
ከባድ መሣሪያ ፣ ታንክና የጦር አይሮፕላን የሚሠሩት እም
ብዛም ፋይዳ አልነበረውም ። የሰው ልጅና የተፈጥሮ መራራ
ጦርነት ብቻ ነበር ። እና የተፈለገውን ለማስገኘት የሚያስፈል
ገው የሰው ልጅ ወኔና ቆራጥነት ከዚያም ባሻገር ከተአምር ያላ
ነሰ ድርጊት ነበር ።

በተጨማሪ ፣ ጠላት የውጊያ ወረዳዎቹን ሁኔታ በመጠቀም ፣
ያቀደው የውጊያ ስልት የአብዮታዊውን ጦር ንቅናቄ በሰፋት
ለጥጦ ወይም ወጥሮ በመግታት ታክቲክ ላይ የተመሠረተ ነበር ።
ይህን ለማድረግ ቀላል ነበር ። ቁልፍ በሆኑ አንዳንድ የከፍታ
ነጥቦችና መተላለፊያዎች ላይ ባለ 50 ካሊበር መትረየሶች
ጠምዶ የስብጥር ተኩስ መከፈት ብቻ ይበቃል።ሠራዊቱ «ካሚን»
ውስጥ ገብቶ (ሀ ፊደል ቅርጽ) እንዳይቆረጥና እንዳይመታ በግድ
መሰጠጥ ይኖርበታል ። ይህ ደግሞ ከፍተኛ የሰው ኃይል ይጠይ
ቃል ። እነዚህን ቁልፍ ገዢ መሬቶች እንዲከላከል ያደረጉት
በአብዛኛው ከአካለ ስንኩላን ተውጣጥቶ የተቋቋመው 75ኛ
ብርጌድ ነው ይባላል ። አብዛኞዎቹ እግር የላቸውም ። ወደኋላ
ሊያፈገፍጉ አይችሉም ። እና ባለ 50 ካሊቨር የያዘ አንድ አካለ
ስንኩል ወንበዴ ባለበት ካልተደመሰሰ በስተቀር አንድ ሻለቃ
ጦር ገትሮ ሊይዝ ይችላል ። በዚህ ላይ ጠላት የተማመነው
ፈጥኖ በመነቃነቅ ችሎታው ላይ ነበር ። ተረተሩን ያውቀዋል ።
መግቢያ መውጫውን አጥንቷል ። አየሩን ተለማምዶታል ። እንደ
በረሀ ግመል ውሀ ሳይጠጣ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ ይችላል ። ውሀ
የሚገኝበትንም ነጥብ ያውቃል ። ውሀ ሕይወት ነውና ውጊያው
በአብዛኛው የውሀ ነጥቦችን በመያዝ ተጋድሎ ላይ የሚመሠ
ረት ይሆናል ።

ባንጻሩ ፣ አብዮታዊው ሠራዊት በካርታ ላይ ካልሆነ በስ
ተቀር የውጊያ ወረዳዎቹን እምብዛም አያውቃቸውም ። ካርታዎ
ቹም ላይ ሠፍረው የሚገኙት ያንዳንድ የውጊያ ወረዳዎች ስም
ርቀት ፣ ከፍታና ስፋት አልፎ አልፎ በትክክል ተመዝግበው
አይገኙም ። አቅጣጫን ስቶ የመጥፋት ዕድል ሊያጋጥም ይች
ላል ። በዚህ ላይ ደሞ እንደሽሮ ደም አፍልቶ የሚያንተከትከው
የአካባቢው አየር ሁኔታ አለ ። ለሠራዊቱ እንግዳ የሆነ የአየር



ጠባይ ነው ። አየሩ ራሱ ገዳይ ነው ። ይህም ይሁን የሰው ልጅ
ከፈለገና ከቆረጠ የማይቋቋመው ነገር የለምና ፣ ውሀ ጥማቱንና
ግለቱን ይቋቋመው ይሆናል ። ዋናው ችግር እየተዋጉ እንደ ፎቅ
ቀጥ ብለው የቆሙትን ተራራዎች ከመውጣቱ ላይ ነበር ። የና
ቅፋ ተራራዎችን ፣ ስንቅና ትጥቅ ይዞ እየተዋጉ የሚወጡ መሆ
ናቸው ይቅርና ፣ በባዶ እጅም እየቧጠጡም በቀላሉ የሚሞከሩ
አይደሉም ። አይበገሩም ። ተራሮቹ ጫፍ ላይ መሽጎ የተከማቸው
ጠላት ደግሞ ዝም ብሎ አይጠብቅም ። ራሱን ለመከላከል
ብዙ ጥረት ማድረግም የለበትም ። ምቹ ሥፍራ ላይ ተቀምጦ ፣
ቦምብ ማዝነብና የድንጋይ ናዳ ውርጅብኝ ማውረድ ብቻ ይበ
ቃል ። እንዲሀ ዓይነቱ ውጊያ ነበር አብዮታዊ ጦሩን የሚ
ጠብቀው ። ራስን ለመስዋእትነት የማቅረብ ሚሽን ወይም
ተልዕኮ ነበር ። እና ለዚሀ ተዘጋጅተዋል ። ዝግጁነታቸው
ፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር ። አየሁት ። ኮራሁ ።

ገሰጻውን ያደረገልን አንድ ረዘም ያለ ፣ ቀጭን ፣ መልከ
መልካም ፣ ወጣት ብርጋዴር ጄኔራል ነበር ። እሁን በቅርብ
ቀን ነበር ሠራዊቱ ፊት የብርጋዴር ጄኔራልነት ማዕረግ የተሰ
ጠው ። ቀይ ፣ መልከ መልካም ፊቱን የሣሕል ንዳድ አክስሎ
ታል ፣ የሣሕል ቁር አርሶታል ፣ የሣሕል ከሚሲን አዥጎርጉሮ
ታል ። ብዙ አይናገርም ። እንደ ፈላስፋ ረጋ ብሎ እያሰበ ረጂም
ጢሙን በረጃጅም ጣቶቹ ይጎነትላል ። ጥቁር የብረት ከዘራ
ከእጁ አትለይም ፣ ይመረኮዝባታል ፣ ካርታ ያሳይባታል ፣ በእሷ
ረዳቶቹን ይጠራል ፣ ይሸኛል ። ረዳቶቹ ከፊቱ ይልቅ የከዘራውን
ንቅናቄ ነው የሚመለከቱት ። ትእግሥቱንና ቆራጥነቱን አደነቅ
ሁለት ። በተለይም ፣ «ከነዚህ ሰዎች ጋር አንድ ላይ ብንቆም ፣
ይህን ገዢ መሬት ይዘን ፣ የሚበግረን የውጭ ጠላት ከቶ አይኖ
ርም ነበር ። ሁለታችንም ወኔ ለወኔ የምንተዋወቅ ያንዲት ኢት
ዮጵያ ልጆች ነበርን ። ያለመታደል ነው ። ለዚህም ነው ይህ ጦር
ነት እጅግ አሳዛኝ ፣ እጅግ መራራና አሰቃቂ የሚሆነው» በማ
ለት በመጨረሻ የተናገረው ነገር ቤጣም አድርጎ ልቤን ነክቶት
ነበር ።

ኮሎኔል ታሪኩ ወልዳይ ነበር ስለጠላት የውጊያ ስትራተ
ጂና ታክቲክ ሲገልጽ የቆየው ። ጠቁሮአል ፣ ከስቷል ፣ ጠጉሩ

የባሰውኑ ረዝሟል ። ጢሙ አድጓል ። ጠጉር ብቻ ሆኖ ነበር
የሚታየው ። እና ቁመት የጨመረ መስሎ ታይቶኝ ነበር ።
በገለጻው መደምደሚያ ላይ ፣ «በአጠቃላይ የምናካሂደው ጦርነት
መስዋእትነትን የሚጠይቅ ነው ። ለዚህ ተዘጋጅተናል ። በብዙ
መስዋእትነት የአብዮታዊ ጦር አባሎች ክቡር ሬሣ ላይ የድል አርማ
ዎቻችን የአብዮታዊ ጦር አባሎች ክቡር ሬሣ ላይ የድል አርማ
ችን እንደሚያውለበልብ ጥርጥር የለኝም» ብሎ ነበር ። አል
ተጠራጠርኩም ። ኰሎኔል ታሪኩ የማያደርገውን ነገር የሚናገር
ሰው አይደለም ። ግን ለምን እንደሚሸሽኝ አልገባኝም ። አፍአ
በት ከደረስኩበት ጊዜ ጀምሮ ባየሁት ቁጥር ከሩቅ ይሸሸኛል ።
ራሱን ለመስዋዕትነት በገዛ ፈቃዱ ያዘጋጀ ፣ ቀይ እንቡጥ የተባለ
አንድ ሻለቃ ምልምል ጦር ይዞ ከፍታ ነጥብ 1702 ላይ ለመዝ
መት እየተዘጋጀ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ ።

የቀይ እንቡጥ ሻለቃ ጦር አባሎች በሙሉ ከእሱ ሳይለዩ
ከአጋዴን እስከ ሣሕል ሲዋጉ የቆዩ ናቸው ይባላል ። እንደ
ወንድም ይወዱታል ፣ እንደ ጦር አለቃ ያከብሩታል ። እሱም
እንደራሱ አድርጎ ይወዳቸዋል ። እያንዳንዳቸውን በሙያቸውና
በስማቸው ያውቃቸዋል ይባላል ። ባንድ ልብ ፣ ባንድ መንፈስ ፣
ላንድ ዓላማ ወደከፍታ ነጥብ 1702 ለመዝመት ሁሉም ዝግጁ
ነበሩ ።

ከፍታ ነጥብ 1702 ትልቁ ተራራ ሆኖ አይደለም ። ከእሱ
የሚበልጡ ፣ ለምሳሌ እንደ ከፍታ ነጥብ 2059 ያሉ ተራራዎች
አሉ ። ምናልባትም ከዚህም የሚበልጡ ሌሎች ይኖራሉ ። ነገር
ግን ፣ ከፍታ ነጥብ 1702 የናቅፋ በር ቁልፍ ነው እየተባለ የሚነ
ገርለት ከናቅፋ አየር ሜዳ በስተጀርባ በአራት ኪሎ ሜትር ርቀት
ላይ የሚገኝ ስትራተጂካዊ ተራራ ነው ። ይህን ገዢ መሬት ከያዙ
የናቅፋን በር ለመቆጣጠር ይቻላል ። እና የኰሎኔል ታሪኩ
ኢላማ ይህ ገዢ መሬት ነበር ። እንደሰማሁት ስለ ከፍታ ነጥብ
1702 ሲያስብና ሲያልም እየዋለ ያድራል ይባላል ። ስለእሱ
ያስባል ፣ ስለእሱ ያልማል ። ስለእሱ ይናገራል ። ሌት ፣ አንዳንዴ
በቅዠት ልቡ እየባነነ ይነሳል ይባላል ። ያ ተራራ የከረረ ስሜት
አሳድሮበት እብድ አድርጎታል ሲሉ ሰምቻለሁ ። ግን ከሩቅ የሚ
ሸሽኝ በዚህ ምክንያት የተነሳ አልመሰለኝም ። በፊያሚታ ጊላይ
ምክንያት መሆን አለበት አልኩ በልቤ ። ሌላ ምን ይኖራል?
ጠብ የለንም ። ከዚህ ቀደም የተዳረስንበት ነገር የለም ። ሥራና



ጊዜ ባያራርቀን በልጅነት ጓደኞች ነበርን ። ወይስ ዕድሜ አራር
ቆን ይሆን ? ዕድሜ ሰዎችን ይለውጣል ። ጓደኞች እንደ ባዳ ሊ
ተያዩ ይችላሉ ። ምክንያቱን ለማወቅ ፈለኩ ፤ እሱን ለማነጋገር
የምፈልግበት ሌላም ምክንያት ነበረኝ ። ከእሱ ጋር ወደ ከፍታ
ነጥብ 1702 ለመሔድ ቆርጬ ነበር ። ስለዚህ ወደማረፊያዬ
አልሔድኩም ። ኰሎኔል ታሪኩን መፈለግ...... ነበረብኝ ። ዕድሜ
ለፍሬው ዘሪሁን ኰሎኔል ታሪኩን ለማግኘት ጊዜ አልወሰደ
ብኝም ። ፍሬው የአፍአበትም ከንቲባ ሆኗል ። የደረሰበት ከተማ
ሁሉ ከተማው ይሆናል ። ዝናው ቀድሞት አፍአበት ደርሶ ኖሮ ፣
ጦሩ ሁሉ «ከንቲባ» እያለ ነበር የሚጠራው ። ከሙቼው ደርሶ
በሁሉም ዘንድ ተወዳጅነትን ለማትረፍ እንደቻለ በጣም ያስገ
ርማል ። ኰሎኔል ታሪኩን ተከትለን ወደ ከፍታ ነጥብ 1702
ለመሔድ ተስማምተን ነበር ። ሌሎች ሦስት ጋዜጠኞች ፣ አንድ
ቴሌቪዥን ፊልም አንሺና ረዳቱ ፣ እንዲሁም አንድ ፎቶግራፍ
አንሺ፣ በቀልድ «ከአዝማቻችን እንዴት ተለይተን እንቀራለን!»
በማለት ከኔ ጋር ለመሔድ ቆርጠው ነበር ።

የቀይ እንቡጥ ሻለቃ ጦር ሠፈር ከአፍአበት ሆስፒታል ፊት
ለፊት ነበር ። የጦሩ አባሎች እሳት አንድደው የፈላ «ሚሊ ድራ
ፍት» እየጠጡ ይዘፍኑና ይጨፍሩ ነበር ። የጦርነት ዳንኪራ
ነበር የሚረግጡት ። የኰሎኔል ታሪኩ ረዳት ድንኳኑን አሳየኝ ።
የፋኖስ መብራት ነበር ። ኰሎኔል ታሪኩ ጠርሙስ ውስኪ ፊቱ
ገትሮ ፣ ካንድ ትንሽ አግዳሚ የእንጨት መቀመጫ ላይ በመሆን
ሽጉጡን ይወለውል ነበር ። እኔን ማየት ደስ ያለው አልመሰለ
ኝም ። ቢሆንም ፣ «ይህችን ጠርሙስ ብቻህን ልትጨርሳት ኖሮ
አል!?» አልኩና ከፊት ለፊቱ ቁጭ አልኩ ።

የግዱን «ያዝ» አለና ጋቤጣ ሰጠኝ ። ብርጭቆ አልነበረም ።
«ለድል እና በልጅነት አብረን ላሳለፍነው ጊዜ!» ብዬው ጋቤጣ
ዬን አነሳሁ ።

«ምናልባት የመጨረሻ ጠርሙሼም ፣ የመጨረሻ ጽዋዬም
ናት ። ካሥመራ ነው ይዤአት የመጣሁት ለድል!» ብሎ
እሱም ጋቤጣውን አነሳ ። ጋቤጣዎቻችንን አጋጨን ። ደረቁን
ውስኪ ደህና አድርጌ ከተጎነጨሁ በኋላ ፣ «ለምን እንዲህ ትላ
ለህ?» ብዬ ጠየኩት ።

«የምመራው ራሱን ለመስዋዕት ያዘጋጀ ጦር መሆኑን ታውቃለህ?» አለኝ ።

«አውቃለሁ ። ግን በድል ትመለሳለህ ። እና ገና ብዙ ጽዋ ዎች አብረን እናነሳለን» አልኩት ።

«ተስፋ አለኝ ።» ብሎ ሽጉጡን ቀጭ ፥ ቀጭ አድርጎ ከፊ ተሽ በኋላ መያዣው ውስጥ ጨምሮ ዝም አለ ።

ዓይኔን ይሸሽ ነበር ። ደረቁ ውስኪ ድፍረት ስለሰጠኝ ነው መሰለኝ በቀጥታ ወደመጣሁበት ወደ መጀመሪያው ጉዳይ አመራሁና «ምን አደረኩህ? ለምንድነው የምትሸሽኝ?» ብዬ ጠየኩት ።

ከአንገት በላይ በሆነ አነጋገር ፥ «የምሸሽህ ይመስልሃል እንዴ?» አለኝ ።

«እውነት ታሪኩ ንገረኝ ። በኔና ባንተ መካከል ምን የሆነ ነገር አለ? ለማወቅ እፈልጋለሁ» አልኩት ።

«ምን ማለትህ ነው? ምን ሆነ?»

«ፊያሜታ ጊላይ ትሆን ያቀያየመችን?»

«ማን ናት ፊያሜታ ጊላይ?» ቢልም ፊቱ ድንገት ሲለወጥ ታየኝ ።

«እውነቱን ንገረኝ ። እኔ እያወቅሁ አንተን ቀርቶ ሌላም ሰው በዚህ የማስቀይም ሰው አይደለሁም» አልኩት ።

«በእንደዚህ ዓይነት ነገር ላይ መነጋገር አሁን ብንተው ይሻላል» በማለት በነገሩ ወደፊት ላለመግፋት በቁርጠኛነት ከወሰነ በኋላ ፤

«ስለጦርነቱ እንጫወት ። እዚህ ምን አመጣህ?» ብሎ ጠየ ቀኝ ። እኔም ሁኔታውን በማየት ነገሩን ትቼ ፥ «ጦርነቱ የጋዜጠ ኞችም ጦርነት ነው ። ታሪክ ለመመዝገብ ነው የመጣሁት» ካል ኩት በኋላ ቀጥዬ ፥ «ፈቃድህ ከሆነ ካንተ ጋር ለመሔድ እፈል ጋለሁ» ብዬ ምኞቴን ገለጽኩለት ።

«ወዴት?»

«ወደ ነጥብ 1702..........»

«አብደሀል!»



«ምነው? አንተ አብደሀል?»

«የመስዋእትነት ተልእኮ ነው..........»

«አውቃለሁ ። የኔ ደም ብርቅ ነው ያለህ ማነው? ወይስ ለመስዋእት የሚቀርብ የሰባ ጣቦት መስዬ አልታየሁህም?» ብዬ አሳቅሁት ።

ሁላችንም ጋቢጣዎቻችንን እንደገና ሞላን ።

ደስ እያለው ሔዶ ነበር — «ጥሩ አሳብ ነው ። ቆራጥ መሆንክን አደንቃለሁ...... እውነት ። ግን እኔ ልወስንልህ አል ችልም ። የበላይ ውሣኔ ይጠይቃል » አለኝ ።

«የማንን?»

«የእዝ አዛዡን» ብሎ ቀጠለና ፥ «ይህ ወታደራዊ አፕሬሽን ነው ። በውጊያ ወረዳ ጋዜጠኞችን የማስተናገድ ልምድ የለንም ።

«ስለእሱ አትስጋ ። ራሳችንን እንጠብቃለን» ብዬው ቀጠልኩና ፥ «ጄኔራልን እጠይቀዋለሁ ። አንተ ከደገፍከኝ እሱ እምቢ አይልም ። ስለታሪክ እሱ ከኔ ይበልጥ ይጨነቃል ። ሽኩም እንደማንሆንብህ በዚህ ውስኪ እምልልሀለሁ» አልኩት ።

«እዎ ፥ ብዙዎቻችን ስለግል ታሪካችን ይበልጥ እንጨነ ቃለን ። ልክ ነህ» አለኝ ።

«ይህን ማለቴ አልነበረም ። ግን ፥ እንዴት?» አልኩት ።

«ዛሬ በአዛዥነት የተሠማራነው ሁሉ ወጣት መኰንኖች ነን ። እና አብዛኛዎቻችን የሥልጣን ጉጉት ሳይኖረን አይቀርም ። በደህና ሁኔታ ብዙዎቻችን ምናልባት ከብርጌድ መሪነት አናል ፍም ነበር ። በቢሮክራሲም ውስጥ ምናልባት እንደዚሁ ሳይ ሆን አይቀርም ። ያንድ ክፍል ኃላፊ መሆን የማይገባው ዛሬ የመምሪያ ኃላፊ ሆኖ ይገኛል ። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በግድ የሥልጣን ጉጉትን ይፈጥራል — ያራባል...... እና ያለብንን ኃላፊነት ወደ ጎን እያልን ሥልጣን ስናባርር ፥ ተንኮል ስንሸ ርብ ፥ እንዱን በሾኬ ጥለን እንዴት እንደምናልፈው ስናውጠ

ነጥን እንውላለን ። አደገኛ አዝማሚያ ነው ። አዎ ፤ እንዳልኩት ተራ ረዳት ሆነው ከመሥራት ደረጃ ሊያልፉ የማይችሉ ብዙ ግለሰቦች ዛሬ ፤ ዕድሜ ላብዮቱ ፤ ቱባ ሹማምንት ሆነዋል ። ጥሩ ነው ። አብዮት የመደብ ሹም ሽረት አይደል? ነው'ኮ ። ግን ለሥልጣን ሽሚያ ሠፊ በር የተከፈተ እንደሆነ ደግ አይደለም ። ጓደኛው ካጠገቡ እንደቀስት ወደ ላይ ተወርውሮ ሥልጣን ኮርቻ ላይ ጉብ ሲል ያየ ሰው ሁሉ ፤ ዛሬ እኔስ ከማን አንሳለሁ? እገሌን አላያችሁትም እንዴ? ትናንት ምን ነበር? በማለት ሥልጣን ፈላጊና አሳዳጅ እየሆነ ነው ። ሥልጣን የምንፈልገው ለሕዝብ ጥቅም ፤ ዕድገትና ብልጽግና ፤ ኩራትና ልዕልና ቢሆን ኖሮ ባልከፋም ነበር ። ግን አይደለም ።

«ለግል ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው ሥልጣን የሚያሳድዱ ሰዎች በዝተዋል ። አደገኛ አዝማሚያ ነው — በሦስት ነገሮች ምክንያት ፤ ያለምንም ችሎታ ሥልጣን የሚፈልጉ ወይም ሥልጣን ላይ የወጡ ሰዎች ሲበዙ አገር ይበደላል፡አንደኛ አገር ቀልድ አይደለም ። አገር ፤ ታውቀኛለህ ፤ አውቅሃለሁ፡ጀርባዬን እከክልኝ እክልሃለሁ በሚል መርሕ ተጠራርተው በተሰበሰቡ ሰዎች አትመራም ። ሁለተኛ ፤ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በሥልጣን አካባቢ እየበዙ ከሔዱ አድሃሮት መከተሉ አይቀርም ። ሚሌቫን ጂላስ እንዳለው አዲስ መደብ እንዳይፈጠር ያሰጋል ። ሦስተኛ ፤ የሥልጣን መባለግ የማይቀር ነው ። ለምን መሰለህ? በርስት ፤ በቤት ኪራይ ፤ በልዩ ልዩ ገቢ መኩራራትና መንደላቀቅ ዛሬ ቀርቷል ። የበፊቱ የገቢ ምንጭ ደርቋል ። የብዙዎቻችን ግላዊ ሱስ ግን እንዳለ ነው ። አብዮቱ አልወረሳቸውም ። ታዲያ ምን ይሁን? ብልሐቱ ቶሎ ዘሎ ሥልጣን መጨበጥ ነው — በመምሰልና በማስመሰል ፤ በብልጠት ፤ ባፈጮሌነት ፤ በዘዴ ፤ በተንኮል ። የተንኮል ገበያ ደርቷል ። ከዚያ እንግዲህ ምናለ? መኪናና ቪላ ማማረጥ ፤ ጥሩ መብላት ፤ መጠጣት ፤ መልበስ ፤ መሽቀርቀር ፤ በየዕለቱ የበሰለ ብርቱካን እየመሰሉ መሔድ — እንዲያም ሲል ቆንጆ ቆንጆዎችን እያማረጡ ሕይወትን መቅጨት ። በስልክ ሀሎ! እያሉ ቤት ለምትፈልገው ማሰፊያ ቤት ፤ ሥራ ለምትፈልገው ማሰፊያ ሥራ ፤ የደመወዝ ጭማሪ ለምትፈልገው ማሰፊያ ጭማሪ ። ተጠቅሞ መጥቀም ፤ በልቶ ማብላት ፤ ማብላትና መብላት ። በሥልጣን እየተጠቀሙ ጥቅሞችን ለወደዱትና ለፈለጉት እንደ ጠበል ማርከፍከፍ ። ይህ ሁሉ እየታየ ነው ። እኔ የምሰጋው



በሕዝብ ስም ተነስተን ከሕዝብ እየራቅን — ለሕዝብ ባዳ እየሆን እንዳንሔድ ነው ። ጥራት! ጥራት! በሕዝብ ስም ከሚነግዱ ነጋዴዎች አብዮቱን ማጥራት ያስፈልጋል ። ለግል ታሪክ ፤ ለግል ዝና ይበልጥ ስለምንጨነቅ ኅብረት ጠፍቶ ግላዊ ሩጫና ጀብደኝነት ይነግሣል ። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በተለይ በጦር ሜዳ አደገኛ ነው ። እኔ ከጠላት ይልቅ በጣም የሚያሰጋኝ ይህ ነው» ብሎ አጫወተኝ ።

«ምን ይደረግ! አብዮት ነው ። ያብዮት ወቅት ነው ። አብዮት የውሀ ልኩን እስኪያገኝ ድረስ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ይኖራል» አልኩት ።

«አብዮት የንዑስ ከበርቴዎች ሽግሽግ ማለት አይደለም» ብሎ ድንኳኑ ውስጥ ተሰቅሎ የሚገኘውን አንድ አርማ በልዩ ትኩረት ሲመለከት ከቆዩ በኋላ ፤ «በቅድሚያ የሰፊውን ሕዝብ ኑሮ መኖር ፤ ሞቱን መሞት መማር አለብን ። ከእሱ ምኞት ውጭ የሆነ ምኞት ሊኖረን አይገባም ። ይህን እንተውና እንጠጣጃል» ብሎ ጋቢጣውን አነሳ ።

ጠጣን ። ድንገት ጸጥ ብሎ ቀረ ። የቀይ እንቡጥ ጦር ፉከራና ቀረርቶ ይሰማ ነበር ። ዛሬ ዘፈንና ጨዋታ ፤ ነገ ጦርነትና ሞት ። የወታደር ኑሮ...... ሕይወት...... «የመንደራችን ልጆች እየሰበሰብክ የጦርነት ጨዋታ ስታጫውተን የምትውለው ትዝ ይልሀል?» አልኩት ።

ፈገግ ብሎ ፤ «የወደፊት ኑሮዬ ይታየኝ ነበር መሰለኝ!» አለ ።

«መኖር ደግ ። እውነተኛውን ጨዋታ አብረን ልንጫወት ነው» አልኩት ።

«አዎ ፤ መኖር ደግ ነው» ብሎ በረጂሙ ተነፈሰና ፤

«አሥመራ እንዴት ናት» አለኝ ።

«አልተለወጠችም ። አሁንም ውብና አሳዛኝ ከተማ ናት» አልኩት ።

«ኤርትራ በሙሉ ውብና አሳዛኝ ናት» አለኝ ።

«በቀይ ኮከብ ዘመቻችን አንድ ዓይነት ተሐድሶ ታገኛለች ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ» አልኩት ።

«የኔም ተስፋ ይኸው ነው» ብሎኝ ዝም አለ ።

የውስኪ ጠርሙሳችን ባዶ ሆናለች ። የቀይ እንቡጥ
ጦር ፉከራ ፣ ቀረርቶና ጭፈራ ከበፊቱ አይሎ ይሰማ ነበር ።

በመጨረሻ—«የሚያሳዝነው ተገንጣይነት በኤርትራ ምድር
ያልበቀለ ፣ ከኤርትራውያን ጭንቅላት ያልወጣ የባዕዳን ተጽዕኖ
መሆኑ ነው ። ሌላው የሚያሳዝነው ነገር ይህን የባዕዳንን የበኩር
ልጅ በመሣሪያነት የሚያገለግሉትም ሆኑ የሚዋጉት የዚሁ
ክፍለ ሀገር ተወላጆች መሆናቸው ነው ። በሺህ የሚቆጠሩ ኤር
ትራውያን ይህችን ውብ የሆነችና አሳዛኝ አገር የሚያደሙትን
ያህል ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ኤርትራውያን ደግሞ ባንጻሩ ፣ ለዚች
አገር ክብርና አንድነት እየደሙላት ነው ። ለምሳሌ እንዳንተ
ያሉት ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አማራጭ የለውም ። ሕልውናው
አንድነቱ ብቻ ነው ። አንድ ኢትዮጵያዊ አንድነቱን አጥቶ እን
ዴት ሊኖር እንደሚችል አይታየውም!» አልኩት ።

«እኔም አይታየኝም ። መቸም ስብእናውን አጥቶ የሚኖር
ሕዝብ የለም» አለኝ ።

በጣም አድርጎ ሲከነክነኝ የቆየ ነገር ስለነበረ ፣ ያኔ በድል
አድራጊነት ሲገሠግሥ የመጣው ሠራዊት ፣ ተፈተው በመፈር
ጠጥ ላይ የነበሩትን ወንበዴዎች እያሳደደ ሳይደመስስ ለምን
ቀረ? ወንበዴዎቹ ፋታ አግኝተው ናቅፋ ላይ እንዲሰባሰቡና
እንዲጠናከሩ የሆነበት ምክንያት ምን ነበር? ድሉን በማስፋት
ያኔ ቢደመስሱ ኖሮ ፣ ዛሬ ተጨማሪ መስዋእት እንከፍል ነበር
ወይ? ብዬ በጥያቄ አጣደፍኩት ።

«ምናልባት ፣ ሠራዊቱ ድሉን በማስፋት የጠላትን ወገን
እስከመጨረሻው ሰው ከመደምሰስ የተገታበት ምክንያት ፣
ጠላት ሽንፈቱን ተገንዝቦ የውይይትና የእርቅ መንገድ ይመር
ጣል በሚል ግምት ይሆናል ። እርግጠኛ አይደለሁም ። የኤርትራ
ችግር እንዳያልቅ የሚፈልግ ማን ይኖራል?» ብሎኝ ዝም አለ ።

ብዙ ሊያናግረኝ አልፈለገም ። ልቡ ከቀይ እምቡጥ ጦሩ
ጋር ነበር ። በፊያሜታና በእሱ መካከል ስላለው ግንኙነት
ለማወቅ የምችልበት መንገድ በማጣቴ ነደደኝ.....



# ም ዕ ራ ፍ

## አ ራ ት -- 2

የጋዜጠኞች ቡድን ቀይ እምቡጥ ከተባለው ልዩ ሻለቃ ጦር
ጋር ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 እንዲሔድ ለማሳመን የተደረገው
ጥረት ቀላል አልነበረም ። በመጀመሪያ አከራካሪ የነበረው ነጥብ
ማን ኃላፊነቱን ይወስዳል? የሚል ጥያቄ ነበር ። ታሪክን ቀርጾ
በማስቀረት ለትውልድ እንዲቆይ በማድረግ ረገድ ጋዜጠኞችም
እኩል ኃላፊነት ያለባቸው ስለሆነ ፣ ኃላፊነትን መውሰድ የእነሱ
ፈንታ ነው ፣ መሆንም አለበት የሚለው ነጥብ እምብዛም አላከ
ራከረም ። ይልቅ በጣም አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ነጥብ ፣ ቀይ
እምቡጥ የተባለውን ጦር ተከትላችሁ ለመሔድ ምን አስመረጣ
ችሁ? የሚለው ፣ ልዩ ግብረ ኃይል ፣ ማለትም ፣ ራሱን በፈቃደኛ
ነት ለመስዋእትነት ያዘጋጀ ግብረ ኃይል እንደመሆኑ መጠን
እሱን አጅባችሁ መሔድ አጉል ጀብደኛነት ይሆናል በማለት ፣
ይህን ልዩ ግብረ ኃይል አጅበን እንዳንሔድ የሚከላከሉን አንዳ
ንድ አዛዦች ሲኖሩ ፣ ከቀይ እምቡጥ ጦር የበለጠ ተልእኮ ያላ
ቸው ጦሮች አሉ ፣ እነሱን ተከትላችሁ ብትሔዱ ፣ ሁኔታው
ለሥራችሁ ያመቻል ፣ እንደምትሉት በእርግጥ ታሪክን ቀርጻችሁ
ለትውልድ የማስቀረት ዓላማ ካላችሁ ፀዚሁ ግንባር ከሚዘም
ቱት ብርጌዶች ጋር ብትሰለፉ ይሻላል በማለት የከረረ ክርክር
የሚያቀርቡም ነበሩ ። በግልጽ ፣ ከእኔ ጋር ለምን አትመጡም?
የሚሉ አዛዦችና የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊዎችም ነበሩ ። ከቀይ
እምቡጥ ልዩ ጦር ጋር ለመዝመት አንደኛውን ቆርጨ ነበርና
በአሳቤ ጸናሁ ።

«ጓድ ጸጋዬ ፣ በጦር ሜዳ አሳበ ግትርነት ሀታ የለውም»
አለኝ ፣ የናደው እዝ አዛዥ ጢሙን እየጎነተለ ።

«እኛም በፈቃደኛነት ራሳችንን ለመስዋእትነት ለማቅረብ
መብት አለን ። ወደ ከፍታ ነጥቧ 1702 እንሔዳለን በቃ ። በዚህ
ነጥብ ላይ በመከራከር ጊዜ ለምን እንደምናጠፋ አይገባኝም?»
በማለት የመጨረሻ አሳቤን አጠናክሬ ገለጽኩ ። ምን ቸገረኝና?
ጦር ፍርድ ቤት የለኝም! አሳቤን የሚያስለውጠኝ ነገር አልነበ
ረም ። እኔም እንደ ኰሎኔል ታሪኩና እንደ ቀይ እምቡጥ ጦር
አባሎች ፣ ከፍታ ነጥብ 1702 የከረረና የጋለ ስሜት እያሳደረብኝ

ሔዶ ነበር ። ወኔያቸው ወኔዬ ፣ ሕልማቸው ሕልሜ ሆኗል ። ድላቸው ድሌ ይሆናል ፣

ሞታቸውም ሞቴ ። ቀንም ሆነ ሌት ፣ ከፍታ ነጥብ 1702 ጫፍ ላይ ወጥቼ ስቆም በእውኔም ሆነ በሕልሜ ይታየኝ ጀምሮ አል ። ከፍታ ነጥብ 1702 ሁለተኛ ተፈጥሮዬ ሊሆን ምንም አልቀረውም ።

ከስብሰባው ስንወጣ ፣ ኰሎኔል ታሪኩን ፣ «ምነው ዝም አልክ? ልትደግፈኝ ይገባ ነበር» አልኩ ።

«ምን ብዬ?» አለኝ ።
«ወሳኝ ተልእኮ ነው በማለት......»
«ደግሞ ለራሱ ታሪክ ሲል ነው ይበሉኝ?»
«ቢሉህስ?»

«እኔ የማስብለትና የምጨነቅለት የግል ታሪክ የለኝም» ካለኝ በኋላ ፣ ረጃጅም እጆቹን የት እንደሚያስገባቸው እየተቸ ገረ ፣ «ለማንኛውም ነገር እንኳን ደስ ያለህ ። ከዛሬ ጀምሮ በኔ ቁጥጥር ሥር መሆንክን እወቅ ። እና ቀልድ የለም ። እመነኝ ፣ ምን አቀበጠኝ? ብለህ የምትቆጭበት ጊዜ ሩቅ አይደለም» ብሎኝ ሔደ ረጃጅም ቅልጥሞቹን እየዘረጋ ። ጠበንጃ ሲይዝ ብቻ ነው እጆቹን ምን ላይ እንደሚያውላቸው የሚያውቀው ። እግሮ ቹም ቅልጥፍና የሚያገኙት በጦር ሜዳ ብቻ ነው ይባላል ። ካልጐተጐቱት በስተቀር ብዙ አይናገርም ። ጊዜውን የሚያሳል ፍበት ልዩ ነገር የለውም ። ጠርሙስ ውስኪ ፊቱ ገትሮ ዝም ብሎ ይጠጣል ። አንዳንዴ፣ በጦር ሜዳዎች ካጠገቡ የወደቁትን የጦር ባልደረቦቹን እያሰበ ዝም ብሎ እንባውን ያፈሳል ። ተጫ ዋችና ደስተኛ የሚሆነው በጦር ሜዳ ነው ይባላል ። እሱን በጦር ሜዳ የማይበት ጊዜው ሩቅ አልነበረም ። ቀይ እምቡጥ ሻለቃ ጦር ያን ቀን ከሰዓት በኋላ ፣ በ1300 ሰዓት እንዲነቃነቅ ታዞ ነበር ።

ልክ በተባለው ሰዓት ከእፍእበት ተንቀሳቀስን ። ቀይ እም ቡጥ ጦር እግረ መንገዱን ፣ ቀደም ብሎ ለተንቃነቀው ለ17ኛ ክፍለ ጦር ብርጌዶች ስንቅ የማድረስ ተልዕኮ ነበረው ። ስንቅ የጫኑ ብዙ የሲቪል ከባድ መኪናዎች ከጦሩ ጋር አብረው ተነቃ ነቁ ። ቀይ እምቡጥ ጦር የታጠቀው ቀላል መሣሪያዎች ብቻ ነበር ።



ጦሩ ከሠፈሩ የተነቃነቀው በጠንካራ ሞራልና በጋለ ስሜት ነበር ። ጦሩ በጥሩ ሞራል የተነቃነቀው ፣ ቀደም ሲል ወደ ሰሜን የተነቃነቁት 17ኛ እና አንበሳው 3ኛ ክፍለ ጦሮች የመጀመሪያ ምዕራፍ ግዳጃቸውን በተሳካ ሁኔታ ፈጽመዋል የሚል አስደሳች ዜና ስለደረሰ ነበር ። የቀይ ባሕርን ዳርቻዎች ይዞ ወደ አልጌና የሚገሠግሥ በመምሰል ወደ ሰሜን የሔደው የአንበሳው 3ኛ ክፍለ ጦር አንድ ክንፍ ድንገት ወደ ግራ በመታጠፍ ፣ ጠላት ባላሰበውና ባልጠበቀው መንገድ በሚያስደንቅ ፍጥነትና ቅልጥ ፍና ሮራ ጸሊም የተባለውን ቁልፍ የሆነ ወታደራዊ መሬት በቁ ጥጥሩ ሥር አዋለ ። የወገን ጦር አመጣጥ ድንገተኛ ስለሆነበት ግራ ጎኑ የተጋለጠው የጠላት ጦር የመከላከል ውጊያ ለማድረግ አልቻለም ። ሞኙ 3ኛ ክፍለ ጦር ወደ አልጌና በመጓዝ ላይ ነው የሚል ግምት በጠላት ዘንድ በማደሩ ፍጹም ተዘናግቶ ነበር ። የጠላት ወገን የሞተው ሞቶ ፣ የተማረከው ተማርኮ ፣ የተረ ፈው እግሬ አውጭኝ እያለ ፣ ትጥቁን ጥሎ ፣ ነፍሱን ይዞ ፈረ ጠጠ ። ከደረሰው ሪፖርት ለመረዳት እንደተቻለው 2000 የጠ ላት ሬሣ አስቆጥረው 77 ማርከው ከ317 በላይ ልዩ ልዩ መሣ ሪያዎችንና የመገናኛ ሬዲዮኖችን የተረከቡበት ውጊያ ነበር ። በእርግጥም ፣ ፍጹም የሆነ ታክቲካዊ ድል ነበር ።

እንዲሁም ከቀምጨዋ ተነስቶ በናሮ ሜዳና በቲክሲ ሸለቆ መሐል ለመሐል እየሰነጠቀ ወደ ሮሆረት የተሰበቀው 17ኛ ክፍለ ጦር ካንድ የድል ምዕራፍ ወደ ሌላ የድል እርከን በእስ ደናቂ ፍጥነት እየተሸጋገረ ሔዶ ፣ የጠላትን የግራ ሰበራ እየጠ በቀና ስርጦችን እየዘጋ የጊልሳን (ቲክሲን) ዝቅተኛ መሬት ግራና ቀኝ እና ከምዕራብ በኩል የሚገኙትን ከፍተኛ ወታደራዊ ግዢ መሬቶች ከቁጥጥሩ ሥር በማዋል የናቅፋን በር በማንኳኳት ላይ ይገኛል የሚል ዜና በደረሰ ጊዜ በቀይ እምቡጥ ጦር ላይ ያደረው ደስታ ከዳር እስከ ዳር አስተጋባ ። ጦሩ በሞራል እየተ ሰበቀ ወደፊት ይወረወር ጀመር ። ቃኝ ወይም አብሪ ኃይል ማስቀደም አልነበረበትም ። ዝም ብሎ ወደ ግቡ መምዘግዘግ ነበር ።

ቀይ እምቡጥ ጦር ፣ 17ኛ ክፍለ ጦር ሰባብሮና ጠርጎ ባለ ፉቸው የድል ጎዳናዎች ስለነበረ የሚጓዘው በመንገድ ላይ የጠላት እክል እንደማያጋጥመው አስቀድሞ አውቋል ። የ17ኛ

ክፍለ ጦር አንዱ ግዳጅ ለቀይ እምቡጥ ሻለቃ ጦር መንገድ እያጸዳ ሁኔታዎችን አመቻችቶ መቆየት ነበር ። ቀይ እምቡጥ ለልዩ ተልእኮ የተሰለፈ እንደመሆኑ መጠን ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 እየተዋጋ እንዲሄድ አስቀድሞውኑ አልተፈለገም ።

3ኛ እና 17ኛ ክፍለ ጦሮች ናቅፋ ለመግባት ከጊልሳ ሽዊ አልፎ የሚሔደውን የእግር መንገድና ወደ ናቅፋ አልጌና የሚያገናኘውን መንገድ መዝጋት ፣ እስካሁን የያዟቸውን ቁልፍ ቦታዎችና ግራና ቀኝ ክንፋቸውን ማጠናከር ነበረባቸው ። ነገር ግን ይህን ለማድረግ የመሬቱ ቅርጽና ስፋት አይፈቅድም ። በዚህ ላይ ጠላት መንገዱን ለመዝጋት ይሻማል ። ጠላት ተሻምቶ መንገድ እንዳይዘጋም ሆነ ፣ ወደ ናቅፋ የሚያረማምዱትን እንደ 1521 ፣ 1527 ፣ 1969 ያሉትን ከፍታ ነጥቦች ለመያዝ ፣ ለነዚህ ሁሉ ቁልፍ የሆነውን ከፍታ ነጥብ 1702 በቅድሚያ መስበር በጣም አስፈላጊ ሆኗል ። ጠላትም ይህንኑ ዐውቆ ይህን ገዢ መሬት ላለመልቀቅ «ነጥብ 1702 ወይም ሞት» በማለት መሽጎ ይጠብቃል ። እና የ3ኛና የ17ኛ ክፍለ ጦሮች ቀሪ ግብ በቀይ እምቡጥ ጦር ተልእኮ መሳካት ወይም አለመሳካት ላይ ያረፈ ነበር ። የተጣለበትን ኃላፊነትና አደራ የማያውቅ አንድም የቀይ እምቡጥ ጦር አባል አልነበረም......

«ይኮሩብናል»
«እናሳፍራቸውም»
«በኛ ሬሣ ክምር ላይ ወደ ናቅፋ ይረማመዳሉ ።»
«ነጥብ 1702 ላይ የቀይ ኮከብ ዘመቻችንን ቀይ ትርኢት እናሳያለን ። »
«እጅህን አትስጥ ። ልቡ ላይም መቆም ነው ። ማን ይፈራል ሞት ?»

«ታሪኩን የመሰለ ጀግና የጦር ገበሬ ፣ ይዘን የወንበዴዎች ጦር ፊታችን ማን አባቱ ሊቆም ! እንደታሪኩ ደረታችንን ገል ብጠን ነው የምንገባበት!» የሚሉ ኃይለ ቃላት በጦሩ ዘንድ በየቦታው ይነገሩ ነበር ።

አሸዋማው መሬት ብቻ ነበር አልፎ አልፎ የጦሩን ፈጣን ጉዞ የሚገታው ። ሁለት ከባድ የጭነት መኪናዎች አሸዋ ውስጥ



ገብተው ተቀረቀሩ ። የአየሩ ግለት እያየለ ሔዷል ። እንፋሎት የመተንፈስ ያህል ነበር ። የምንጓዘው ሸለቆዎችን ተከትለን ስለነበር ንፋስ ጨርሶ የሚነፍስ አይመስልም ። አፍን ያደርቃል ። አያስተነፍስም ። በማጅር ግንድ የሚንቆረቆረው ላብ እንደ ውሀ ይጨመቃል ። እያንዳንዱን ሰው ከወደ ጀርባው ሲመለከቱት ዝናብ የዘነበበት መስሎ ይታያል ። መኪናዎቹ ተገፍተውና ተጎትተው እስኪወጡ ድረስ ጦሩ ተገን ፣ ተገን ይዞ ቆመ ። ያለ ግራር ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ሌላ የሚታይ የዛፍ ዘር የለም ። አካባቢው ድንጋያማ ኮረብታዎች ይበዙበታል ። ጥቂት ወታደሮች አካባቢውን ለመቃኘት ሔደው ነበር ። ሌሎች ብዙ ወታደሮች አሸዋ ውስጥ ገብተው የተቀረቀሩትን መኪናዎች ይገፋሉ ፣ ይጎትታሉ ። ኰሎኔል ታሪኩም ከወታደሮቹ ጋር አብሮ ይሠራል ። ወታደሮቹን ፣ እሱ የማይሠራውን ነገር ፈጽሞ አያሠራቸውም ። የሚገርመው ነገር ላብ የሚባል ነገር አይታይበትም ። ድንገት ቅልጥ ያለ ተኩስ ይሰማ ጀመር ። ጦሩ በያለበት በደረቱ መሬት ያዘ ። የማደርገው ነገር ጠፍቶኝ ባለሁበት ተገትሬ ቀረሁ ።

ኰሎኔል ታሪኩ ፣ «መሬት ያዝ!» ብሎ ጮኸብኝ ። ሽጉጡን መዞ ቆሞ ነበር ። በደረቴ ለጥ አልኩ ። ትንሽ ቆይቶ ሁለት ቦምቦች ፈነዱ ። ሸለቆው አስተጋባ ። ምድርና ሰማይ የተደበላለቀ መሰለኝ ። ከዚያ በኋላ ጸጥ አለ ። ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ ። ቀደም ሲል አካባቢውን ለመቃኘት የሔዱት ወታደሮች በመተጋገዝ የቆሰሉ ሰዎች ተሸክመው መጡ ። ኋላ እንደተረዳሁት የቆሰሉት ሰዎች ተቆርጠው የቀሩ የጠላት ወገኖች ነበሩ ። ሦስቱ ቀደም ሲል ሞተዋል ። የተቀሩት ሁለት ሰዎች ክፉኛ ቆስለው ያጣጥራሉ ። ሳያቸው ዘገነነኝ ። ሰውነታቸው በቦምብ ተጨማልቋል ። ለመጀመሪያ ጊዜ የጦርነት አሰቃቂና አስቀያሚ ገጽታ ታየኝ ። ሆዴ ክፉኛ ታወከ ። ሰው እንዳያየኝ ዞር ብዬ መራራ ሐሞት እስኪያስመልሰኝ ድረስ አስታወክሁ ። ቀጥሎ የሆነው ነገር ነበር አደንዝዞ ያስቀረኝ ። ክፉኛ ቆስለው የሚያጣጥሩትን ሰዎች በመርዳት ረገድ ሊደረግ የሚችል አንዳችም ነገር አልነበረም ። ስቃያቸው የከፋ ቢሆንም ፣ ሞት አልገላገላችሁም ብሎ ይተናነቃቸዋል ። ኰሎኔል ታሪኩ ሽጉጡን መዞ በሁለት ጥይት ገላገላቸው ። የሰው አንጎል ወጥቶ ሳይ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር ። ፈዝዤ ቀረሁ...... ኰሎኔል ታሪኩ መጥቶ እስከሚያናግረኝ ድረስ

የት እንደ ነበርኩ ፣ በእውን ይሁን ወይም በቅዠት ዓለም ውስጥ እንዳለሁ አላውቅም ነበር ።

«እንዴት ነው'ኮ ታሪክ የምትቀርጹት?» ባለኝ ጊዜ ነበር ወደ እውነት ዓለም የተመለስኩት ። ከሰውነቴ ውስጥ ያለ የሌለ ፈሳሽ ነገር ተጨምቆ የወጣ ይመስል እያልበኝም ነበር ። ሙቀቱ ምኔም አልነበረም ። የምሰጠውም መልስ አልነበረኝም ። ቀጠለና ፣ «ገና የባሰ ታያለህ ። በጦር ሜዳ ሞት ምንም አይደለም ። እንደ መተንፈስ ወይም እንደ መብላት ተራ ነገር ነው ። የጦርነት መልክ አስቀያሚ ነው ። ቢሆንም ዳግመኛ እንደማታስታውክ ተስፋ አለኝ» ብሎ ሳቀብኝ ።

«እንደዚያ ማድረግ ነበረብህ?» አልኩት ።
«ምን?»
«ሰዎቹን ።»

ወታደሮች ሠፈ ጉድጓድ ቆፍረው ሬሣዎቹን አፈር ማልበስ ላይ ነበሩ ። ከመቸው ያንን የሚያክል ጉድጓድ እንደቆፈሩ ይገርማል ።

«መሞታቸው አይቀርም ነበር ። ከሚሰቃዩ ይሻላል ብዬ ነው ። ሌላም ምክንያት ነበረኝ» አለ ።
«እንደምን ያለ?»
«እንዳየሃቸው ሰውነታቸው ተቆራርጦ ነበር ። ጉዶሎ ሰውነት ይዞ ከመኖር መሞት ይሻላል ።»

«እውነት ይሆን ታስባለህ!»

«የለም ፣ እኔ ኢትዮጵያን ነው የማስበው ። አካለ ጎዶሎ የሆነች ኢትዮጵያን ማየት አልፈልግም» እንዳለኝ ፣ ረዳቱ መጥቶ ወታደራዊ ሠላምታ ከሰጠው በኋላ ፣ «የውሀ ሰዓት ደርሷል ጓድ ኰሎኔል» አለው ።

የኰሎኔል ታሪኩ ረዳት የመቶ አለቃ ጠና ጋሻ ይባላል ። በቅርብ ጊዜ ከተራ ወታደርነት ባንድ ጊዜ የመቶ አለቅና ማዕረግ የተሰጠው በዕድሜ ጠና ያለ ቆፍጣና ወታደር ነው ።



«እጅህን አትስጥ ። ጠላት ልብ ላይ ቁም ። ማን ይፈራል ሞት» የሚል ኃይል ቃል ከአፉ አይለይም ። በጀግንነቱ ብዙ የጦር ሜዳ ሜዳዮች የተሸለመ ወታደር ነው ። አብዛኛዎቹ የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች እንደ እሱ በልዩ ልዩ ጦር ሜዳዎች ባሳዩት ጀግንነትና በሠሩት ጀብዱ ልዩ ልዩ ሽልማት ያገኙ ምርጥ ወታደሮች ናቸው ። ፊሽካ ተነፋ ፤

«ለንቅናቄ ተዘጋጁ !»
ሁሉም ባንድ ጊዜ ተዘጋጀ ።
«ኮዳ አውጣ!»
ሁሉም ኮዳውን አውጥቶ በእጁ ይዞ ቆመ ።
«ኮዳ ወደ አፍ!»
ሁሉም ኮዳውን ወደ አፍ ይዞ ይጠብቅ ጀመር ።
«ጠጣ!»
ወታደሩ ሁሉ ውሀውን ይጠጣ ጀመር ።
«ኮዳህን መልስ!»
ሁሉም ኮዳውን መልሶ ከጐኑ ላይ ሻጠ ።
«ወደፊት!»

ኰሎኔል ታሪኩ ወደ መኪናው ከመሔዱ በፊት ፣
«እናንተ ጋዜጠኞች ውሀ በፈለጋችሁ ጊዜ ልትጠጡ ትችላላችሁ» አለኝ ።

ኮዳዬን አውጥቼ ውሀ ጠጣሁ ። ሙቅ ነበር ። ቀዝቃዛ ውሀ በዓይኔ ዞረ ። አንድ ጠርሙስ ቀዝቃዛ ውሀ ባገኝ የተጠየቁትን ዋጋ እከፍል ነበር ። በ1700 ሰዓት ሠፈር ተመርጦ አዳር እዚያው እንዲሆን ተደረገ ። 17ኛ ክፍለ ጦር የሠፈረበት ቦታ ነበር ። ትልቁ ግራር ላይ «አምባሦይራ» የሚል ጽሑፍ ተለጥፎበታል ። መለስ ካለው ግራር ላይ ደግሞ «ኒያላ» የሚል ጽሑፍ ይታያል ። የበረሀ ሐረጎችን በማያያዝ የተሠሩት ዳስ መሳይ ነገሮች ላይ ፣ «አምባሳደር ፣» «ቻው ፣» «ከረን» የሚሉ የሆቴል ስሞች ተጽፈው ይነበባሉ ። መቸም የሰው ልጅ ገሀነብ ውስጥ ቢወድቅም ገነት መመኘቱ አይቀርምና ፣ ነገሩ ያሳቀኝን ያህል አሳዛነኝ ። ሠፈሩ ባንድ ጊዜ በወታደራዊ እንቅስቃሴ ተሞላ ። ዘቦች ቦታ ቦታቸውን ያዙ ። ሹካ እና ማንኪያ የሚል የመተላለፊያ ኮድ ተሰጠ ። ውሀ አቀዝቅዞ ለመጠጣት የሚደረገው ሩጫና

ጥረት የሚያስደንቅ ነበር ። አንዳንዱ ኮዳውን በእርጥብ ጆንያ
አስሮ ከዛፍ ላይ ይሰቅላል ፣ ሌላው ኮዳውን ወስዶ ከደረቅ ወንዝ
ዳር አሸዋ ውስጥ ይቀብራል ። የመቶ አለቃ ጋሻ ጠና የኔን ኮዳ
ወስዶ የት እንደሔደ አላውቅም ። ጋዜጠኞች እንደ እንቁላል
የሚሰበሩ ይመስል የጦሩ አባሎች በሙሉ ሊንከባከቡን ይጥሩ
ነበር ። አንዳንዶቹ ከንፈራቸውን በኃዘን እየመጠጡ ያዝኑልናል።
አሁን እንዲያው እዚህ ምን አመጣችሁ? የሚሉ ይመስላሉ ።

ጸሐይ ከመጥለቋ በፊት የረሻይዳ ብሔረሰብ አባሎች ከየት
መጡ ሳይባል ፣ ተሰባስበው በመምጣት ከጦሩ ሠፈር ትንሽ
ራቅ ብላ በምትገኝ ገላጣ ሥፍራ ላይ ተከማችተው ይታዩ ነበር ።
ከእግር ጥፍራቸው እስከ ራስ ጠጉራቸው በጥቁር ጨርቅ
የተሸፈኑ ሴቶች ከወንዶች ኋላ ተቀምጠዋል ። ፊታቸው አይታ
ይም ። አንድ የራሻይዳ ሴት በአሥር ወይም በአሥራ ሁለት
ዓመቷ ከተዳረች በኋላ ከባሏ ሌላ ማንም ወንድ ፊቷን ሳያይ
ኖራ ትሞታለች ሲባል ሰምቻለሁ ። ምግብ ስትበላም ሆነ ውሀ
ስትጠጣ ተሸፍና ስለሆነ ባሏም ቢሆን ከንፈሯን አያይም ይባ
ላል ። ምን ይመስሉ ይሆን? ያንዷን ፊት ገልጬ ባየሁት የሚል
ስሜት ቢያድርብኝም ፣ የራሻይዳ ባል የሚስቱን ፊት ገልጦ
ያየበትን ወንድ እጅ በያዘው ሠይፍ ቆርጦ ሳይጥል አይመለስም
የሚል ታሪክ ስላለ ፣ አንዱ የእጄን ዋጋ ቢሰጠኝስ በማለት
ስሜቴን ገትቼ ዝም አልኩ ። የቴሌቪዥን ፊልም አንሺያችን
ያንድን ሴት ፊት ገልጦ ለማንሳት ሲሞክር አይቼ ሩጬ ሔጄ
ያዝኩት ። አንዱ የራሻይዳ ጎረምሳ ሠይፉን ለመምዘዝ ይዳዳው
ነበር ፣ ወይም መሰለኝ ። ፊልም አንሺያችንን ፣ አሸብር ዳርጌን
ታሪኩን ሳጫውተው ደንግጦ የያዘውን የፊልም ማንሻ መሣሪያ
ጥሎ ሊሮጥ ምንም አልቀረውም ።

ወደ ጦሩ ፖለቲካ ኮሚሳር ጠጋ ብዬ ፣ «እነዚህ ሰዎች ምን
ሊፈልጉ ነው የመጡት?» ብዬ ጠየኩት የጦሩ ፖለቲካ ኮሚ
ሳር ሻምበል ዋለልኝ ይርጋ ይባላል ።

«የወባ መድኃኒት» አለኝ ።
«ምነው ሁሉም ታመዋል?»
«የለም ፣ አብዛኛዎቹ ከኪኒኑ ጋር ለሚሰጠው ውሀ ሲሉ
ነው የሚመጡት» በማለት መለሰልኝ ።



ውሀ ማግኘት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ለመጀመሪያ
ጊዜ ጭንቅላቴን መታኝ ። የሰው ልጅ በእንደዚህ ያለ የተረገመ
ምድር መኖርን የሚመርጥበት ምድራዊ ምክንያት አልታይህ
አለኝ ። ነገሩ ገረመኝ ። መጀመሪያውኑ የሰው ልጅ የሚኖርበት
አካባቢ አልመሰለኝም ነበር ። የትና? እንዴት? እንደሚኖሩ የሣ
ሕል በረሀ እግዜር ብቻ ነበር የሚያውቀው ። በሌላ በኩል በአ
ብዮታዊው ጦር ላይ ያላቸው እምነት ያስደንቀኝ ነበር ። ደረቅ
ስንቅ፣ ውሀና የወባ መከላከያ ክኒን ከታደላቸው በኋላ ሻምበል
ዋለልኝ ሴቶቹ ወደፊት እንዲመጡ ጋበዛቸው ። ፊት የተቀመ
ጡት ወንዶች በመጀመሪያ ነገሩን እንደ ቀልድ በማየት እየተጠ
ቃቀሱ ይስቁ ጀመር ። ሻምበል ዋለልኝ አምርሮ ሴቶቹ በግድ
ወደፊት እንዲመጡ ለማድረግ ሲል ፣ ወንዶቹም አምርረው
ተነሱ ። በራሻይዶች ልማድ ሴት ልጅ በምንም ሁኔታ ከወንድ
ቀድማ አትሄድም ፣ ከወንድ ፊት አትቀመጥም ። ያልታሰበ
ውጥረት ድንገት ተፈጠረ ። ኰሎኔል ታሪኩ መጥቶ ሁኔታውን
ከተረዳ በኋላ ፣ ሻምበል ዋለልኝን «ተዋቸው ። እንደልማዳቸው
ይሁኑ ። ችግር መፍጠር የለብንም» አለው ።

ሻምበል ዋለልኝ ፣ «እንዲህ ዓይነቱን ጎታች ባሕል እያየን
ዝም ማለት የለብንም ። እነዚህ ሴቶች ዘላለማቸውን የወንዶች
ተገዢዎችና ባሪያ ሆነው እስከ መቼ ይኖራሉ? ማንቃት አለብን ።
የጦሩ አንዱ ተልእኮ ማንቃትና ማደራጀት ነው» በማለት
ለመከራከር ሞክሮ ነበር ።

«አዎ ፣ ጓድ» አለ ኰሎኔል ታሪኩ በርጋታ ፣ «ልክ ነህ ።
ግን እንዲህ ዓይነቱ ነገር ጊዜ ይወስዳል ። ንቃት ሲባል ከሕ
ዝቡ ንቃተ ሕሊና ውጭ ወይም በላይ ሊሆን አይችልም ። ነጥ
ቡን ይለቃል ። ጓድ ፣ ንቃት ጊዜ ይወስዳል...... ጊዜን ይጠይ
ቃል ፣ በግድ የሚሆን ነገር አይደለም ። እነሱን ለማንቃት እነ
ሱን መምሰል አለብን ።»

❦

ለራት ጋሌጣና የቆርቆሮ ምግብ ተሰጠን ። ከቆርቆሮ ም
ግብ ውስጥ ሽሮ፣ ዝግኒ ወይም አትክልት መርጦ መብላት ይቻ
ላል ። ከሁሉም አንጀት ገብቶ የሚፈውሰው ግን «ሚሊ ድራፍት»
ነበር ። የበሶ ብጥብጥ ነው ። በስኳር ተበጥብጦ ካደረ ትንሽ
ስለሚፈላ ትንሽ ሞቅ ያደርጋል ። ለራብ! ለውሀ ጥም! ለመጠጥ!

ምን ጊዜም «ሚሊ.ድራፍት!» ይላል የጦር ሜዳው ማስታወቂያ ። ሁሉም በስኳርና በውሀ በጥብጦ ያቀዘቀዘውን ሚሊ. ድራፍት ሊጋብዘን ይሯሯጥ ነበር ። «ከንቲባ» ከእምባሦይራ ኒያላ ፤ ከኒያላ ከረን እያለ የቀዘቀዘ ሚሊ. ድራፍት በጋቤጣ መለጋት ጀምሮ አል ። «ከንቲባ በሞቴ!» የማይለው ወታደር አልነበረም ። በጊዜ ተኛን ። ልብስ ፤ ጫማ ማውለቅ የለም ። ከነጫማህ ትውላለህ ፤ ታድራለህ ፤ ትሞታለህ ። እባብና ጊንጥ ያስፈራል ። ሲቀፈኝ ሔጄ አሸዋ ውስጥ ተኛሁ ። ሁሉም እንደኔ በጀርባው ተኝቶ ኮከብ ይቆጥር ነበር ። የጠራው ሰማይ ቀረብ ያለ መስሎ ይታያል ። ቢደከመኝም እንቅልፍ እምቢ አለኝ ። ያሳለፍኩት ማዕከላዊ ሕይወት ባሳቤ መጣ ። ከሁሉም ትዝ ያለኝ በወሀኒ ቤት ሲሚንቶ ላይ እየተኛሁ ያሳለፍኩት ያንድ ዓመት ጊዜ ነበር ። አሁን ሳስበው እንድ ዓመት ብቻ ሆኖ አይታየኝም ። አሥር ዓመት ሆኖ ይሰማኛል ። ቀኖቹም ረጂም ነበሩ ። ምግቡና መኝታው በጣም መጥፎ ነበር ። እና የታሰርኩት ደግሞ ከተራ ሌቦችና ማጅራት መቺዎች ጋር ነበር ። ለእነሱ እሥር ቤቱ እንደቤታቸው ነበር ። ፍርዳቸውን ጨርሰው የተለቀቁ እለት እንዴት እንደሚሰርቁና ማጅራት እንደሚመቱ ከማሰብ ሌላ አሳብ አልነበራቸውም ። እኔም በሌብነት ነበር የታሠርኩት ፤ በፍቅር ሌብነት ። በጣም የምወዳት አንድ ልጅ ነበረች ። ሂሩት አጎናፍር ትባላለች ። የ17 ዓመት ልጃገረድ ነበረች ። እኔም የሐያ ዓመት ጎረምሳ ነበርኩ ። ተዋደድን ። ይዣት ኮበለልኩ ። ገንዘብ አልነበረኝም ። አብዛኛውን ጊዜ ምግባችን ፍቅር ነበር ። የአሥራ ሁለተኛ መልቀቂያ ፈተና ለመውሰድ ስዘጋጅ ነበር ይዣት የኮበለልኩት ። እሷ የአሥረኛ ክፍል ተማሪ ነበረች። ከአንድ ወር በኋላ ታድነን ተያዝን ። ቤተሰቦቿ ከመኳንንት ዘር ነበሩ ። በተለይም እናቷ ከእቴጌ ጋር የቅርብ የሥጋ ዝምድና አላቸው ይባል ነበር ። ልጅቷ በዘመድ ዛቻና በእባቷ ዱላ ብዛት ፤ ፍርድ ቤት ቀርባ ፤ ያለውዴታዋ በግድ ያስኮበለልኳት መሆኔን በመሐላ መሰከረች ። ለመከራከር አልቻልኩም ። ጠጉሬን ተላጭቼ ወህኒ ቤት ወረድኩ ። ለፍቅር የተከፈለ ክቡር ዋጋ ነበር ። ገና ወደፊት ፍቅር የሚጠይቀኝ የበለጠ ዋጋ ይኖር ይሆን? ብዬ አሰብኩ ። በሮማን ኀለተ.ወርቅ ቆርጬ ነበር ። እሁን ግን እርግጠኛ አይደለሁም ። ፈያሜታ ጊላይ ከቀይ ኮከብ ዘመቻ ጋር ድንገት ልቤ ውስጥ ገብታለች ። ከሮሜ ጋር ላወዳድራት አልፈለኩም



ግን ብልህነቷ ፤ ንጽሕናዋ ፤ ቀልድና ለሕይወት ያላት ፍቅር ለጊዜው አመዘነብኝ ። ምናልባት የቅርብ ጉዳይ ይሆናል ። አላውቅም ። ጠፍቻለሁ ። ምናልባት እንደ እድል ሆኖ በዚህ ጦር ሜዳ ራሴን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አውቀው ወይም አገኘው ይሆናል ፤ ወይም ለዘላለም እንደጠፋሁ እቀር ይሆናል ......

በሕይወት ከለውጥ በቀር ምን ቋሚ ነገር አለ?...... ምን አሰጋህ? ብዬ ፤ አሸዋ ውስጥ ተገላበጥኩ ። ምንም የሚያሰጋ ነገር በዚህ ዓለም የለም ፤ ትኖራለህ ወይም ትሞታለህ ። ስጋቱ ምንድነው? ሕይወት እንዳመጣጡ ከያዙት የሚያሰጋ ነገር የለም......

«እንቅልፍ እምቢ አለህ እንዴ?» አለኝ የመቶ አለቃ ጋሻጠና ። አጠገቤ ተኝቶ ነበር ።

«ያለ ጣራ አይሆንልኝም መሰለኝ?»

«የኛ ጣራ ሰማይ ፤ መኝታችን ዐፈር ነው ። የትም እንቅልፍ ይወስደናል» አለኝ ።

«ልምድ ይጠይቃል» አልኩት ።

«ምነው አይለመድ? ይኸውና ከሰማይ በቀር ጣራ ሳላይ ስምንት ዓመት ሊሆነኝ ነው ። ባለፉት ስምንት ዓመታት ጣራዬ የኦጋዴንና የባሌ ሰማዮች ነበሩ አሁን ደግሞ የኤርትራ ሰማይ ። እጅ አለመስጠት ነው ። ልቡ ላይ መቆም ። ማን ይፈራል ሞት!» አለ ።

«በውትድርና ነዋ የኖርከው?»

«ዕድሜዬን ሙሉ ። ሌላ ሥራ አላውቅም ። እንዋጋለን ፤ እንገድላለን እንሞታለን ። የቁማር ኑሮ ነው የምንኖረው ። እጅ አለመስጠት ነው!» ካለ በኋላ በውትድርና ስላሳለፈው ሕይወት አንስቶ ያጫውተኝ ጀመር ።

በሐያ ዓመቱ ነበር ወታደር የሆነው ። በትምህርቱ ጎበዝ ነበር ። ወታደር ለመሆን የመረጠበትን ምክንያት አያውቅም ። ምናልባት ዩኒፎርሙ ይሆናል የሳበው ። እግረኛ ወታደር መሆን የመረጠበትንም ምክንያት አያውቅም ። የአየር ኃይል ወይም

የባሕር ኃይል ፣ ወይም የታንከኛ ወይም የመድፈኛ ብርጌድ
አባል ለመሆን ይችል ነበር ። ባይሆን ከጣራ ሥር የሚተኛበት
አልጋ ይኖረው ነበር ። የእግረኛ ወታደር ሕይወት የእህያ ሕይ
ወት ነው ይባል ። ግን ከእግረኛ ወታደር ሕይወት ተለይቶ መኖር
አይፈልግም ። የእግረኛ ወታደር ሕይወት ትምህርት ቤቱም ሕይ
ወቱም ሆኖ ቆይቷል ። የእግረኛ ወታደር ሕይወት የእህያ ሕይ
ወት ነው ያለበትን ምክንያት አስረዳኝ ።

አንድ ወታደራዊ መሬት ያለ እግረኛ ወታደር ተጋድሎ
አይያዝም ። ከአየርና ከየብስ ምን በአይሮፕላንና በመድፍ ቢደ
በደብ ያለ እግረኛ ወታደር የሞት ሽረት ትግል ፣ ሩጫ ፣ ላብና
ደም ፣ ስቃይና ሞት አይሆንም ። በመጨረሻ የሚዋጉት ሰዎች
ናቸው ። ጦርነትን የሚዋጉት አውሬዎች ወይም አማልክት አይ
ደሉም ። ሰዎች ናቸው ። እግረኛ ወታደሮች ናቸው ። እንደ
ማንኛውም ሰው ለመኖር ፣ ለማግባት ፣ ለመሳቅና ለመጫወት
የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው ። እግረኛ ወታደር ነው በመጨረሻ
ሳንጃውን ወድሮ ጠላትን የሚያጠቃው ፣ ለሞት ወይም ለመግ
ደል የሚሮጠው ፣ ወደ ጠላት ወረዳ በደረቱ እየተሳበ የሚሔ
ደው ፣ ላቡን የሚያንቆረቁረው ደሙን የሚያፈሰው ። ታሪክ
ያስታውሰው ይሆን? የለም ። አዎ ፣ ታሪክ ይጻፋል ። ግን የሚ
ጻፈው ታሪክ ምናልባት የሚያስታውሰው ነገር ቢኖር የጊዜውን
ታክቲክና ስትራተጂ ፣ ከዚያም ግፋ ቢል የአዛዥ መኰንኑን
ትርታ ይሆናል ። ታሪክ ጨካኝ ነው ። የመቶ አለቃ ጋሻ ጠና
ማን ነበር?የታሪክ ነገር ጉዳዩም አይደለም።ስም ነበር — በቃ ።
በጦር ሜዳ ምንም ነገር እውን መስሎ አይታይም ። እውን
ሆኖ የሚታየው ቁጥር ብቻ ነው ። ይህን ያህል ሰው ሞተ ፣
ቆሰለ ፣ ተማረከ ፣ ጠፋ — በቃ ። የተያዘውን ወረዳ ማጠናከር ፣
በተረፈው ቁጥር ላይ ተመስርቶ ለነገ ውጊያ አቅድ ማውጣት —
ማጥቃት — ማፈግፈግ ። «ይኸው ነው የእግረኛ ወታደር
ሕይወት» አለኝ በመጨረሻ ። በፈቃዱ ራሱን ለቀይ እምቡጥ
ጦር ተልእኮ ለምን እንዳዘጋጀ ሊያስረዳኝ አልቻለም ። ለታሪክ
ብሎ አልነበረም ። አሁን ጋሻ ጠናን ማን ያስታውሳል? የሚል
ነበር መልሱ ። ወይም ሹመትና ሽልማት ፈልጎ አልነበረም ።
ጋሻ ጠና የእለት ጉርሱንና የዓመት ልብሱን ካገኘና ጤና ከሆነ
ስለኑሮ የሚያስብና የሚጨነቅ ሰው አይደለም ። ሞትን ፈልጎ
አልነበረም ። እንደማንኛውም ሰው ሕይወቱን ፣ ሕይወትን ይወ



ዳል ። ወይም ሳገሩ ክብርና ለአብዮቱ መሳካት ከሌሎች ይበልጥ
ተቆርቋሪና አሳቢ ሆኖ አልነበረም ። «እንጃ ፣ ብቻ ጥቂቶቻችን
ራሳችንን አሳልፈን ለመስጠት ካልተዘጋጀን ሌላው እንዴት
ሊኖር ይችላል ?» የሚል አሳብ ወይም እምነት ነበረው ። አባ
ባሉ ትርጉም ሰጠኝ ። ሕይወትን መውደድ ብቻውን አይበ
ቃም ፣ ሌሎችም እንዲወዱት ማስተማር ያስፈልጋል ፣ አዎ ፣
ክርስቶስ ለሰው ልጆች ፍቅርን ያስተማረው በምን ነበር? ራሱን
አሳልፎ በመስጠት ተግባር ነበር...... ውይይታችን ሔዶ ፣ ሔዶ
ወደ ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም አመራ ።

«አጋዴን አብረን ነበር ፣ ካብዮቱ በፊት» አለኝ ።
«እውነት?» አልኩት ።

«ያኔም እንዳሁኑ ጀግና ነበሩ ። ጀግና ሰው ደስ ይለኛል»
አለ ።

«በቅርብ ታውቃቸው ነበር?» ብዬ ስጠይቀው ፣ ስለሊቀ
መንበሩ የሚከተለውን ታሪክ አጫወተኝ ።

«መሐንዲስ የሆነ አንድ ወጣት መኰንን ነበር ። ሰጠሩ
ጥቂት ቤቶች እንዲሠራ ይታዘዛል ። የተፈቀደለትን በጀት
ቆጥቦ የተፈለጉትን ቤቶች ከታሰበው በላይ በጥሩ ሁኔታ ከሠራ
በኋላ ፣ ቆጥቦ ባተረፈው ገንዘብ ለጦሩ ማለፊያ የመዝናኛ ሥፍ
ራዎች ይሠራል ። ጦሩ በሙሉ በሥራው ተደሰተ ። በመጨረሻ
ከፍተኛ መኰንኖች ያሉበት የቁጥጥር ኮሚቴ መጣ ። የቁጥጥር
ቡድኑ የሚመራው በአንድ ጄኔራል ነበር ። ሥራው ተጎብኝቶ
ገለጻ ከተደረገ በኋላ ጄኔራሉ ምሥጋና ያቀርባሉ ተብለው ሲጠ
በቁ ፣ ያልታዘዝከውን ማን ሥራ አለህ? በማለት በወጣቱ የጦር
መሐንዲስ ላይ የተግሳጽ ናዳ ያወርዱ ጀመር ። የጄኔራሉን ፊት
ያዩ ሌሎች መኰንኖችም ፣ በወታደራዊ ደንብ ያልታዘዙትን
መሥራት አግባብ አይደለም ሲሉ ተቹ ። ወጣቱ መሐንዲስ
እንባው መጣ ። በመጨረሻ የተናገሩት ጓድ ሊቀ መንበር ፣ የያ
ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ነበሩ ። «የተረፈው ገንዘብ
ለተባለው ሥራ ወጥቷል ተብሎ ቢበላ ኖሮ ፣ በተጨማሪ ምን
ተሠራ? ለምን ተሠራ? የሚለው ጥያቄ አሁን አጠያያቂ አይሆ
ንም ነበር ፣ ቅን ሥራ የሚያስወቅስ ከሆነ ያሳዝናል!» ማለት
የጄኔራሉን ቀንድ እንዴት እንደሰበሩና ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የአን

በሳው የመጫሪያ ግምጃ ቤት መኰንን ሆነው በሚሠሩበት
ወቅት ፣ አንድ ሌላ ጀኔራል ፣ አንድ ቀን የመኪና መለዋወጫ
ዕቃ ባስቸኳይ ላክ ብሉ ሲልከባቸው ለግል አውቶሞቢል ቀርቶ
ለጦሩም የሚሆን መለዋወጫ ዕቃ የለም ብለው ስለሰጡት
መልስ ካጫወተኝ በኋላ ቀጥሎም ፣ «መቸ ይህ ብቻ አንድ ቀን
ደግሞ እንዲህ ሆነልህ ። ንጉሡ ለጉብኝት ይመጣሉ ። ተመል
ደግሞ እንዲህ ሆነልህ ። ንጉሡ ለጉብኝት ይመጣሉ ። ተመል
ካች አጥተው የወደቁ መጫሪያዎችና ተሽከርካሪዎችን ትተው
ደህና ደህናውን ነገር ብቻ እንዲሳበኙ ከበላይ ትእዛዝ ይሰጣል ።
የሚያስቆጭና የሚያናድድ ትእዛዝ ነበር ። እንዲያስጎበኙ የታዘ
ዘ ቅም እሳቸው ነበሩ ። እንደታዘዙት ደህና ደህናውን ነገር
ያስጎበኙና በመጨረሻ እንዲደበቁ የተደረገ ትንም ጭምር ንጉ
ሡን ወስደው ያሳያሉ ። ንጉሡ በመቆጣት ካባቸውን አጥፈው
ይሔዳሉ ። በዚህ ምክንያት ፣ በአለቆቻቸው ዘንድ ፣ አደገኛ
መኰንን ነው እየተባሉ ሲጋዙና የማዕረግ እድገት ሲታለፉ ነው
የቆዩት ። አይ ወንድ! አይ ጀግና! ከዚህ ጀግና ሰው ጋር ቁሞ
መዋጋትና መውደቅ በእውነት ክብር ነው» በማለት ስለሰው
ዬው የሚያውቀውን ያህል ነገረኝ ።

እንደምንም እንቅልፍ አሸለበኝ ። ዓይኔን ስከፍት ከንጋቱ
አሥራ አንድ ሰዓት ሆኖ ነበር ። የመቶ አለቃ ጋሻ ጠና ባይቀሰ
ቅሰኝ ኖሮ በጦር ሜዳም የጧት እንቅልፍ አሸንፎኝ እዚያው
እቀር ነበር ። ጦሩ ለመንቀሳቀስ ተዘጋጅቷል ። ፍሬው ዘሪሁን
መጥቶ «ማታ ጉድ ልንሆንልህ ነበር» አለኝ ፡

«ምን ሆናችሁ?»

«እኔና አሸብር ማታ ሜዳ ወጥተን ስንመለስ ዘቡ ፣ «ቁም!
አንተ ማነህ?» ሲሉ ጉድ ፈላልህ ሁለታችንም ደንግጠን ነው
መሰለኝ ፣ የይለፍ ቃሉ ተረሳን ። አሸብር አስታውሶ ፣ «እረ በፈ
ጠረህ! «ሹኮች ነን!» ባይለው ኖሮ ይጨርሰን ነበር» አለኝ ።

ሳቅሁና «ከንቲባ ነኝ አትለውም ኖሮአል?» አልኩት ።

ነገሩ በጦሩ ዘንድ ተለምቶ ኖሮ ፣ ጋዜጠኞች መባላችን
ቀርቶ ፣ «ሹኮች» እየተባልን መሳቂያ ሆነን ነበር ። ኰሎኔል
ታሪኩ ነበር መጥቶ በመጀመሪያ ፣ «ሹኮች» እንደምን አደራችሁ?
ያለን ።



«ጦር ሜዳ ይስማማሀል ልበል?» አልኩት ።
«እንዴት?» አለኝ ።
«ደልቶህ ያደርክ ትመስላለህ»

ፊቱ ያበራ ነበር ። ሰብእናውም ተለውጧል።ጥሩ ፈገግታ
ከፊቱ ላይ ይታያል ። ካላሽን የጨበጠው እጁ ሥራ ይዟል ።
ርምጃውም ቅልጥፍና የተሞላበት ነበር ።

«ወታደር ነፍስ የሚዘራው ሥራው ላይ ነው» አለኝ ።
«ሹኮችም ከእንግዲህ ነፍስ ይዘራሉ ። ታያለህ» አልኩት ።

ምን ምን እንደምሸትና ምን እንደምመስል ካሁኑ ጠፍ
ቶኛል ። ምን ምን እንደምሸት አላውቅም ። ምቾትና ሕልውና
ትርጉም አልነበራቸውም ። እውን ሆኖ የሚታየኝ ነገር ቢኖር
ከፍታ ነጥብ 1702 ብቻ ነበር ። እና እያንዳንዱ ሰው ወደ መጨ
ረሻ ግቡ ፣ ወደ ተወሰነለት ጥሪ ፣ ይፈጥን ነበር ። በፍጥነት ነበር
የምንጓዘው እንዴ ብቻ ነበር ለውሀ የቆምነው ። የሞቀ ውሀ እየተ
ስማማኝ ሔዷል ። ወታደሩ በዚህ በረሀ ከቀዝቃዛ ይልቅ ትንሽ
ሞቅ ያለ ውሀ ነው ጥም የሚቆርጠው ሲለኝ ይገርመኝ ነበር ።
ነገሩ እውነት ሆኖ አግኝቼዋለሁ ። ጸሐይ ከመጥለቋ በፊት እንደ
ገሠገሥን ሔደን ፣ የ17ኛ ክፍለ ጦር መሰብሰቢያ ወረዳ ከሆ
ነው ከከፍታ ነጥብ 492 ደረስን ። የ17ኛ ክፍለ ጦር አባሎች
በሆታና በጭብጨባ ደማቅ የሆነ አቀባበል አደረጉልን ። እጅግ
የሚያስደስት አቀባበል ነበር ። የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች
ራሳቸውን ለውጊያ ከማዘጋጀት በቀር በሠፈሩ ሌላ ግዳጅ አል
ነበራቸውም ። እንዲያውም የ17ኛ ክፍለ ጦር አባሎች አስተና
ጋጅ በመሆን ምግብ ፣ ውሀ ከማቅረብም ሌላ ልብሶቻቸውን
ወስደው ያጥቡላቸው ነበር ። የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች ሰውነ
ታቸውን እንዳ የጸዱ ታዘዙ ። ካሜራችን ተከተላቸው ። ገላቸውን
ሲታጠቡ አፋፍ ላይ ቆሜ እመለከታቸው ነበር ። ራሳቸውን
ለሞት የሚያጠምቁ መ( ለው ታዩኝ ። ለዚህ አደገኛ ተልእኮ እያ
ንዳንዳቸውን ያነሳሳው ነገር ምን እንደሆነ አላውቅም ። እያንዳ
ንዳቸው ለዚች አገርና ለዚህ አብዮት ከሌሎች ይበልጥ ተቆርቋሪ
ሆነው አይደለም ፣ ወይም አይመስለኝም ። ግን አንድ ነገር ይሰማ
ኝ ነበር ። በውስጣቸው የሕይወት እሳት የሚነድ ነጻ ሰዎች ነ

በሩ ። ነጻ ሰው ውብ ነው ፣ ቆንጆ ነው ። እና ሁሉም ውቦች ፣ ቆንጆዎች ነበሩ ። ልቤ በጣም አዘነ ። ጀምበሯ ከናቅፋ ተራሮች በስተጀርባ ልትጠልቅ አሽቆልቁላለች። ሰማዩ እንደ ደም ቀልቶ ይታይ ነበር ። ቀጥሎ የሆነው ነገር ነው በይበልጥ ልቤን የነካው ።

የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች ለዘመዶቻቸው ወይም ለተወካዮቻቸው ፣ ወይም ለሚመለከተው ሰው የሚያስተላልፉት መልእክት ካላቸው እንዲጽፉ ተጠይቀው ነበር ። ምን መልእክት እንደሚተው ለማወቅ ፍላጎት ስላደረብኝ አንዳንዶቹ የጻፉትን እንዲያሳዩኝ ጠይቄአቸው ነበር...... «ምናልባት አደጋ ደርሶብኝ የሞትኩ እንደሆነ ያለኝ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ለቀይ ኮከብ ዘመቻ እንዲሰጥልኝ እጠይቃለሁ» የሚሉ መልእክቶች ብዙ ነበሩ ። እሳልፈው የሚሰጡት ውድ ሕይወታቸው አልበቃ ብሎአቸው ይሆን? በማለት ተገረምኩ ። ለሚ(ት ፣ ለልጅ ፣ ለወንድም ፣ ይሆን? በማለት ተገረምኩ ። ለሚስት ፣ ለልጅ ፣ ለወንድም ፣ ለእህት ፣ ለአባት ወይም ለዘመድ የተጻፉ ደብዳቤዎች ጥቂት አልነበሩም ። አንዳንዶቹ ፣ ስለጉዞአቸውና አሁን ስለሚጠብቃቸው ተልእኮ ነበር የጻፉት ። እና አብዛኞዎቹ ደብዳቤዎች ፣ «ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ሌላ ጊዜ እጽፋለሁ ። ስለኔ አታስቡ ። ደህና ነኝ ። ለምንድነው የማትጽፉልኝ? እኔ ካንቺ...... ወይም ካንተ ናፍቆት በስተቀር ሌላ አሳብ የለኝም......» በሚሉ ዐረፍተ ነገሮች የተደመደሙ ነበሩ ። ከዚህም ባሻገር ፣ «ናቅፋ ደርሰናል ። እንደ አያያዛችን ከሆነ ይህ ጦርነት ጊዜ የሚፈጅ አይመስልም ። በቅርብ ቀን እመጣለሁ ። እስከዚያ ድረስ ገንዘብ ካለ ላኪ (ወይም ላክ) ። ራዲዮና ቴፕሪኮርደር አልጌናና አፍአበት በርካሽ ዋጋ ይገኛል ።» ካሉ በኋላ ፣ ሲመለሱ ምን ለማድረግ እንዳሰቡ በዝርዝር የጻፉ ሰዎችም ነበሩ ። አንዱ ባጠራቀመው ገንዘብ ያቺኑ ማሳ እንዴት እንደሚያለማና ያቺን ጎጆ እንዴት እንደሚያቃና ይጽፋል ። ሌላው በችግር ምክንያት ያቋረጠውን ትምህርት እንዴት አድርጎ እንደሚቀጥልና እምን ደረጃ ድረስ ለመማር እንደሚፈልግ ያትታል ። ከጦር ሜዳ እያሌ ጠቃሚ ትምህርት አግኝቻለሁ ።

ተለውጫለሁ ፣ ከእንግዲህ እንዳለፈው ጊዜ ተመልሼ የምቀብጥ አይመስለኝም ። መጠጥ የሚባል ነገር ትቻለሁ ። እንደ



ድሮው በትንሹም በትልቁም ነገር አልናደድም።ጦር ሜዳ ያስክናል ። ውዴ ሙች ፣ ቅናትም ትቻለሁ ። አሁን የምቀናው በሕይወት ብቻ ነው ። አሁን የምመኘው ነገር ቢኖር ደስታና ተድላ የሰፈነበት ፣ የሰከነና የቀዘቀዘ ኑሮ መኖር ብቻ ነው ። ወደፊት የምንኖረው ኑሮ ይታየኛል ፣ ልጄን ሳሚልኝ ። ስመለስ የበደልኳችሁን በደል ሁሉ ድርብ አድርጌ እክሳለሁ በማለት የፉጻ ሌሎችም ነበሩ ። አዎ ፣ በሰው ልብ ተስፋ ምንጊዜም አይሞት ። ሕይወት ካለች ተስፋ ምን ጊዜም ይኖራል ። «በማደርገው መራራ ትግል ወድቄአለሁ»፣ «ለድል በሚደረገው ትግል ተሠውቻለሁ» ፣ «ናቅፋ የኔ መቃብር ፣ ያብዮቴ አምባ ትሆናለች» ፣ «ሞት አይቀርምና የሚሞቱበትን ቦታና ሁኔታ መርጦ መሞት ታላቅ እድል ነው ። ግን ናቅፋን አደራ ፣ እኔ የታሪክ ሰው አይደለሁም ። ተራ ወታደር ነኝ ። ግን ለኢትዮጵያችን ሕልውና ኤርትራን ወሳኝ ናት ሲሉ ሰምቻለሁ ። ለኢትዮጵያ ሕልውና ተሰውቻለሁ ። ከሕይወቴ በቀር ላገሬ የማበረክተው ሌላ ውድ ነገር የለኝም ። ወገኔ ፣ ከኢትዮጵያ ሕልውና ሌላ አደራ የለኝም ። አደራህን ። በኤርትራ ምድር የተከሰከሰው አጥንቴ በቁጣ እንዳይጮህ አደራ!» ወዘተ የሚሉም መልእክቶች ነበሩ ። የሚገርመው ነገር እኔ የማስተላልፈው መልእክት አልነበረኝም ። ጨርሶም አላሰብኩበትም ነበር ። ስለሞት አስቤ አላውቅም ። የሙያዬ ባሕርይ ፣ ያለምንም ስጋትና ጭንቀት በማያቋርጥ እሁን» ሁኔታ ውስጥ የመኖር ልማድ አሳድሮብኛል ። ስለወደፊት ለምን ይታሰባል? ትኩስ ዜና ፣ ትኩስ ሕይወት! ሞት ለኔ ምኔም አልነበረም ፣ ሆኖም አያውቅም ። ትኩስ ዜና ከማጣት ፣ አበቦችን ካላማየትና የቆንጆ ሴት እጅን ለመንካት ካለመቻል የበለጠ ስቃይና መለየት ምን ይኖራል! ሞት ትርጉም ሰጥቶኝ አያውቅም ። ምናልባት እድሜ ስላልተጫነኝ ይሆናል ። ሞት ሲቃረብ አሳቤ ምናልባት ሳይለወጥ አይቀርም ። አላውቅም ። አሁን ግን ሞት ሩቅ ሆኖ ነው የሚታየኝ ። ምን የሚያሰጋ ነገር አለ ? ከሞትክ ሁለት ነገር ብቻ ያስገሀል — መንግሥተ ሰማያት ትገባለህ ወይም ገሀነብ ትወርዳለህ — እንዲህ ያለ ነገር ካለ ማለቴ ነው ። መንግሥተ ሰማያት ከገባህ ምንም የሚያሰጋህ ነገር የለም ። ገሀነብም ከወረድክ የሚያሰጋህ ነገር የለም ። ከጓደኞችህ ጋር እጅ ለእጅ ስትጨባበጥ ለስጋት ጊዜ አይኖርህም» የሚል ጥቅስ የት እንዳነበብኩ ቦታው ጠፋኝ ። ከከፍታ ነጥብ

1702 ሌላ የሚያሲጋኝ ነገር አልነበረም ። እሱም ቢሆን ምን ያስጋል? ይያዛል ወይም አይያዝም ። ይልቅ ጭንቀቴ ዜናውን እንዴት አድርጌ እንደማስተላልፍ ነበር ። ጭንቀቴ ምንድነው? ነገ ምን ትርጉም አለው? ደሞ ለምን ይጨነቃል? እውን ነገር አሁን ብቻ ነው ። አሁን አለሁ ፣ ደህና ነኝ ፣ እተነፍሳለሁ ፣ ውብ ኮኮቦች እቆጥራለሁ ፣ ይበቃል ። አሁን አለህ ወይም የለህም ። ጭንቀቱ ምንድነው?...... ሌሊት ሁለት ጊዜ በእንቅልፍ ልቤ ቃዢቼ በመ ባነን ነቅቼ ነበር ። ሁለቱንም ጊዜ ላብ አስምጦኝ ነበር ። አንድ ጥይት በሔድኩበት እየተከተለች ታባርረኛለች ። እንዳትመታኝ እሮጣለሁ ። ላመልጣት አልችልም ፣ ትደርስብኛለች ። ገደል አፋፍ ላይ እደርሳለሁ ፣ መሔጃ የለኝም ። እና ጥይቷ እየተወረወረች ትመጣብኛለች ። ባንኜ እነቃለሁ ። በሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ከፍታ ነጥብ 1702 ላይ የወጣን ይመስለኛል ። ጠላት የለም ። ተራራው እንደ ሰው ልብ ሲመታ ይሮማኛል ። ቆይቶ የተራራው ትርታ አደንቋሪ ይሆናል ። ልቤ አብሮ ይሸበራል ፣ ነፍሴ ተጨንቃለች ። ተራራው ተጠምዶ እንደቆየ ቦምብ ድንገት ይፈነዳል ፣ ዓለም ይደበላለቃል ፣ ምጽዓት ይሆናል ፣ ጠርብ ድንጋዮች ሰማዩን ያለብሱታል ። እንደገና እያላበኝ እነቃለሁ ።

ልክ በ10 ሰዓት ከመሰብሰቢያ ወረዳችን ከከፍታ ነጥብ 492 ተንቃንቅን ። ቲከሲ ላይ ቶሎ ይነጋል ። ሮራ ጸሊም ላይ የንጋት ጸሐይ በሙሉ ድምቀቷና ውበቷ ስትወጣ ማየት እጅግ ያስደንቃል ። ተፈጥሮ ውብ የንጋት ትርኢት የምታሳይበት ቦታ ነው ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍታ ነጥብ 1702ን ከሩቅ አየሁ።የአካባቢው ትልቁ ተራራ ባይሆንም ከሌሎቹ ይልቅ ግርማ ሞገስ ተጎናጽፎ ታየኝ ። ቀጥ ብሎ ከምድር ወደ ሰማይ የተወረወረ ተራራ ነው ። የመቶ አለቃ ጋሻ ጠና ነበር ተራራውን ያመሹል ለከተኝ ። የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች በሙሉ እንጋጠው ተራራውን በአድናቆት ይመለከቱ ነበር ። ፊታቸው ያበራል ። ያውና የመጨረሻ ግባቸው! የልባቸውን ትርታ የሰማሁ መሰለኝ ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የራሴን የልብ ትርታ ነበር የማዳምጠው ።

ኰሎኔል ታሪኩ ወደኔ ሲመጣ አየሁት ። አረማመዱ ሁሉ ፈጣንና ቀልጣፋ ሁኗል ። አዲስ ዩኒፎርም ለብሷል ። ተርብ መስሏል ።



«ዛሬ አምሮብሀል» አልኩት ።

«የክት ልብሴን ነው» ብሎኝ ፣ ከሩቅ የሚታየውን ተራራ በዓይኖቹ ሲቃኝ ከቆየ በኋላ ፣ «ቆንጆ ተራራ ነው ። መቃብሬ እዚያ ላይ ቢሆን አይከፋኝም ። ለሰማይ ቅርብ ነው ፣ አይመስልህም?» አለኝ ።

«እኔስ ለመቃብሬ አዲስ አበባን ነው የምመርጠው ። ብዙ አበባዎች ያሉበት ቦታ ይሻለኛል» አልኩት ።

«እኛ ይህን ተራራ መርጠናል» አለኝ ።

«የሚሞትበትን ቦታ ማንም ሊመርጥ አይችልም ፣ ጀግኖችም ቢሆኑ» አልኩት ።

«ደርሰናል እንግዲህ» ብሎኝ ጦሩን ተከትለን ወደ ውጊያ ወረዳው እንዴት እንደምንሔድ አስረዳኝ ። ከጦሩ ኋላ መሆን ነበረብን ። የሕክምና ጓድ ኃላፊ የሆነ አንድ አሥር አለቃ በባል ደረባነት ተሰጠን ። ማንኛውንም መመሪያና ትእዛዝ መቀበልም ያለብን ከእሱ ነበር ። ወደ ከፍተኛ ነጥብ 1702 የሚወስደው መጠጊያ መንገድ ሁሉ በፈንጂ ታጥሮአል ። እና ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። አለዚያ በፈንጂ ድንገት ወደ ሰማይ ጉኑን እንደምንቀር የታወቀ ነገር ነበር ።

«አይዞህ ፣ ስለኛ አታስብ» አልኩት ።

«እንድትሞቱ አልፈልግም ። የወሬ ስንቅ ይዛችሁ ብትመለሱ ይሻላል» አለኝ ።

«ንገረኝ ታሪኩ በሞቴ ፣ ስለሞት አስበህ ታውቃለህ?» አልኩት ። ከብረት ቆቡ ውስጥ ወጥቶ የተንጠለጠለውን ረጂም ጠጉሩን መዞ እየገመደ ፣ «ወታደር በጦር ሜዳ ስለሞት አያስብም» አለኝ ።

«እንዴት?» አልኩት ።

«የቀበሮ ጉድጓድ ስንቆፍርና ፣ በደረት ስንሳብ ፣ ስንፏቀቅ ፣ በቀበሮ ጉድጓዳችን ውስጥ ሆነን ሲያልበንና ስንሲጋ ፣ ስናጠቃና ስናፈገፍግ ፣ ስለሞት ለማሰብ ጊዜ የለንም ። እንዴት ልበልህ?

ጠላት ነው ሁልጊዜ የሚሞተው ፣ አንተ አይደለህም» ካለ በኋላ ፣ ባሳብ ተውጦ ቆየና ፣ «ይልቅ ሕይወት ነው የሚያሳስበው ፣ ሞት አይደለም» ብሎ የእጅ ሰዓቱን ተመለከተና ፣ ውጊያው የሚጀመርበት ጊዜ ተቃርቧል ። አደራችሁን ተጠንቀቁ ። ቻው ። ከፍታ ነጥብ 1702 ላይ እንገናኛለን» በማለት በጣቶቹ የድል ምልክት አሳየኝና ትንሽ ከሔደ በኋላ ተመልሶ መጣ ። አተኩሮ ተመለከተኝ ። አንድ ነገር ሊነግረኝ ነው ብዬ ስጠብቅ አሳቡን ለውጠና ምንም ሳይለኝ ዝም ብሎ ተመልሶ ሔደ ። ምን ሊነግረኝ ፈልጎ ይሆን? ሆዴን ቆረጠኝ ።

ከዝቅተኛ መሬት በመጀመር ቀጥተኛ ግድለት ያለውን ተረተር በግራ በኩል ይዘን ወደ ግባችን እንጠጋ ጀመር ። አካሔዳችን ስንዝር በስንዝር ነበር ። ጊዜ ራሱ ድንገት ቀጥ ብሎ የቀረ መሰለኝ ። ተራራው ተረተሩ ፣ ሸለቆውና ግድለቱ እንደ መቃብር ጸጥ ብሎአል ። የዓለም ልብ ትርታ ድንገት ቀጥ ብሉ ፣ ሕይወት ለዘላለም አሸልባ የቀረች ያህል ሆኖ ነበር የሚሰማው ። የሰፈነው ጸጥታ ከባድ ውጥረትና ጭንቀት ሰው ላይ ያሳድራል ፣ ስጋት ይፈጥራል ፣ ያስጨንቃል ። የ17ኛ ክፍለ ጦር አካል የሆኑት 19ኛ እና 11ኛ ብርጌዶች ሥርጡን ይዘው ከቀይ እምቡጥ ሻሊቃ ጦር ግራና ቀኝ ተሰልፈዋል ። ሁለቱም ብርጌዶች ቀደም ብለው በውጊያ ወረዳው በመገኘት መሽገዋል ። ሁሉም ከቀበሮ ጉድጓዳቸው ውስጥ ሆነው ይታያሉ ። ሙቀቱ አይጣል ፣ 38 ድግሪ ሴንቲግሬድ ደርሷል ። ኰሎኔል ታሪኩ የተናገረው ሐቅ በመጠኑም ቢሆን ተከሰተልኝ ። ጦርነት ሲባል ሁልጊዜ የጨበጣ ውጊያ ማለት አይደለም ። በአብዛኛው ከቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ሆኖ የጠላትን ተኩስ ውርጅብኝ እያዳመጡ ላብ የመድፈቅ ፣ በስጋት የመጨነቅ ፣ በደረት እንደድመት የመሳብ ፣ የመንፏቀቅ ፣ ወሳኝ ሰዓት ስትደርስ የማጥቃት ፣ ቦታ የመያዝ ካልሆነም የማፈግፈግ ተግባር ነው ። ጦርነት እንደ ዳማ ጨዋታ ነው ። ግራና ቀኝ ጎንህንና ጀርባህን እየጠበቅህና የጠላትን ደካማ ጐን እያየህ እንደሁኔታው ታጠቃለህ ፣ ወይም ታፈገፍጋለህ ። የጠላት ተኩስና ኃይል ከበረታብህ ታፈገፍጋለህ ፣ ከተከበብክና መውጫ ካጣህ እጅህን ትሰጣለህ ። የጦርነት ጨዋታ ደንብ እንዲሁ ቢሆንም ፣ አብዛኛውን ጊዜ ደንቡ በተግባር አይውልም ። የጠላት ተኩስ ምን ቢበዛ ፣ ኃይሉ ምን ቢጠናከርና ከበባው ምን ፍጹም ቢሆን ፣ ሰዎች



አብዛኛውን ጊዜ እስከመጨረሻው ሰው ድረስ ይዋጋሉ ። በጦር ሜዳ ሎጂክ አይሠራም ። የተረፉት ጀግኖች ይሆናሉ ። የሞቱትስ? ክብር ለሙታን ። በእውነት ጦርነት አስቀያሚ ነው ። ያስጠላል ። ግን የሰው ልጅ ያለ ጦርነት የኖረበት ጊዜ የለም ። የሰው ልጅ ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው ። የሰው ልጅ ያለጦርነት የሚኖርበት ጊዜ ይመጣ ይሆን? ምኞት ነው ። የጦርነትን ጥፋት በሰው ልጆች ላይ የሚጋብዙ ሠይጣናዊ ኃይሎች እስካሉ ድረስ ምን ተስፋ ይኖራል?

በየተራራውና በየተረተሩ ሰፍኖ የቆየው ከባድ ጸጥታ ድንገት ተናግቶ ምድር ቀውጢ በመሆን ፣ መድፎች ያጓሩ ፣ የስታሊን ኦርጋኖች ተራራውንና ተረተሩን ያናግሩ ፣ መትረየሶች ይንፈቀፈቁ ክላሽኖች በየጎራው ይንጣጡ ጀመር ። ባንድ ጊዜ ድብልቅልቁ ወጣ ። አየሩ በፈንጂ ጢስና በጥይት ባሩድ ሽታ ተበከሏል ። ተዋጊ አይሮፕላኖች እንደ ቀስት ከሰማይ ወደ መሬት እየተወረወሩ አስበርጋጊና አስፈሪ ድምጽ ሲያሰሙ ከቆዩ በኋላ ከፍታ ነጥብ 1702 ፣ ካርታ ቁጥር 5044 ላይ የቦምብ ዝናብ ያዘንቡ ጀመር ። የወገን ከባድ መሣሪያ ከግራና ከቀኝ ያለ ማቋረጥ ያጓራል ። ተራራው ፣ ይቃጠላል ፣ ይነዳል ፣ ይጋያል ። የጠላት ባለ 50 ካሊበር መትረየሶች ከየተራራው ጫፍ ይንተከተካሉ ፣ ያስካካሉ ። ጸረ አይሮፕላኑን ያደበላልቁታል ። ቢ—10 ጸረ ታንክ መሣሪያዎች ይተኮሳሉ ። የእጅ ቦምቦችና ፈንጂዎች እንደ ነጎድጓድ ይጮሀሉ ። ሰዓቱ ደረሰ!

ባልደረባችን ያስር አለቃ ዳምጤ መሣሪያዎቹን በድምጽ እየለየ ያመለክተኝ ነበር ።መድፍ —ቦምብ —ፈንጂ —ሞርታር —ጸረ ታንክ —ጸረ አይሮፕላን አር ፓ.ጂ —ዶሽካ ሾቲ አር ዙ23— ቢ.ኤም — ወ.ዘ.ተ ። ካሜራችንን አንድ ምቹ ቦታ ላይ ጠምደን ነበር ። ፊልሙ ይዞራል ።

«እንዴት ነው?» አልኩት አሸብርን ።

«እስካሁን ጥሩ ነው ። ተራራው ጥሩ ሆኖ ይታያል ። ግን ለመጠጋት እንዴት ነው የምንችለው?» አለኝ ።

«ለመጠጋት ፈጽሞ አትችሉም ። እንኳን ለናንተ ለወታደሩም አስቸጋሪ ነው ። የሞት ተራራ ነው» አለኝ ። ያ10/ አለቃ ዳምጤ

«ከዚህ በኋላ ምንድነው የሚሆነው?» አልኩት ።

«እንግዲህ የቀይ እምቡጥ ጦር ግዳጅ ተቃርቧል ። አሁን መሐል ለመሐል ወደ ተራራው እየተጠጉ ናቸው ። ጊዜው ሲደርስ ከ11ኛ ብርጌድ በስተጀርባ ድንገት በመዞር ፣ በግራ በኩል ሰብረው ለመውጣት ነው የተዘጋጁት » አለኝ ።

«በዚያ በኩል ግድለቱ ቀጥተኛ ስለሆነ አስቸጋሪ አይሆንባቸውም ወይ?» አልኩት ።
«የተመረጠውም በዚህ ምክንያት ነው.....»
«እንዴት? ለምን?»
«በዚያ በኩል ይመጡብናል ብለው አያስቡም ተብሎ ስለታሰበ ነው» በማለት አስረዳኝ ።

«እስቲ ተስፋ እናድርግ» አልኩት ።

ከ58ኛ እና ከ51ኛየጠላት ብርጌዶች የተውጣጣ 1ኛ እና 3ኛ ሻለቃ ጠንካራ ኃይል ከፍተኛ ነጥብ 1702 ላይ መሽጎ የሚጠባበቅ መሆኑ ታውቋል ። ትኩረታቸው መሐል ለመሐል ሰንጥቆ በሚመጣው ቀዳሚ ጦርና ተደራቢና ደጀን ጦር ላይ መሆኑን ከኢላማቸው ለመረዳት ይቻል ነበር ። የተፈለገውም ይህ ነበር ። ተራራውን በከባድ መሣሪያና በተዋጊ አይሮፕላኖች የመደብደቡ ሥራ ቀጥሏል ። ዓለም ተደበላልቋል ። የሚሰማው የተኩስ ድምጽ እብዶች ተሰባስበው በምጽአተ መድረክ ላይ እንደሚጫወቱት ሙዚቃ ነበር!በተዋጊ አይሮፕላኖች የታጀቡ ትላልቅ አይሮፕላን መጥተው ተራራው ላይ ፓራ ኮማንዶዎችን በጃንጥላ ያወርዱ ጀመር ። የጠላት ተኩስ በረከተ ። ልቤ ተሰቀለ ። ግን ዓይኖቼን ለመክደን አልቻልኩም ።

«ምነው! ለእልቂት መዳረግ አይሆንም!» አልኩት ያሥር አለቃ ዳምጤን ።

«አይዞህ! ደሚዎች ናቸው» አለኝ ።
ደሚዎች ከሩቅ ሲመለከቷቸው ልክ የእውነት ሰዎች ይመስላሉ ።
«በቃ አሁን ነው!» አለ ።



«ከንቲባ» ስሜት ይዞት ወደ ፊት ሮጠ ። እንዲመለስ ብጮሀበትም ሊሰማኝ አልቻለም ። ተከተልኩት ። ደመ ነፍሴን ነበር የምሮጠው ፣ እሱን ለመያዝ ይሁን ወይም ከእሱ ጋር ለመሔድ ፣ የማደርገውን ነገር አላውቅም ነበር ። 19ኛ እና 11ኛ ብርጌዶች በቀኝና በግራ በኩል ሣንጃ ወድረው እየተኮሱ ተንቃነቁ ። የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች ልክ እንደተባለው ከ11ኛ ብርጌድ በስተጀርባ ዞረው ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 የሚያወጣውን አስቸጋሪ ግድለት ተያይዘውት ነበር ። ኰሎኔል ታሪኩ ፣ ሰዎቹን በያዘው ሽጉጥ ወደፊት እንዲሔዱ እየጋበዘ ፣ ካንዱ መረማመጃ ድንጋይ ወደ ሌላ በመዝለል ፣ ከጦር ጓዶቹ ፊት ቀድሞ ተራራውን ተያይዞታል ። የመቶ አለቃ ጋሻ ጠና ከጎኑ ነበር ። ጦሩ ከሚተኩሰው ጥይት ይልቅ በወኔ የሚያሰማው የውጊያ ጩኸት ይበልጥ የሚያስፈራ እና የሚያስበረግግ ነበር ።

ከንቲባን ደርሼበታለሁ ። ግን ተመለስ አላልኩትም ። ቀይ እምቡጦችን ተከትለን ጋራውን እንቧጥጥ ጀመር ። የድንጋይ ናዳ ግራና ቀኛችንን ይበራል ። ፈንጂና ቦምብ ምድሪቱን ያናውጣል ፣ የጠላት መትረየስ ያለማቋረጥ ይንተከተካል ፣ ይንፈቀፈቃል ። ጠላት ነቅቶ ወደ ቀይ እምቡጦች አቅጣጫ ዞሮ ነበር ። ግን ፣ ቀይ እምቡጦች የእጅ ቦምብ እንደጨበጡ ከጠላት ምሽጎች እየዘለሉ መግባት ጀምረዋል ። የፈንጂ ጢስና የባሩድ ሽታ ያፍናል ፣ ያስለቅሳል ። ካንድ በኩል ያለማቋረጥ እየተንፈቀፈቀ አላራምድ ያለ የጠላት መትረየስ ነበር ። የተኩስ እሩምታ ይረጭበታል ፣ የቦምብ ጋጋታ ይወርድበታል ። ግን መትረየሱ ላንቃውን አይዘጋም ፣ መረማመጃ በር ዘግቶ ዝም ብሎ ይንጣጣል ። አንድ ቀይ እምቡጥ እንደ ነብር እያደባና በደረቱ መሬት ይዞ የሞት ላንቃውን ወደማይዘጋው የጠላት መትረየስ ሲሳብ ድንገት አየሁትና ትንፋሼን ውጬ ዝም አልኩ ። ከንቲባም እንዲሁ አይቶት ኖሮ ፣ ቀጥሎ የሚሆነውን ነገር በውል ለማየት ጓጉቶ ሳይሆን አይቀርም ፣ አንገቱን ቀና አደረገ ።
«አብደሀል እንዴ! መሬት ቇዝ!» አልኩት ።
ዞር ሲል በአፉ ደም ሲወጣ አየሁ ።
«ከንቲባ!» ብዬ ጮህኩ ።

አልሰማኝም ። የጠላት መትረየስ ወደሚንጣጣበት አቅጣጫ ቴፑን እንደያዘ በረረ ። በዚያኑ ጊዜ ወደ መትረየሱ ይሳብ

የነበረው ቀይ እምቡጥ በደረቱ እንደተኛ አንድ ቦምብ ከወረወረ በኋላ ፣ እንደ ነብር ዘሎ መትረየሱ ተጠምዶበት ወደ ነበረው ምሽግ ገባ ። ከንቲባ መሐል መንገድ ሲደርስ ወደቀ ። ከተኛሁ በት ተነስቼ ወደ ከንቲባ ሮጥኩ ።

«ከንቲባ! ከንቲባ!»

አይሰማኝም ። ጸጥ ብሎ ቀርቷል ። ወዙ እንዳለ ነበር ። የምጸት ሳቅ የሚስቅብኝ መስሎ ታየኝ ። እንገቱ ላይ ተጠምጥሜ ሳምኩት ። እና እንደአበደ ሰው ተነስቼ መትረየሱ የሞት ላንቃውን ይከፍትበት ወደነበረው ምሽግ ሮጥኩ ። የመትረየሱ ላንቃ በመዘጋቱ ቀይ እምቡጦች ሆ!ብለው ወደ መጨረሻ ግባቸው መረማመድ ጀምረዋል ። እንደ ሮጥኩ ሔጄ ከምሽጉ ገባሁ ። መትረየሱና ተኳሹ በቦምብ ጋይተዋል ። ቀይ እምቡጡ የሌላውን መትረየሱና ተኳሹ ... ከመትረየሱ ኋላ ጋይቶ የወደ ጠላት ጉሮሮ እንዳነቀ ውድቋል ። የቀይ እምቡጡን ክላሺን አነሳ ቀው ጠላት እግረ ቆራጣ ነበር ። የቀይ እምቡጡን ክላሺን አነሳ ቀው ጠላት ሬሣዎችን ወደላይ እየተን ጠራራሁና እየጮሁኩ በሳ ሁና የጠላት ሬሣዎችን ወደላይ እየተን ጠራራሁና እየጮሁኩ በሳ ንጃ ወጋሁ...... ወጋሁ...... እስከሚበቃኝ ድረስ ። እና ቁጭ ብዬ ማልቀስ ጀመርኩ ።

እንደ ሞተ ሰው ሆኘ ነበር በሙታን መካከል የምዘዋወ ረው ። ግንባሩ በጥይት ተነድሎ የወደቀ ፣ ስውነቱ እንደ ወንፊት በጥይት ተበሳስቶ የተዘረረ ፣ ጭንቅላቱ ተቆርጦ ከላዩ ላይ የበ ረረ ፣ እጅና እግሩን አጥቶ የተንጋለለ ፣ የተሰበረ ፣ የጋየ ምሽግ። ደሙን እያዘራ «ስለ ወንድ ልጅ ፣ ውሀ እባካችሁ......» እያለ ጠብታ ውሀ የሚለምን ፣ በሞትና በመኖር ስቃይ መሐል ተይዞ ፣ «እባካ ችሁን ስለወንድ ልጅ አትለፉኝ ፣ ጨርሱኝ ፣ ለነፍስ እሆናችኋ ለሁ ......» እያለ የሚማጠን ድምጽ ፣ እዚህም እዚያም ስውነታ ቸው በታላቅ ፍርሀት የሚርበደበድ እንገታቸውን የደፉ ምርኮ ኞች ። በገሀነብ አዳራሽ ውስጥ እንደመዘዋወር ነበር ። የጠላት ወገን የሞተው ሞቶ ፣ የቆሰለው ቆስሎ ፣ የተማረከው ተማርኮ ፣ የተቀረው ትጥቁን እንዳለ ጥሎ ፈርጥጧል ። ካሜራችን ወዲህና ወዲያ ይሮጥ ነበር ። ከፍተኛ ነጥብ 1702 በቀይ እንቡጥ ቁጥጥ ሥር ቢውልም አልፎ አልፎ ተኩስ ይሰማል ፣ ስለታሪክ ምንም ደንታ አልነበረኝም ። የስው ልጅ ስቃይ ታሪክ ምን ታሪክ ይሆ



ናል? ታሪክነቱ ምኑ ላይ ነው? ጭንቅላቴ ዝም ብሎ ይዋኝ ነበር ። ጥላቻ ብቻ ነበር ልቤን የሞላው ። እና ቀይ እምቡጦች ለምርኮ ኞች ደረቅ ራሽንና ውሀ ሲሰጡ ፣ የቆሰለውን ሲያክሙና አይዞህ እያሉ ሲያጽናኑ ተመልክቼ ፣ በንዴትና በጥላቻ ፣ «እነዚህን የታሪክ ዲቃላዎች ለምን አትጧቸውም!» በማለት ጮህኩባቸው።

ትዕዛዜን የሚቀበል ወይም የሚሰማኝ ሰው አልነበረም፣ ያበድኩ መስያቸው ሳይሆን አይቀርም ሁሉም በመገረም ዝም ብለው ይመለከቱኝ ነበር ።

«ምን ታዩኛላችሁ! ጅሎች! እውነቴን ነው ። እነዚህ የታሪክ ዲቃላዎች ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ያለምንም ርኅራኄ በጭካኔ ሲጨፈጭፉን የነበሩ አውሬዎች ናቸው ። እኛ ለእነሱ ሰዎች አይደለንም ፣ የማናስብ እድጊዎች ወይም ጥሬ ሥጋ የሚጎምዱ «ሌሌዎች» ነን! ለእነሱ እኛ አሁንም ቅኝ ገዢዎችና ወራሪዎች ነን ። በእነሱ ግምት እኛ እንኳን ሌላውን ራሳችንንም ለማስተዳደር የማንችል አህዮች ነን! እድል ካገኙ አይምሩንም ። ጨካኝ አውሬዎች ናቸው......» እያልኩ ስጮኽ አንድ ሰው ትከ ሻዬን ይዞ ወደኋላ ጉተተኝ ። ኰሎኔል ታሪኩ ነበር ።

«አይዞህ» አለኝ ።
«ምን አይዞህ ትለኛለህ? በላቸው!»

«አሺ ጓጋዬ ፣ አይዞህ ። ይህ ጦርነት ነው ። ስህተቱ የነዚህ ምስኪን ሰዎች አይደለም ። ያስመታደል ሆኖ ነው እንጂ ፣ በሌላ ጊዜና ሁኔታ ከነዚህ ሰዎች ጋር እንደወንድማማች አብረን እንስቅና እንጫወት ነበር» በማለት ሊያጽናናኝ ሲሞክር ከምር ኮኞቹ መካከል አንዱ የተሰጠውን ደረቅ ራሽን አንድ ቀይ እም ቡጥ ፊት ላይ በድፍረት ወርውሮ ሊያንቀው ተነሳ ።

ኰሎኔል ታሪኩ እኔን ለቀቀኝና ሔዶ ፣ ምንድነው? አለው ።
«እንት ነጻ አታወጣኝም!»
«ታዲያ ማነው ነጻ የሚያወጣህ!»
«ፔትሮ ዶላር መጥቶ ነጻ እስከሚያወጣው ይጠብቅ! በለው! አልኩኝ ።
«ሻዕቢያ ስዘላለም ትኑር!» አለ ።

ሌላው ምርኮኛ በታላቅ ቁጣ «ሻዕቢያ ትውደም!» ብሎ ቀጠለና ፣ «ይህ ሰው እኛን አይወክለንም» ከጥቂት ጊዜ በፊት ከኋላ በጥይት እየደበደበን ሲያዋጋን የነበረ አረመኔ ነው ። ኑሮአችን ከኋላችን እሳት ከፊታችን እሳት ነበር ። አሁን ነጻ ወጥተናል ፣ ወንድሞቼ ነጻ ወጥተናል» አለና እንባውን ዱብ ዱብ አደረገ ።

ኰሎኔል ታሪኩ ወደ ደንፊው ምርኮኛ መለስ ብሎ ፣ «ይህን ሰው ፈትሸው» በማለት የመቶ አለቃ ጋሻ ጠናን አዘዘው ።

ጋሻ ጠና እንደታዘዘው ምርኮኛውን ሊፈትሽ ጠጋ ሲለው ፣ መሣሪያውን ለመቀማት ይታገለው ጀመር ። ኰሎኔል ታሪኩ ራመድ ብሎ በግራ እጅ አንቆ ያዘውና ፣ አትሞትም! ይህች ምድር ከወንበዴዎች ነጻ መውጣቷን ሳታይ አትሞትም! ውሰዱት ይህን ወስላታ!» አለ ።

ወንበዴው አልተበገረም። ኰሎኔል ታሪኩን ፊቱ ላይ ተፋበበት ። ታሪኩ አልተናደደም ። ለጥቂት ሴኮንዶች ዝም ብሎ ተመለከተው ። በግራ እጁ ወደ እሱ ሳብ አደረገውና ግንባሩ ላይ ሳመው ። እና ሽጉጡን መዞ እዚያው ግንባሩ ላይ ባንድ ጥይት ነድሎ ጣለው ። ሌሎቹን ምርኮኞች ብርክ ያዛቸው ። መቆም ስላቃታቸው ። ወደቁ......

«ከፊቴ ውሰዷቸው !» አለ ኰሎኔል ታሪኩ ። ተመትቶ የወደቀው ወንበዴ የጓድ መሪ ነበር ። ኪሱ ሲፈተሽ አንድ ቁራጭ ወረቀት ተገኘች ። አጭር መመሪያ ተጽፎበታል ። መመሪያው ፣ «አሥመራ ባስቸኳይ ሔደህ ለሥዕላይ በራኺ ሪፖርት አድርግ ። ፓራዲዞ ቡና ቤት ታገኘዋለህ ። እና አሮማይ የሚለውን ኮድ አስታውስ» ይላል ። ኮዱ በመመሪያው ላይ አልተገለጸም ። ብዙ ገንዘብ በኪሱ ይዞ ነበር ። «አሮማይ» የሚለው ቃል ጭንቅላቴን መታኝ ። ኰሎኔል በትሩ ተሰማ ስለ አሮማይ የጠየቀኝ ጥያቄ ትዝ አለኝ ። የሰውዬው መገደል ቢጸጽተኝም ምንም ማድረግ አልተቻለም ። ሞቱን የፈለገበት ምክንያት አሁን ገባኝ ። እና ሬሣውን ረገምኩ ። ቢሆንም የሥዕላይ በራኺን ማንነት በማወቄ ደስ አለኝ ። ሥዕላይ በራኺ! እጉያችን ውስጥ! ገረመኝ ። የኰሎኔል በትሩ ጥርጣሬም አስደነቀኝ ። አሮጌ ቀበሮ!



ብዙ ቀይ እምቡጦች ብናጣም ድሉ የኛ ሆኗል ። ከንቲባ አንዱ ቀይ እምቡጥ ነበር ። የከንቲባን ሞት መቀበል ወይም ማመን አልቻልኩም ። በቅርብ የሚያውቁትና የሚወዱት ሰው ሲሞት ማመን ያስቸግራል ። ትዝታው አይሞትም ። በዚያኑ እለት ዘጠኝ መቶ የጠላት ሬሣ ተቆጠረ ። በቦምብ ከጋዩት ሌላ አያሌ መሣሪያዎች በወገን ጦር እጅ ገቡ ። የቀይ እምቡጥ ዘመቻ ዓርማ ከከፍታ ነጥብ 1702 ላይ ሲተከል የነበረው ስሜት እጅግ አድርጎ ልብ የሚነካ ነበር ። ለወደቁት የቀይ እምቡጥ ጀግኖች እሩምታ ተተኮሰ ፣ የሕሊና ጸሎትም ተደረገላቸው ። ሁሉም የሞቱት የጀግና ሞት ነበር ። አብዛኛዎቹ የሞቱት የእጅ ቦምብ እንደጨበጡ ጠላት ምሽግ ውስጥ ዘሎ በመግባት ነበር ። ብቻውን የወደቀ አንድም የቀይ እምቡጥ ጀግና አላየሁም ። የጠላት አንገት አንቀው የወደቁ ብቻ ነበሩ ። ጓዶቻቸው ወደፊት እንዲራመዱ መስዋእት የሆኑ ነበሩ ። ኰሎኔል ታሪኩ ለቀይ እምቡጥ ዘመቻ ዓርማ ወታደራዊ ሠላምታ በሚሰጥበት ጊዜ ፣ እንባው ጉንጮቹን አቋርጦ ጫካ ከመሰለው ጢሙ ውስጥ ገብቶ ሲጠፋ ይታይ ነበር ። ጀምበሯ አቆልቁላለች ። ሮራ ጸሊም ጠቁሮአል ። ሰማዩ በሺህ ቀለማት አሸብርቆ ቀልቷል ። አድሀባ ሸለቆ ላይ ጸሐይ ስትጠልቅ ማየት ሌላው የተፈጥሮ ትንግርትና ተአምር ነበር ። ይገርማል ፣ የሰው ልጅ የመኖር ናፍቆት እንዲያድርበት ተፈጥሮ ዘላለም እንደጋበዘችው ትኖራለች ። የተረፍነው ጥሪዋን ተቀብለን በደም የያዝነውን የውጊያ ወረዳ ማጠናከር ጀምረን ነበር ። ሥራው ብዙ ጥረት አልጠየቀም ። ተጠናክሮ የቆየውን የጠላት ምሽግ በይበልጥ የማጠናከር ሥራ ነበር ። ቲከሲ ወደሚገኘው የወገን ማዘዣ ነጥብ ተመልሼ እዚያ እንዳድር ኰሎኔል ታሪኩ ጠይቆኝ ነበር ። ግን አሳቡን አልተቀበልኩትም — «ለምንድነው እንዳንዳችሁ የማትቆጥረኝ!» በማለት ።

«ይሁን ። አንዳችን ነህ» በማለት ተወኝ ።

«እንኳን ደስ ያለህ» አልኩት ።

«አስደናቂ ድል ነው ። ግን ድሉ የቀይ እምቡጦች ብቻ አይደለም ። ከጥሩ ቅንብርና እቅድ የተገኘ የጋራ ድል ነው» አለኝ ።

ልክ ነበር ። አሁን ሳስበው እቅዱና ቅንብሩ በጣም የሚያስደንቅና የሚያስመሰግን ነበር ። ቀጠለና ፣ «ግን ፣ አሁን አንድ ችግር ይታየኛል» አለኝ ።

«ምን ? »

«ጠላት ድንገት ሆኖበት ነው እንጂ ይህን ነጥብ በቀላሉ አይለቅም ነበር ። አሁንም ተስፋ ቆርጦ አይቀርም ። ይህ ነጥብ ከተያዘ ሌሎችም ነጥቦች አንድ ባንድ ይወድቃሉ ። የናቅፋ በር ተከፈተ ማለት ነው ። እንደምታየው ናቅፋ ከዚህ ነጥብ በስተጀርባ ናት ። ስለዚህ ጠላት ያለ የሌለ ኃይሉን አሰባስቦ መልሶ የማጥቃት ርምጃ የሚወስድ መሆኑ የማይቀር ነገር ነው ። ፈጥነን በመንቃነት ድሉን ካላሰፋን ኋላ ችግር ይገጥመናል» አለኝ ።

«ታዲያ ችግሩ ምንድነው?»

«ፍጥነትና የሰው ኃይል ። እኛ የሽምቅ ተዋጊዎች ፍጥነት የለንም ። በዚህ ላይ ደግሞ አንዳንድ ኃይሎቻችን ልምድ ያንሳ ቸዋል ። አሁን ወሳኙ ነገር ፍጥነት ነው» አለኝ ።

ለናቅፋ መንደርደሪያና መሸጋገሪያ ድልድይ የሆነው ከፍታ ነጥብ 1702 በመያዙ ፣ የ17ኛ ክፍለ ጦር ዋስትና የሆነው የግራ ክንፍ 11ኛ ብርጌድ በሁለተኛው ቀን ወደ ከፍታ ነጥቦችን 1521 1527 1590 በአንድ ምዕራፍ አጥቅቶ ለመያዝ ተንቀሳቀሰ ። በ1807 ሰዓት እነዚህ ነጥቦች በሙሉ በወገን ጦር እጅ የወደቁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ ሰማን ። ከእንግዲህ የናቅፋ መውደቅ የጊዜ ጉዳይ ነበር ። ጋቢጣዎቻችንን እያጋጨን የፈላ ሚሊ ድራ ፍት ስንጠጣ አመሸን ። ካሁኑ ስለናቅፋ ማለም ጀምሬ ነበር ። ናቅፋ ካለንበት ከሰባት ኪሎ ሜትር በላይ አትርቅም ። አጠቃላዩ የድል ምሥራች ደወል ሲደውል ይሰማኝ ነበር ። አንዱ ቀን ሔደ ፣ ሌላው ቀን መጣ ። ካንድ ድንጋይ ጥላ ሥር ቁጭ ብዬ ማስ ታወሻዬን እየተመለከትኩ ሳስተካክል ከከፍታ ነጥብ 1702 በስተቀኝ ድንገት ከባድ ተኩስ ተከፈተ ። ድብልቅልቁ የወጣ የከባድ መሣሪያዎች ተኩስ ነበር ። ምን ይሆን ? እያልኩ ሳስብ ኰሎኔል ታሪኩ ረዳቱን ልኮ አስጠራኝ ። ናቅፋ ለመግባት የሚ ደረገው የማጥቃት ርምጃ የተጀመረ መስሎኝ ደስ ብሎኝ ነበር ። ግን የታሪኩን ፊት ላይ አድርብኝ የነበረው የደስታ ስሜት እንደ በጋ ጉም ከውስጤ ቦንኖ ጠፋ ።



«ምንድነው?» አልኩት ።

«ከፍታ ነጥብ 1702ን ለቀን መውጣት አለብን» ብሎኝ የእጅ ሰዓቱን ተመለከተና ፣ «ልክ በ18 መቶ ሰዓት» አለኝ ።

«ትቀልዳለህ!»

«ትዕዛዝ ነው» አለኝ ።

«ግን ፣ ለምን? ምን መጣ?»

ሁኔታውን ረጋ ብሎ አስረዳኝ ። ጠላት ያለ የሌለ ኃይሉን አሰባስቦ በመስበቅና ፣ ቢ— 10 ጸረ ታንክ ፣ 120 እና 82 ሚ.ሚ. ሞርታሮች ወደፊት በማቅረብ ፣ እንዲሁም መድፍና ታንክ በርቀት በመጠቀም 19ኛ ብርጌድ ይዞት የነበረውን ከፍታ ነጥብ 1755ን ሰብሮ በመግባት አስለቅቋል ። ከፍታ ነጥብ 1755 ጠላት እጅ ተመልሶ ከወደቀ ፣ ከፍታ ነጥብ 1702 በግራ ክንፍ በኩል ክፉኛ ስለሚጋለጥ ለመከላከል እጅግ ያስቸግራል ። እንዲያውም ለመከላከል አይቻልም ። የመከላከሉን ኃይል ለማጠናከር እን ዳይቻል ደግሞ አጎራባች ኃይሎች ስለዘገዩ በወቅቱ አይደርሱም ። ሌላ አዲስ ተዋጊ ኃይል ለማሰለፍ የጊዜው ሁኔታ አልፈቀደም ። በመካሔድ ላይ ያለው ውጊያ የወገንና የጠላት ጦር በጠባብ ወረዳ ላይ የተሰባጠረበት ሁኔታ ስለሆነ በተዋጊ አይሮፕላኖችም ሆነ በከባድ መሣሪያዎች ለመጠቀም አላመቸም ። በዚህ ላይ ውጊያ የሚደረግባቸው ወረዳዎች ሁሉ በጣም ጠባብ ስለሆኑ አሁን ተጨማሪ የሰው ኃይል ቢገኝም እንደልብ ማሰለፍ ያስ ቸግራል ። ሌላው ችግር ጠላት ያደረገው የተጠናከረ ዝግጅት ነበር ። ጠላት የወገንን ጦር ንቅናቄና አሰላለፍ በሚገባ ያው ቃል ። በቂ መረጃ አለው ። የመረጃ ምንጫቸው ካልተዘጋ የወገን ጦር በጦር ሜዳ የሚያደርገው ፍልሚያ ሊሰምር አይችልም ። ስለዚህ ለጊዜው ያለው አማራጭ የተያዙትን ወታደራዊ መሬቶች ለቆ ወደኋላ ማፈግፈግ ወይም በጠላት ተቆርጦና ተከቦ እየተዋጉ ማለቅ ወይም እጅ መስጠት ብቻ ነው ።

«እውነትክን ነው?» አልኩት ።

«ይኸው ነው» አለኝና በራዲዮ መገናኛ በኮድ መልክ የደ ረሰውን አጭር ትእዛዝ እንደገና ካነበበ በኋላ የመቶ አለቃ ጋሻ ጠናን ጠርቶ ፣ ቀይ እምቡጦች ልክ በ18 መቶ ሰዓት ነጥባቸውን ለቀው ለመውጣት እንዲዘጋጁ አዘዘው ።

ይህን ስትራተጂካዊ ነጥብ ለማስለቀቅ ውድ ሕይወታቸውን እሳልፈው የሰውት ቀይ እምቡጦች ታዩኝ ፡፡ በታላቅ ንዴትና ቁጣ ፣ «ይህን ሁሉ ቀደም ብለን ለምን አላሰብንበትም ነበር! ናቅፋ ለመድረስ የቀረን ሰባት ኪሎ ሜትር ብቻ ነው ፡፡ አሁን እነዚህን ነጥቦች መልቀቅ ምን ማለት ነው? ወይስ ወታደራዊ ቀልድ ነው!» አልኩት ፡፡

«የለም ጾግሽ ፣ የጦርነት ጨዋታ ነው ፡፡ ማጥቃት እንዳለ ሁሉ ማፈግፈግም ይኖራል ፡፡ የበላይ አለቆቼ የዚህን ገዥ መሬት ወሳኝነት ያውቃሉ ፡፡ ሊቀን እንድንወጣ የፈለጉት ለሕይወታችን ሰግተው ነው ፡፡ ግን እኛ የመጣነው በፊትም በሕይወታችን ቆርጠን ነው ፡፡ ለቆን መውጣት የለብንም» ብሎ መልእክቱን እኪሱ ከተተ ፡፡ ደስ የሚል ፈገግታ ፊቱ ላይ ይታይ ነበር ፡፡ ባሳቡ የቆረጠ መሆኑ ያስታውቃል ፡፡ ቀጠለና «እኔ አልሄድም ፡፡ ይህ ተራራ የኔ ተራራ ነው ፡፡ በእጄ የተከልኩትን ዓርማና ቀይ ሰንደቅ በእጄ ከመንቀል ሞቴን እመርጣለሁ!» አለኝ ፡፡

ላጭር ጊዜ ከባድ አሳብ ዋጠኝ ፡፡ ግን የማስበውን ነገር አላወቅሁም ፡፡ ከባድ ዝምታ ብለው ይሻላል ፡፡ የጋሻው ጠና ተመልሶ መምጣት ነበር ከዝምታዬ የቀሰቀሰኝ ፡፡ በጓዶቻቸው ደም የያዙትን ነጥብ ለቆ ለመሔድ የሚፈልግ አንድም ቀይ እምቡጥ እንደሌለ ለኰሎኔል ታሪኩ ነገረው ፡፡

«እርግጠኛ ነህ?» አለው
«እርግጠኛ ነኝ ጓድ ኰሎኔል.....»
«እኔም ከእነሱ እንደማልለይ ንገራቸው ፡፡ እዚሁ እንሞታለን.....»
«የበላይ ትእዛዙስ ጓድ?»

«ስለእሱ አትጨነቅ፣ ይህን ገዥ ወታደራዊ መሬት መልቀቅ የለብንም ፡፡ እስከ መጨረሻ ሰው ድረስ እንዋጋለን ፡፡ የማስረዳቱ ኃላፊነት የኔ ነው » ብሎ አሰናበተውና ወደኔ መለስ በማለት ፣ «አንተና ጓዶችህ አሁን መሔድ አለባችሁ» አለኝ ፡፡

«ማን አለህ! » አልኩት ፡፡
ሳቀና ፣ «ወታደራዊ ትዕዛዝ ነው» አለኝ ፡፡



«እንደኛ እኔ ወታደር አይደለሁም ፡፡ ሁለተኛ ምነው አንተ አልተቀበልከው?» አልኩት ፡፡

ከተቀመጠበት ተነስቶ ፊቴ ሲንጐራደድ ቆየና ፣ «ስማኝ ጾጋዬ ፣ ከበላይ የተሰጠው ትእዛዝ ልክ ነው ፡፡ ለሕይወታችን ታስቦ ነው ፡፡ ግን ይህ ገዥ መሬት ነው ፡፡ በምንም ሁኔታ መልቀቅ የለብንም ፡፡ ከዚህ ቀደም እንዳልኩህ በጦር ሜዳ ምክንያትና ሎጂክ ሁልጊዜ አይሠራም ፡፡ መኖር የሰው ምኞት ነው ፡፡ ግን እኛ አሁን ከሎጂክ ውጭ ሆነናል ፡፡ እና አሁን የኛን አስተሳሰብ የሚለውጥ ምንም ኃይል የለም ፡፡ እዚሁ ለመሞት ፈልገናል ፡፡ እና እዚሁ እንሞታለን» አለኝ ፡፡

«እኔም» አልኩት ፡፡
«እንድትሔድ የምፈልግበት ሁለት ምክንያቶች አሉኝ.....»
«ምንና ምን?»
«አንድ እዚሁ ብትቀር ማን ታሪካችንን ያቀርብልናል?»
«ታሪክ ገደል አባቱ ይግባ!»
«ሁለት ፣ የምታደርስልኝ የግል መልእክት አለኝ.....»
«ምን ?»
የታሸገ ኢንቬሎፕ ከደረት ኪሱ አውጥቶ ሰጠኝና ፣

«መልእክቱ ምንና ለማን እንደሆነ አልነግርህም ፡፡ በሕይወት ከተገናኘን መልሰህ ትሰጠኛለህ ፡፡ ካልሆነም ኢንቮሎፑን ከፍተህ ምን እንደሆነ ካየህ በኋላ ለሚመለከተው መልእክቱን ታደርስልኛለህ ፡፡ ይህችን ውለታ አድርግልኝ» ብሎ እጄን ጨብጦ ያዘና «መልእክቱ ቁም ነገር ኖሮት አይደለም ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ጅልነት ነው ፡፡ ግን ዋናው ነገር ያንተና የጓዶችህ መሞት ጥቅም የለውም ፡፡ የምትጽፏቸውና የምትናገሯቸው ነገሮች ፣ የምታትሟቸው ፎቶግራፎችና የምታሳዩዋቸው ፊልሞች ላሁኑ ብቻ ሳይሆን ለመጪውም ትውልድ ይጠቅማሉ ፣ ትምህርት ይሆናሉ» በማለት እንድንሔድ ሲያግባባኝ ከቆየ በኋላ ፣ በመጨረሻ ፣ «እምቢ ብትልም በግድ እሰድሃለሁ ፡፡ እውነቴን ነው ፡፡ ምንም ቢሆን ኃላፊነት ይሰማኛል» አለኝ ፡፡ ቀልዱን አልነበረም ፡፡ የምሩን እንደሆነ ፊቱ ይናገር ነበር ፡፡
«ለምን?» አልኩት ፡፡
«ለታሪክ» አለኝ ፡፡

በግድም ሆነ በውድ መሔድ ነበረብኝ ። የግል መልእክቱን እንዳደርስለት የጣለብኝ ኃላፊነትና አደራ በጣም ከብዶኝ ነበር ። 18 መቶ ሰዓት ከመድረሱ በፊት ቀይ እምቡጦችን ከተሰነባበትን በኋላ ወደ ቲከሲ ለመሔድ ተነሳን ። እንባዬን ቋጥሬ ለመያዝ አልቻልኩም ። ኰሎኔል ታሪኩ በመጨረሻ ስም ከተሰናበተኝ በኋላ ፣ የሜዳ መነጽሩን ካንገቱ ላይ አውልቆ ሰጠኝ ።

«ምን ያደርግልኛል?» አልኩት ።

«ከእንግዲህ ምን ይጠቅመኛል? ጠላት ወደኔ ነው እንጂ የሚመጣው እኔ ወደ እሱ አልሄድም ። ባይሆን ከሩቅ እንድታየኝ ይረዳሀል ፣ ሩቅ እይበት ። ቻው» ብሎ እንደለመደው በጣቶቹ የድል ምልክት አሳየኝ ።

ትዝ ብሎኝ ከተገደለው ወንበዴ ላይ የተወሰደውን መመሪያ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት ።

«ምን ትሠራበታለህ?» አለኝ ።

«ያስፈልገኝ ይሆናል» አልኩት ።

ወረቀቷን ፣ ከያዘው ኮሮጆ ውስጥ አውጥቶ ሌሎችም ወረቀቶች ጨምሮ ሰጠኝ ። ሌሎቹ ወረቀቶች ላዛዥ መኰንኑ የሚሰጡ ነበሩ ። እኔም እንደእሱ በጣቶቼ የድል ምልክት አሳየሁትና ፣

«በድል እንገናኛለን» አልኩት ።

«በእርግጥ ድል ከኛ ጋር ነው» አለኝ ።

አገላብጬ ሳምኩትና አጃቢዎቻችንን ተከትለን ቁልቁለቱን ተያያዝነው ። ሆዴ አላስችለኝ ስላለ ወደኋላ መለስ ብዬ አየሁት ። ቀጭን ሽንጡን ይዞ ቁሞ ሳየው ናቅፋ ተራሮች ላይ በግርማ ሞገስ የሚያንዣብብ ንስር መስሎ ነበር ።

አጃቢዎቻችን ለሌሎች የወገን ጦሮች ካስረከቡን በኋላ ከመንገድ ተመለሱ ። በፍጥነት ነበር የምንጓዘው ። በየመንገዱና በየሥርጡ ከፍተኛ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ይታያል ። በወሳንሳ የሚሔዱ ቁስለኞችም ነበሩ ። አንድ ቁስለኛ ከተኛበት ተነስቶ ተኩስ ወደበረከተበት አቅጣጫ ታላቅ ድምጽ እያሰማ ሲሮጥ አየሁ ።



ልቀቁን በማለት ከጓደኞቻቸው ጋር የሚተናነቁ ሌሎችም ቁስለኞች ነበሩ ። ዓይኔ ግን ያረፈው አንድ ወጣት ቁስለኛ ላይ ነበር ። ከፋኛ ቆስሏል ። የሞርታር ፍንጣሪ እግሩን ቆርጦታል ። ደጋግሞ፣ ሲቃየን እያያችሁ ምነው ዝም ትሉኛላችሁ? ቦምብና መሣሪያዬን አስጨብጣችሁኝ እዚያው ብትተውኝ ወይም ብትጨርሱኝ ምን ነበረበት! እባካችሁን ጨርሱኝ!» እያለ ይማጸናል ። እንዲሁ ሲማጸን ትንሽ መንገድ እንደሔድን ፣ እንዴ አሳርፉኝ ብሎ ጓደኞቹን ለመነ ። ካንድ ቁጥቋጦ ጥላ ሥር ትንሽ እንዲያርፍ እድል ሰጡት ። አንዱን ወታደር ጠራውና የሆነ ነገር ነገረው ። ወታደሩ የሰማውን ሰምቶ ዞር ከማለቱ ቁስለኛው ወጣት ከተዘናጋው ወታደር ሽጉጡን ከመቀጽበት ላጥ አድርጎ በዚያው ቅጽበታዊ ፍጥነት ራሱን ጨረሰ ። ትራጀዲ ሲበዛ ያደነዝዛል መሰለኝ ደርቄ ቀረሁ ። ስሜት ከውስጤ ተጨምቆ አልቆ ባዶ የሆንኩ ያህል ሆኖ ነበር የሚሰማኝ ። ከበስተቀኛችን ጦርነቱ እንደተፋፋመና እንደተቀጣጠለ ነበር ። ምንም እክል ሳይገጥመን ምሽት ላይ ቲከሲ ፣ ማዘዣ ነጥብ ደረስን ። ለአዛዥ መኰንኑ ኰሎኔል ታሪኩ የላካቸውን ወረቀቶችንና ካርታዎችን አስረከብኩ ። በብረት ከዘራው መሬት እየወጋ በንዴት ይቃጠል ነበር ። የኰሎኔል ታሪኩና የቀይ እምቡጦች መልእክት ቀደም ሲል ደርሶታል ። አንዳንዴ እንደ አበደ ሰው ዝም ብሎ በጥቁር ብረት ከዘራው ካርታ አሸዋ ላይ ይስላል ። አይናገርም ። ቆይቶ ፣ ቆይቶ ፣ እሳት ይተነፍሳል ። ረዳቶቹ ከበውት ቆመዋል ። መሣሪያ አልታጠቀም ። ረዳቶቹ ሆነ ብለው መሣሪያውን ያስፈቱት ይመስላል ። አሥር ዓይነት ጥያቄ ቢያቀርብልኝም ኰሎኔል ታሪኩ በላከው መልእክት ላይ የማክለው አሳብ አልነበረኝም ።

«ለምን! ለምን!» ብሎ የብረት ከዘራውን አሸዋ ላይ ተከላት ። ከከፍታ ነጥብ 1702 የሚመጣውን ዜና ወይም መልእክት ለመስማት ከራዲዮ መገናኛ ዙሪያ ተሰብስበን አመሸን ። መጨረሻ የደረሰን መልእክት ፣ «ተከበናል — ቆሎ አልቆብናል — ቢሆንም ድሉ የኛ ይሆናል — ውጭ !» የሚል ነበር ። የታሪኩ ድምጽ ነበር ። ከድምጹ በስተጀርባ ከባድ ተኩስ ይሰማ ነበር ። የራዲዮ መገናኛ መሣሪያውን ከበን ቆየን ። ስንት ሰዓት እንደ ቆየን አላውቅም ። ጊዜ ትርጉም አልነበረውም ።

«ቀይ እምቡጥ ና! ቀይ እምቡጥ ! ናደው ነኝ ። ትሰማኛለህ? ቀይ እምቡጥ!...... ቀይ እምቡጥ !..........»

ከከፍታ ነጥብ 1702 የሚመጣ አንዳችም መልስ አልነበረም ። የሙታን — የመቃብር — የጀግኖች — የቀይ እምቡጦች ዝምታ! መልስ አልነበረም ። ከፍታ ነጥብ 1702 መልስ አይሰጥም ። ጸጥ ብሎ ቀርቷል ። እንዳልኩት የሚወጣኝ እንባ አልነበረኝም ። ደርቄአለሁ ። ውስጤ ደረቅ አሸዋ — ደረቅ የማሕል አሸዋ ሆኗል ። ውስጤ እንደ ደረቁ የማሕል አሸዋ ይፋጃል ። ግን የስሜት ጠብታ አልነበረውም ። ያን ሌሊት እንቅልፍ በዓይኔ አልዞረም ። እንደ ማሕል በረሀ ደርቄ አደርኩ ።

ተስፋ ማድረግ ሰው መሆን አይደል ። ተስፋ አልቆረጥኩም። ተስፋ ሁሉ ጠፍቶ ፣ ተስፋ ማድረግ አይቀርምና ፣ ከከፍታ ነጥብ 1702 መልእክት መጥቶ እንደሆነ በማለት ወደ ራዲዮ መገናኛው ሔድኩ ። የመጣ መልእክት አልነበረም ። ብልግና ከተሞላበት ከወንበዴዎች ስድብ ሌላ ምንም እንደሌለ ራዲዮ ኦፕሬተሩ ነገረኝ ። ከማዘዣው ነጥብ ላይ ወጥቼ ፣ ታሪኩ በሰጠኝ የሜዳ መነጽር ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 ተመለከትኩ ። ታሪኩ የለም ። ግን ተራራው የታሪኩ መንፈስ መስሎ ታየኝ ። የወገን ጦር ለጊዜው ቲክሲንም ለቆ ወደ ሌላ ማዘዣ ነጥብ መንቃነቅ ጀምሮአል ። ወደኋላ የማፈግፈጉ ንቅናቄ ድርጅታዊ ቅንጅት የተሞላበትና ሥርዓት የሰፈነበት ነበር ። የጦርነቱ ፍጻሜ አልነበረም ። እንዲያውም አዲስ ጦርነት ይቀጥላል ። አሁን ወይም ነገ ናቅፋ ትወድቃለች ። ታሪኩ እዚያ አይገኝም ። ግን ታሪኩን የመሰሉ ጀግኖች ይኖራሉ ፣ ናቅፋ ይደርሳሉ ። ሁሉም ታሪኩ ናቸው ፣ እሱም እነሱን ነው ። አንድ ናቸው ። አደራ ያለኝን ኤንቬሎፕ ከፍቼ መልእክቱን ተመለከትኩት ። ከመደንገጤ የተነሳ ለትንሽ ጊዜ ልቤ ቀጥ አለ ። ትንፋሼም አጠረኝ ። ዓይኔንም ለማመን አቃተኝ ። ኤንቬሎፑ ውስጥ ከፊያሜታ ጊላይ ፎቶግራፍ ሌላ መልእክት አልነበረም ። ከደረቷ ላይ «አልተገናኘንም ፣ ደህና ሁኝ» የሚሉ ቃላት በቀይ ቀለም ተጽፈው ይነበባሉ ። «ይህች ውሻ! የውሻ ልጅ!» ከማለት ሌላ የምለው ነገር አልነበረኝም ። ሰማይ ፣ የልቤን መራራ ጩኸት ሳይሰማው አልቀረም ።



# የ ፊ ያ ሜ ታ  ጊ ላ ይ

# ደ ብ ዳ ቤ

## ም ዕ ራ ፍ  አ ም ስ ት

ውጊያ የሚደረግባቸውን ወረዳዎች ወደኋላ እየተውኩ ርቄ በሔድኩ መጠን የተኩስ ድምጽም ከጆሮዬ እየራቀ ይሔድ ነበር ። ይህን ያበደ የተኩስ ሙዚቃ ጆሮዬ ስለለመደው አንድ ነገር የጠፋብኝ ይመስል ቅር ፣ ቅር ይለኛል ። ገሀነብን ማጣት ቅር የሚያሰኝበት ምክንያት ባይገባኝም ቅሉ ። ገሀነብ ነበር ። የሚቀር ነገር ቢኖር ምናልባት ጥላቻ ብቻ ሳይሆን አይቀርም ። ባይሆን ለኔ እንደዚያ ነበረ የተሰማኝ ። ሰው ሰውን ለመግደል እንደ አውሬ ጥርሱን አግጦ ሲሮጥ ታያለህ ። ያስጠላሀል ። የሰው ስቃይ ታያለህ ። ያስጠላሀል ። የምትወዳቸውን ጓደኞችህን ድንገት ካጠገብህ ታጣቸዋለህ ። ያስጠላሀል ። ድል ታገኛለህ ፣ ግን ያንን ድል ያገኘኸው የሰው ሕይወት በማጣት ስለሆነ ያስጠላሀል ። እና በደህና ከጦር ሜዳ መመለስም ምናልባት ሳያስጠላ አይቀርም ። ሞትን አይተሀል ። ከሞት ጋር ፊት ለፊት ስትፋጠጥ እንዴት ነበርክ — ጀግና ወይስ ፈሪ? ስለራስህ ማንነት አዲስ ያገኘኸው እውቀት ያስጠላሀል ። እና ታብዳለህ ። ምክንያቱም እንዲህ ነኝ በማለት ስለራስህ የነበረህ አሳብ ይለወጥና ማን እንደነበርክና ምን እንደሆንክ ይሳከርብህና እውነታ ይጋጭብሀል ። አብደህና አካለ ስንኩል ሆነህ ትቀራለህ ። በእውነት ጦር ሜዳ የቀሩት ይሻሉ ይሆን? ሁሉንም አግኝተው ፣ ሁሉንም ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አጥተዋልና። የጦርነትን አስቀያሚ ገጽታ ዳግመኛ አያዩትምና ነው ። ከጭንቀትና ከስቃይ ባሻገር ሆነዋል ። በሕይወት ያለነውስ? ደስታና ሠላም የሰፈነበት ፣ ከጦርነት ጭንቀትና ስቃይ ነጻ ይሆነ ሕይወት የምንኖርበትን ጊዜ በመናፈቅ ተስፋ ማድረጋችንንና መሰቃየታችንን መቀጠል አለብን ። መኖር ድፍረትን ይጠይቃል ...... ግን ለመፈላሰፍ ፋታ አላገኘሁም ። ያሳክከኝ ነበር ። የለበስኩትን ልብስና ያደረ

ግሁትን ማማ ሳላወልቅ አሥር ቀን ሆኖኛል ። ደም እስከሚወጣኝ ድረስ ነበር የማከው ። እና ደግሞ የሆድ ድርቀት ይዞኝ ነበር ። ሰውነቴ ሁሉ እንደበስበሰ ፋንዶ ነበር የሚሸተው ። እከክ ፣ ድርቀት ፣ ግማት ፣ ይህም ያስጠላል ።

አፍአበት ስደርስ ጉልበቴ ከዳኝ ። ሰውነቴ ተንቆሻቁሾ ያለቀ መሆኑ የተሰማኝ እዚያ ስደርስ ነበር ። በየትኛው አቅም እንቀሳቀስ እንደነበረ አሁን ሳስበው ገረመኝ ። ምናልባት የመኖር ፍላጎት ብቻ ሳይሆን አይቀርም ሲገፋፋኝ የነበረው ። ያለ እድል ሆኖ ለእረፍት ጊዜ አልነበረኝም ። ባንድ ሰዓት ውስጥ ወደ አሥመራ መብረር ነበረብኝ ። ጋዜጠኛ ለእረፍት ያልታደለ ፍጡር ይሆን? ጊዜ የሚሰጠው ሰው የለም ። ሌሎች በሚወስኑለት ጊዜ ነው የሚኖረው ። ዜናም ቢሆን የእሱን ምቾት ጠብቆ አይደለም የሚደርሰው ። የጋዜጠኛ ሕይወት በማያቋርጥ በረራ ይመስላል ። ቢሆንም ደስ አለኝ ። ያገኘሁትን መረጃ ለኰሎኔል በትሩ ለማድረስ በጣም ቸኩዬ ነበር ።

ወደ አሥመራ የምትበረው አይሮፕላን ሰለሞን በትረን ፣ የሺጥላ ማስረኛን (ሱስ ሎቭ) እና መጽሐፈ ዳንኤልን ብቻ ነበር የምትጠብቀው ። ወንበዴዎች አፍርሰውት የሔዱት የአፍአበት ሆስፒታል ጥገና ሥራ አልቆ ስለነበረ እሱን ለማየት ነበር ያንጊት ከአሥመራ የመጡት ። ሆስፒታሉ ትንሽ ስለሆነ ቁስለኞች ድንኳን ውስጥ ነበር የሚተኙት ። የጦር ሜዳውን ምስል መልሶ አመጣብኝ ። በመቶ የሚቆጠሩ ቁስለኞች በጣር ተይዘው ያቃስታሉ ። ገና የሚመጡ አዲስ ቁስለኞችም ነበሩ ። ያፈጠጠ ቁስል ደም — የሞት ሽታ ፣ በየክፍሉ ፣ በየድንኳኑ ። ሐኪሙና አስታማሚዎቹ አሳዘኑኝ ፣ እረፍትና እንቅልፍ ካጡ ብዙ ቀን የሆናቸው ይመስላሉ ። ሐኪሙ አሁን ገና ከአፕራሲዮን ክፍል መውጣቱ ነበር ። አፕራሲዮን የተደረገው ሰው ሞቶአል ። ክፉኛ የቆሰለ ሌላ ሰው በቃሬዛ አልጋ እየተሳበ ወደ አፕራሲዮን ክፍል ይወሰድ ነበር ። ሐኪሙ ዝም ብሎ ወደ ሰሚን ይመለከታል ። በሕልም ዓለም ውስጥ ያለ መሰለኝ ። ወጣት ሐኪም ነበር ። የሚያስበውን የማውቅም መሰለኝ ። እንደ ሕይወት ያለ ውድ ነገር ማጣት ያሳዝናል ። ጦርነት ያስጠላል ..........

አፍአበት አየር ማረፊያ ስደርስ እንዳጋጣሚ እኑ ሰለሞን በትረም መጡ ። ሰለሞን አሁንም እንደቸኮለ ነበር ። የድካም



ምልክት አይታይበትም ። መጥቶ ሊስመኝ ሲል ፣ «በፈጠረህ ተወኝ» ብዬው እጄን ዘረጋሁለት ።

«ምነው?» አለኝ ።
«ፋንዶ ፣ ፋንዶ ነው የምሸተው.....»
«እምን ፣ ከሩቅ ይሰማኛል ። እባካችሁን ከዚህ ገሀነብ ቶሎ እንውጣ» አለ መጽሐፈ ዳንኤል ።

«ሁለት ሰዓት እዚህ መቆየት እንዴት አስቻለህ?!» አልኩት።
«የግድ ሆኖብኝ ። ቶሎ እንሂድ!» አለ ።

መጽሐፈ ቀልዱን አልነበረም ። ከአፍአበት ቶሎ ለመውጣት ቸኩሏል ። እንደ አፍአበት ያለ አቧራማ ቦታ ቀርቶ የጸዳ ቤትም አይመቸውም ። ለምግብ ስንቀርብ ተነስቶ ማሀኑን ካላጠበ አይበላም ። አቧራ ካየ ይጮሀል ። ጧት የለበሰውን ከሰዓት በኋላ ካልለወጠ አይወጣም ። ቀጠለና «አፍአበት የሠለጠነ ሰው የሚኖርበት ቦታ አይደለም ። እንሂድ» አለ ።

ሰለሞን ተጠጋኝና «መልእክት ትቼልህ ልሔድ ነበር ። እንኳን አገኘሁህ» አለኝ ።

«የምን መልእክት?»
«እጮኛህ አሥመራ መጥታለች.....»
«መቼ?»
«ሦስት ቀን ሆኗታል ። ቶሎ ሔደህ ገላህን ታጠብ» አለኝ ።
«መቼ ነው ወጥ ሠርተህ የምታበላኝ?» አልኩት ።
እንጀራና ወጥ በጣም አምሮኝ ነበር ።
«ጊዜ ጠፋ» አለኝ ።
«ሱስሎቭ» ወታደራዊ ካድሬዎችን ያነጋግር ነበር ። መጥቶ ሠላምታ ከሰጠኝ በኋላ ፣ «ጦርነቱ እንዴት ነበር?» አለኝ ። ስለታም ቆንጆ ፊቱ የባሰውን ተስሏል ። ቀጠለና ፣ «የጦሩ ሞራል ግለቱ ነውን» አለኝ ።

«ጥሩ ነው» አልኩት ።
«ተአምረኛ ሠራዊት እያበበ ነው ። ለዓለም ጭቁኖች ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ታላቅ ቀይ ሠራዊት ይሆ

ናል ። ናቅፋ ምንም አይደለችም ። ትግላችን ከናቅፋ ባሻገር ነው ። ሺ ናቅፋዎች ወደፊት ይጠብቁናል ። እና የምናካሂደው ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ መቀየስ ያለበት ከዚያ አኳያ ነው» በማለት ነገረኝ ።

«ጓድ ፣ እኔ አንድ ናቅፋ ካሁኑ በቅቶኛል» አልኩት ።

ያየሁትን አይቻለሁ ። ይበቃል ። ዳግመኛ የጦርነትን አስ ቃቂና አስቀያሚ ገጽታ ላለማየት ቆርጫለሁ ።

«ሱስሎቭ» ያሳብ ልዩነት የሚያናድደው ዓይነት ሰው አይ ደለም ። የሰው አሳብ አክብሮ ይቀበላል ። የራሱንም አቋም በጥሞና እያስረዳ ለማሳመን ይሞክራል ። «ማኅበራዊ ፍትሕን የሚዋጉ ኃይሎች እስካሉ ድረስ ከመታገል ሌላ ምን ምርጫ ይኖረናል? አሳብህ ጥሩ ነው ። የዓለም ተራማጅ ኃይሎች ጦርነት አይፈልጉም ። ግን ጦርነትን ለማስወገድ የምንችለው ተስፋ በመ ቁረጥ አይደለም» አለኝ ።

በመሠረቱ ልክ ነበር ። ካሳቡ ጋር ጥል አልነበረኝም ። ግን ሕይወት ካሁኑ ብዙ ስላቆሰለችኝ ነው መሰለኝ ፣ የሰው ልጅ በመሠረቱ ቅን ነው የሚለው አስተሳሰብ እያጠራጠረኝ መሄድ ጀምሮአል ። ሰው በመሠረቱ ቅን ነው የሚለውን አስተሳሰብ የሚያረጋግጥልኝ ምንም ነገር እስካሁን አላገኘሁም ።

አይሮፕላናችን ከአፍአበት ተነስታ ወደ አሥመራ መብረር ጀምራለች ። ውይይታችን ወደ ጦርነቱ አምርቷል ። መጽሐፈ ዳንኤል ነበር ፣ «ይህን ሁሉ ጦር አሰልፈን ፣ ይህን ሁሉ ዝግጅት አድርገን ፣ ናቅፋን መያዝ እንዴት ያቅተናል? ምንድነው'ኮ ችግራችን? ወይስ ከኛ የተሰወረ ነገር ይኖራል? ማነው'ኮ ይህን እንቆቅልሽ የሚያስረዳኝ?» በማለት ውይይቱን የከፈተው ። በጥ ያቄዎች ሰው መተንኮስ ይወዳል ።

ስለሞን በትረ ፣ «የዓይን ምስክር ይናገር» በማለት የመጽ ሐፉን ጥያቄዎች ወደኔ መራቸው ።

የሚያናድዱ ጥያቄዎች ነበሩ ። ስለሆነም መልስ ከመስጠት ይልቅ የስድብ ውርጅብኝ ነበር እንደመጣልኝ የማወርደው ፣



ቁጭ ብሎ መተቸት ቀላል ነው ። ማንም ተቀማጭ ሊተች ይች ላል ። ናቅፋን አሁን መያዝ እንዴት ያቅተናል? ብሎ መጠየቅ አንድ ነገር ነው ። ናቅፋን ሔዶ መያዝ ሌላ ነገር ነው ። የናቅፋን ተራሮች ሔዶ ያየ ማነው? ሔደው የሞከሩት ሞተዋል ወይም ቆስለዋል ። በተደረገው የመጀመሪያ የማጥቃት ርምጃ ናቅፋ ሳይያዝ የቀረው የወገን ጦር ጀግንነት አንሶት ወይም ሰንፎ አይ ደለም ። በሺህ የሚቆጠሩ አብዮታዊ አርበኞች ወንበዴን ሳይ ሆን የማይበገር የተፈጥሮን ምሽግ ሲጋጥሙ ወድቀዋል ፣ ደምተ ዋል ። ናቅፋ ለምን አሁን አልተያዘችም? በማለት የሚቆረቆር ሰው ካለ ፣ ሔዶ ቦታውን ረግጦ መሞከር አለበት ። ያኔ ነው የአብዮታዊው ሠራዊት ወኔና ጀግንነት ፣ ተጋድሎና መስዋእት ነት ፣ ጥንካሬና ሞራል በውል ሊገባው የሚችለው ። የምን እን ቆቅልሽ! የምን ምስጢር! የናቅፋ ውጊያ የተሰወረ ምስጢር የለውም ። ተፈጥሮ በሰው ወኔ ላይ ስታምጽ ምን ይደረጋል! ሰማይ አይቧጠጥ ወይም ይህ ጀግና ሠራዊት ራሱን ለእልቂት እንዲዳርግ አይደረግ! እኮ ምን? አሁን ያለው አማራጭ አንድ ብቻ ነው ። የጠላትን መውጫና መግቢያ ነጥቦች አንድ በአንድ በቀስታ ፣ ግን በእርግጥ እየዘጉና ቀስ ብለው እየከበቡ ፣ የከበባ ውን ቀለበት እያጠበቡ ፣ እያጠበቡ ሔደው በመጨረሻ ፍልፈሎ ቹን መደበቂያ ጎሬአቸው ውስጥ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አጋ ይቶ ማስቀረት ። ሌላ አማራጭ የለም ። ጊዜና ትእግሥትን ይጠ ይቃል ። ግን የናቅፋ መውደቅ እርግጥ ነው ። ጊዜው ሩቅ አይ ደለም ። እስከዚያ ድረስ ኢኮኖሚያችን ይደማ ይሆናል ። አሁንም እየደማ ነው ። ታዲያ ምን ይሁን ! ያገር ሕልውና ከሌለ ኢኮኖሚ ምንድነው! ለማነው? ጦርነትን አልወድም ፣ ያስጠላኛል ። ከሆነ ልኝ ዳግመኛ ላየው አልፈልግም ። ግን ፣ ጦርነትን በሰው ልጆች ላይ የሚጋብዙ ጥፋተኞች እስካሉ ድረስ መቀጣት ይኖርባቸዋል ። ይቀጣሉም ። አመጽ በአመጽ ብቻ ነው የሚፈታው ። ከናቅፋ ተራሮች ላይ የጀግኖች ደም ይጮሃል!...... አሁን እሰማዋለሁ...... እሰማዋለሁ...... አይሮፕላኗ አሥመራ ደርሳ ባታርፍ ኖሮ ንግግሬን እቀጥል ነበር ።

ጧት ረፋዱ ላይ ነበር አሥመራ የደረስነው ። አየሩ ይወ ብቃል ።

ከአይሮፕላኗ ስንወርድ ፣ «ግን አንድ ነገር ልንገርህ» አለኝ ። «ሱስሎቭ» ።

«ምንድነው?» አልኩት ።
«በሰው ልጅ ላይ ተስፋ አትቁረጥ ። ያለው የመጨረሻ ተስፋ ምናልባት እሱ ብቻ ነው» አለኝ ።
«በሰው ልጅ ላይ ያለኝን እምነት የሚያጠናክርልኝ ነገር ባገኝ ደስ ይለኝ ነበር ። እስካሁን ያየሁት ግን እምነቴን የሚንድ እንጂ የሚያጠናክርሆና አላገኘሁትም» ብዬው ሔድኩ ።

ገና ቤት ከመድረሴ ለኰሎኔል በትሩ ስልክ ደወልኩ ። ስልኩን ያነሳው ጸሐፊው ነበር ።
«ጓድ ኰሎኔልን ነበር የምፈልገው ። ጸጋዬ ኃይለ ማርያም እባላለሁ ። ለአስቸኳይ ጉዳይ ነው.....»

«ምጽዋ ሔደዋል..........»

ወይ አጋጣሚ! ለብርቱ ጉዳይ በፈለኩት ቁጥር ከከተማ የመጥፋቱ ነገር አስገረመኝ ።

«መቸ?»
«ዛሬ..........»
«መቸ ይመለሳል?
«ዛሬ ማምሻውን.....»
«እዚያ የሚገኝበትን ስልክ ልትሰጠኝ ትችላለህ.....»
«አልታዘዝኩም..........»
«እሺ አንተ ደውለህ ልትነግረው ትችላለህ? የሞትና ሽረት ጉዳይ ነው..........»
«ምን ብዬ?»
«ጸጋዬ ኃይለማርያም በጣም ላስቸኳይ ጉዳይ ይፈልግሃል ብለህ ።»
«እሺ እሞክራለሁ ።»

የሞቀ ውሀ ውስጥ ገብቼ ከመነከር ሌላ የሚታየኝ ነገር አልነበረም ። ውሀን የፈጠረ አምላክ! እያልኩ በደስታ ዋኘሁ ። የጦርነትን ኃጢአት ከላዬ ላይ እጥቤ እንደማወጣ ያህል ነበር ሰውነቴን የማሸውና የምፈትገው ። ፊያሜታ ጊላይንም እንደ ቆሻሻ ነገር ከላዬ ላይ እጥቤ አወጣኋት ። ስላታለለችኝ በልቤ ውስጥ ያደረው ጥላቻ ነፍስ ዘርቶ ሲገላበጥ ይሰማኛል ። በዚህ ዓለም ማንን ማመን ይቻላል? እና ሰው በመሠረቱ ቀና ነው የምን ለውስ እንዴት ነው? እያልኩ አስብ ነበር ። የሱስሎቭ ምክር እልዋጥህ አለኝ ። ዛሬ ለመጨረሻ ጊዜ እያታለሁ...... ፎቶግራፏን እሰጣታለሁ...... እና ደህና ሁኚ እላታለሁ ። ከዚያ በኋላ ይህችን ውሻ ዳግመኛ ባይኔ አላያትም ...... ብዬ ወሰንኩ ። በሮሚ መምጣትም ዕድሌን አመሰገንኩ ። ሁልጊዜም ቢሆን እድለኛ ነበርኩ ። አሁን ሳስበው ሕይወትን ይህን ያህል የማማርርበት ምክንያት የለኝም ፤ ሕይወት ይህን ያህል አላንገላታችኝም ። ሮሚ ልክ በጊዜው በመምጣቷ ደስ አለኝ ። ሕይወት አስባ ስትክስ ደስ ይላል ። ሮሚ የት እንዳለች የነገረኝ የለም ። እና ተነስቼ ለረዛን ደወልኩላት ።

«መቸ መጡ!» አለች ረዛን ።
«ካንድ ሰዓት በፊት ። ሥራው እንዴት ነው?»
«ኰሎኔል በትሩ ተሰማ ብዙ ጊዜ እልመጣም ወይ እያሉ ጠይቁኛል..........»
«ሌላስ?»
«ወይዘሪት ሮማን የሚባሉ ብዙ ጊዜ ይደውላሉ.....»
«አድራሻዋን ነግራሻለች?»
«አዎ ፤ ከረን ሆቴል ። ቁጥር 19፤ስልክ ቁጥሩን ይፈልጋሉ?»
«ግድ የለም ።»

ወደ ፊያሜታ ጊላይ ደወልኩ ። ስሜን ስትሰማ ተደናገጠች ። አሳቧም ፤ ድምጿም ተሰባበረብኝ ።

«ምነው ጠፋሁሽ?» አልኳት ።
«እደውልልሀለሁ ስል ደወልክልኝ» አለች በሚሰባበር ድምጽ ።
«መምጣቴን እንዴት ዐወቅሽ?»
ዝም አለች ።
«ምን ሆነሻል?»
«ምንም»
«ዛሬ ማታ የት ላግኝሽ?»
ቶሎ መልስ አልሰጠችኝም ። ቆየችና «ናቅፋ እንዴት ነው?» አለችኝ ።

«ምነው? ደህና ነው» አልኳት ።
«አልሆነላችሁም ይባላል.....»
«የጊዜ ጉዳይ ነው ። አንድ ቀን ይሆናል ።»
ካንገት በላይ ሳቅ ሳቀችና ፡ «ይመስልሀል?» አለችኝ ።

«እርግጠኛ ነኝ ። ለምን እንደምትጠሉን አይገባኝም? ቢሆ
ንም ፍቅር በመጨረሻ ማሸነፉ አይቀርም ። ምን ጊዜም ቢሆን
በጥላቻ የሚመራና በአታላይነት የሚኖር ሰው ወይም ኃይል
በመጨረሻ ይወድቃል ። የናቅፋ ተራራዎች እንደደበቁት አይ
ቀሩም» አልኳትና ወደ ጥያቄዬ ተመልሼ «ላገኝሽ እፈልጋለሁ ።
ጉዳይ አለኝ ። በስንት ሰዓት ላግኝሽ?» ብዬ ጠየኳት ።

«እጮኛህን የት ጥለህ?» አለችኝ ።
«መምጣቷን ሰምተሻል?»

«አዎ ፡ አሥመራ ትንሽ ከተማ ናት ። የምትደብቀው ነገር
የላትም» ብላ ፡ አሁንም ካንገት በላይ የሆነ ሳቅ ሳቀችና ፡ «አይ
ቻታለሁ ። ቆንጆ ናት አባቴ ይሙት ። ግን ሁለተኛ አታየኝም ።
ለምን ታየኛለህ?» አለችኝ ።
እልክ ይሁን ወይም ንዴት ጉሮሮዬን እየተናነቀው ፡ «አን
ቺን ለማየት የምፈልግበት ጉዳይ አለኝ» አልኳት ።
ፎቶግራፉን ሰጥቻት ፡ ደህና ሁኚ ብዬ ከእሷ ላንዴና ለመ
ጨረሻ ጊዜ ከመለየት ሌላ የምፈልገው ነገር አልነበረኝም ።
እንደተጫወተችብኝ እንድትቀር አልፈለኩም ። ባሳቤ ሰው
ለመጉዳት አይሆንልኝም ። ከመጣብኝ ግን ሰይጣን ነኝ ። አንዳ
ንድ በቅርብ የሚያውቁኝ ሰዎች በዚህ የተነሳ ለዘብተኛ ሠይጣን
ይሉኛል ። በዚህ ዓለም ላይ ሁሉ እኩል አታላይና ራሱን ወዳድ
እንዳልሆነ ማወቅ አለበት ፡ በሰው ንጹሕ ስሜት እየተጫወተች
የምትኖር ፡ ይህችን ውሽ ትምህርት ማስተማር አለብኝ ብዬ
ነበር የተነሳሁት ። በስልክ ልነግራት እችል ነበር ። ግን ፡ የጎዳ
ችኝን ያህል ልጎዳት ፈለኩ ። ይሁን እንጂ ፡ ከጥፋቷ የሚማር
ልብ ይኖራት ይሆን? አጠራጠረኝ ። ልቤ ናቅፋ ተራራ ባይሆን
ኖሮ መቸ እንዲህ ጉድ ትሠራኝ ነበር? ኰሎኔል ታሪኩን አስታወ
ስኩት ። መላ ሰውነቴን ዘገነነኝ ። ምን ሊያስተምረኝ ፈልጎ
ይሆን ፎቶግራፏን የሰጠኝ ? ብዬ አሰብኩ ። እሱ ሞቷል ፡ አርፏ
ዋል ። እኔ እሰቃያለሁ ።

«በኋላ እደውላለሁ» አለችኝ ።
«መቼ?»
«ከአምስት ደቂቃ በኋላ..........»
«ጊዜ የለኝም ። ለምን አሁን አትነግሪኝም?»
«እጮኛህን ለማየት ከቸኮልክ ሂድ! ከረን ሆቴል ናት»
አለች ።
«እሺ ይሁን! አምስት ደቂቃ» አልኳት ።

ምን ለማድረግ እንደፈለገች ባይገባኝም ቅሉ አምስት ደቂቃ
ጠበኳት ። እውነትም ከአምስት ደቂቃ በኋላ መልሳ ደወለችልኝ ።

«አንድ ሰዓት ላይ ኒያላ አካባቢ ጠብቀኝ» አለችኝ ።

ወደ ከረን ሆቴል ከመሔዴ በፊት በቪያ ፓራዲዞ አድርጌ
በፓራዲዞ ቡና ቤት በኩል አለፍኩ ። ቡና ቤቷ እዚያው ነበረች ፡
የትም አልሔደችም ። ኰሎኔል በትሩን በማጣቴ ልቤ ተንጠለጠለ ።
ወደ ከረን ሆቴል በቀጥታ ሔድኩ ። ሻለቃ ተክላይ ዘድንግል
ቡና ቤቱ ውስጥ ያንገዋብብ ነበር ። ከላይ እስከ ታች ባለመስመር
ጥቁር ልብስ ለብሶ ሽክ ብሎአል ።

«ግብዣ አለብህ እንዴ?» አልኩት አለባበሱን እያደነቅሁ ።
ባናውቀው ነው እንጂ ሕይወት ሁልጊዜ እንደጋበዘችን
ነው» አለኝ ።
«እዚህ ምን የሚታደን ነገር አገኘህ?»
«ማ! ኮሜ ቤላ!» ብሎ ጣቶቹን ሳመና ፡ ከአዲስ አበባ
በቅርብ ቀን የመጣች ጽጌረዳ የምትመስል ፡ ቆንጆ ልጅ ቁጥር
19 መኝታ ክፍል የምትገኝ መሆኗን ነገረኝ ።
«እውነት?» አልኩት ።
«መኝታ ቤቷ ውስጥ ተቆልፋ ምን እንደምትሠራ አላውቅም
ግን በእውነት ኃጢአተኛ ናት» አለኝ ።

«ለምን?»

«ያንን የመሰለ ውበት መደበቅ ኃጢአት ነው» ብሎ ፡ ክራ
ቫቱን አስተካከለና ፡ «አሊቃዬ በጣም ይፈልግህ ነበር» ሲል
ነገረኝ ።

«ከኔ ምን ይፈልጋል?»
«አላውቅም ። ግን ይፈልግሀል ..........»
«ሥራ እንዴት ነው?» ብዬ ጠየኩት ።

የገቢ ሊሉኝ ፈልጎ ነበር ። ሮሚን ለማየት ቸኩዬ ነበርና ግብዣውን እምቢ አልኩት ። ወደ አንድ ጥግ ጐትቶኝና ድምጹን ዝቅ አድርጎ ፣ «ብትጠነቀቅ ጥሩ ነው» አለኝ ።

«ምነው?»
«ለግድያ እንደምትፈለግ ደርሰንበታል..........»
«ለምን? ማነው እኔን ለመግደል የሚፈልገው?»

ቀስ ብሎ ማፍ ማፉን ነገረኝ ። አሮማይ የሚባል የወንበዴዎች ኅቡዕ ድርጅት ተቋቁሟል ። የአሮማይ ዓላማ ፣ የወንበዴዎችን የመጨረሻ ምሽግ ለመደምሰስ የሚደረገውን ንቅናቄ መግታት ፣ የወገን ጦር ባለበት ቦታ ሁሉ ድንገተኛ ወረራ በመክፈት ማበሳጨት ፣ የጦሩን የስንቅና የትጥቅ መንገዶችን መዝጋትና እንዳመቹ አደጋ መጣል ፣ መገናኛዎችን መቁረጥና መጥለፍ ፣ እንደዚሁም አጥፍቶ የሚጠፋ ጓድ በማሰማራት በሰውና በንብረቶች ላይ ጉዳት ማድረስ ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የክፍለ ሀገሩን ሕዝብ ከፍተኛ ውዥንብር ላይ መጣል እንደሆነ ከነገረኝ በኋላ ፣ «እንዳልኩት አንተ አንዱ ኢላማቸው ስለሆንክ መጠንቀቅ አለብህ ። ይህን ሁሉ ለማወቅ ችለናል ። አሁን ያቃተን ነገር ቢኖር «ሴላቸውን» ማግኘት ነው ። በተጠጋን ቁጥር ፍንጩን ያጠፉብናል ። ሰዎች ድንገት ሞተው ይገኛሉ ፣ ወይም ደርሰንባቸው ስንል ራሳቸውን ያጠፋሉ ። በውስጥ የዘረጉትን መረብ ካልበጣጠስነው ፣ በጦር ሜዳ የምናካሂደው ፍልሚያ ሊሰምር አይችልም ። የሴላቸው መረጃ የለም» አለኝ ።

«ሴላቸውን ማግኘት አሁን ቀላል ሳይሆን አይቀርም» አልኩት ።
«እንዴት?
«በተአምር» አልኩት ። ልነግረው አልፈለኩም ።
«ሴላቸው» ያለበትን ቦታ የሚጠቁመን ሰው ብናገኝ ሚሊዮን ብር እንከፍለዋለን ። አሮማይ ብቻ አይምሰልህ ። ቢሮክራሲ



የሚባል አካል እንዳላቸውም እናውቃለን ። ችግሩ ፣ ማን? የት የሚለው ጥያቄ ነው» አለኝ ።
«ሥዕላይ አለ ወይ? » ብዬ ጠየኩት ።
«አለ ። እሱን መከተል ጥላ እንደማባረር ነው» አለኝ ።
«ፓራዲዞ ቡና ቤት ደህና ነው?»
«ለምን ጠየከኝ?»
«ጥሩ ቡና አምሮኝ ነው»
«ወስጄ ልጋብዝህ..........»
«አመሰግናለሁ ። ሁሉም ነገር ሠላም ነዋ? » አልኩት ።
«አትስጋ ። ከተማዋ በቁጥጥራችን ሥር ናት ። ወደ ግባችን እየተቃረብን ነው ። መቼ? የት? አላውቅም ። ብቻ አንድ ነገር ከቅርብ ይሸተኛል» አለኝ ።

«ኰሎኔል በትሩ ከምጽዋ እንደተመለሰ ሚሊዮን ብር አዘጋጅተህ ጠብቀኝ በለው ። እመጣለሁ ። አሁን 19 ቁጥር የምትጠብቀኝ ልጅ አለች ። ቸኩያለሁ» አልኩት ።

በሁለቱም ጉዳዮች አላመነኝም። የምቀልድ ነበር የመሰለው፣ እዚያው ትቼው ወደ ፎቅ ወጣሁ ። ሮማን ድምጼን ባትሰማ ኖሮ በሩን አትከፍትም ነበር ። በናፍቆት ከተሳሳምን በኋላ ፣ «እክፍልሽ ውስጥ ተዘግተሽ ምን ታደርጊያለሽ?» አልኳት

«ሆ! ምን ዓይነት አገር ነው ልጄ!» አለች ።
«ምነው?»
«ወንዱ በመንገድ አያስኬድም ። በዓይናቸው ቀሚሴን ሲያወልቁ ይታዩኛል » ብላ ፣ በናፍቆት ዓይን ስትመለከተኝ ከቆየች በኋላ ፣ «ከስተሀል ፣ ጠቁረሀል» አለችኝ ።

«ልክ ነሽ ፣ እረፍት ላይ አልነበርኩም» አልኳት ።
«ሺ ሰማንያ ኪሎ ሜትር አጣርሬ ያዝኩህ አይደለም?» አለችና ቀጥላ ፣ «መቼ ነው ይህ ዘመቻ የሚያልቀው?» ብላ ጠየቀችኝ ።

«እንጃ ፣ በእውነት አላውቅም ።....»
«ማጣ ነው እቴ ። በኔ ላይ የመጣ ፍርጃ ሳይሆን አይቀርም» አለች ።

ከሆቴሉ ወጥታ እኔ ካለሁበት ቤት ውስጥ እንድታርፍ አግ ባባኋትና ስመሔድ ተነሳን ። የሆቴሉን ሂሣብ ስመክፈል ስን ሔድ ተክላይ ዘድንግልን አየሁት ። ሮሚን ወስጄ ፣ «ተክላይ ይባላል ። ጓደኛዬ ነው ። ሮማን እጮኛዬ ናት» በማለት አስተ ዋወቅኋቸው ።

ሮሚ ስታየው ደስ አላላትም ። እሷ ዞር ስትል የሌባ ጣቱን ቀስሮ የቀልድ ዛቻ ዛተብኝ ። መኪና ውስጥ ከገባን በኋላ ፣ «ምን ጓደኛዬ ነው ትላለህ? አላስገባ ፣ አላስወጣ እያለ እንዲሁ መከራዬን ሲያበላኝ ነው የከረመው» አለች ።

«ተይው ። ደህና ልጅ ነው ። ቢመኝስ ምናለበት? ውብ ነሽ ። እሱም ሸጋ ነው ። ለክፋት ብሎ አይደለም ። ሕይወትንና ሴቶችን ይወዳል ። ምናለበት?» በማለት አጽናናኋት ።

«ገነት ውስጥ አይደለም እንዴ ያረፉችሁት?» በማለት ግቢውንና ቤቱን አደነቀች ። ግቢው በልዩ ልዩ አበባዎችና ሐረጎች ፣ ጥዶችና ዘምባባዎች የጌጠና የተዋበ ነበር ። ክፍሎቹም በጣም ያማሩና ምቾት ያላቸው ነበሩ ። ዘመቻ እንዲህ ከሆነ መቆየቱ ምን ይከፋል?» አለችና ሻንጣዋን ሳትፈታ መኝታ ቤቱን ማስተካከል ጀመረች ። የተዝረከረከ ነገር ማየት አትወድም ። ልብሶቼም ፣ ጫማዎቼም ፣ እግር ሹራቦቼም በየቦታው ተጥለው ይታያሉ ።

አንድ የቴፕ ክር አንስታ ስትመለከት አየኋት ። ቴፕ ክሩን መሬት እንደጣልኩት እዚያው እረስቼው ነበር ። ምንም ለማድረግ አልቻልኩም ። አሁን ነገሩ ዘግይቷል ። ከጁዋ አልቀ ማው ነገር! ራሴን ረገምኩት ። ፈያሜታ ጊላይ የሰጠችኝ ክር ነበር ። ስሟ ተጽፎበታል ። የሮማን ፊት በቁጣ ሲቀላ አየሁት ። ምን ለማለት ወይም ምን ለማድረግ እችላለሁ? ዝም ብዬ ቆሜ ቀረሁ ። ሬዲዮ ቴፑን አስነስታ ዘፈኑን ማዳመጥ ጀመረች...... ግጥሙን በቃሌ እወጣዋለሁ ። የኩኩ ዘፈን ነበር ። ምናልባት መቶ ጊዜ ሰምቼው ይሆናል ።

«ከሰው የተለየህ ፣ እኔ ምን አውቃለሁ?
እኔ ምን አውቃለሁ



ሳይህ ደስ ይለኛል ስላንተ አስባለሁ
ስላንተ አስባለሁ
አመመኝ ደከመኝ አጣሁ መድኃኒት
ፍቅርህ አስጨነቀኝ እንደ ልብ ውጋት
መውደዱ ከሆነ እኔ አንተን ማየቱ
ልቤ ከተሰማው የፍቅርህ ግለቱ
ገረመኝ እራሴን ሳየው ሁኔታዬን
አንተም እንደኔው ነህ ፣ ወይ እኔ ብቻዬን?
ወዳንተ እያደላ እምቢ አለኝ ተው ብለው
ነጋ ጠባ አንተን ነው የሚያሰላስለው
ልቤ ተቀልፎ ያስባል ለብቻው
ለምወደው ልጅ ግን ያውና መክፈቻው......

ክሩ ላይ ሌላ ዘፈን አልነበረም ። «ጥሩ የፍቅር ዘፈን ነው» አለች ።

ጠጉሬን አክኬ ዝም አልኩ ። ሮማን ተናዳ ጉንጮቿ ሲቀሉ የፈካ ጽጌረዳ አበባ ትመስላለች ።

«ፈያሜታ ጊላይ ማን ናት?» አለች ።

ምን መልስ እንደምሰጣት አጥቼ አሁንም ዝም ብዬ ቀረሁ ። ሻንጣዋን ይዛ ብድግ አለች ።

«የት ልትሔጂ ነው?» ብዬ ሻንጣውን ያዝኩባት ።

«የኔ ወንድም ተወኝ ልሒድበት..........»

«የሆነውን ሁሉ አስረዳሻለሁ ። ዕድል ስጪኝ ፣ እባክሽ» በማለት ልመና ገባሁ ።

«ምንም የምታስረዳኝ ነገር የለም ። ተወኝ!» አለች ።

«እባክሽ ሮሚ ስሚኝ..........»

«ይህንኑ ነበር የፈራሁት..........»

«ምን?»

«አንተ የደረስክበት ቦታ ሁሉ ቤትህ ነው ። በደረስክበት ትለምዳለህ ። መጥኔ እቴ ። ግን አንተ ምን ታድርግ? እኔ ነኝ ቅሌታሟ ። በራሴ ነው የማዝነው ። ባንተ አይደለም......»

«ያለፈው አልፎአል ። አልሰማ አልሺኝ እንጂ አሁን እነግ ርሽ ነበር ። ልጅቷ ወስላታ ነች ። አዝናለሁ ። እባክሽን ሮሚ ፣

ይቅርታ አድርጊልኝ ። ልለምንሽ ። አትሒጅ» በማለት ለመንኳት ሁሉንም ነገር እዚያው ልናዘዝላት ፈልጌ ነበር ።

ልመናዬን አልሰማችም ። «ተወኝ ነው የምልህ! አለዚያ ውርደት ይከተላል! » ብላ የባሰውኑ አፈጠጠችብኝ ።

ግራ ገብቶኝ ራሴን ይዤ ቆምኩ ። የማደርገው ነገር ጠፋኝ ። ንዴት ጉሮሮዬን አነቀኝ ። ከዚህ በላይ መለማመጥ ደግሞ አልሆነልኝም ፤ አይሆንልኝም ። ሴቶች አለ በቂ ምክንያት ሲነጣነጩብኝና አልሰማ ሲሉኝ ቶሎ ግልፍ ይለኛል ። ከዚያ በኋላ መለማመጥ ፈጽሞ አይሆንልኝም ። ሴቶች በመሠረቱ የሚለማመጣቸውን ወንድ ይወዳሉ መሰለኝ ፤ ዝም ብዬ ስተዋቸው ብዙ ሴቶች ፣ እሱ አረመኔ ነው ፣ ጨካኝ ነው የሚል ስም አውጥተውልኛል ። እንኳን በድለው ይቅርና ሴት በድላም ብትሆን መካስ ትወዳለች ። እኔ ግን እንዲህ አይደለሁም ። ከሴት ጋር እልከ መግባትም አልወድም ። የማታዳምጠኝ ከሆነ ጥያት መሔድ ብቻ ነው የማውቀው ። አዎ ፣ ሮማንን በድያት ይሆናል ፣ ግን ለምን አታዳምጠኝም! ለምን አይገባትም!

«ከፈለግሽ ልትሔጂ ትችያለሽ!» ብዬ መንገዱን ለቀቅሁላት።

ሻንጣዋን አንጠልጥላ ወጣች ። ግድግዳውን በቡጢ አልኩትና ተከትያት ወጣሁ ።

«እሺ ፣ መሔዱንስ ሒጂ ። የት ነው የምትሔጂው? ላድርስሽ» አልኳት ።

«አልፈልግም ራሴ እሄዳለሁ..........»

«እባክሽ ሮሚ ፣ አሁን ባታስቸግሪኝ ምናለበት?»

«እኔ የማስቸግር ሴት አይደለሁም ። ታክሲ ሞልቷል ። አትቸገር» ብላ መንገዷን ቀጠለች ።

በሠላም ተውኳት ። ሜዳ ላይ ግብ ግብ ልገጥማት አልችልም። በሠላም እንድትሔድ ከመተው ሌላ ምን ማድረግ እችላለሁ? እንደ እሳት እየነደድኩ ቆሜ ቀረሁ ። ባንድ ፊት ሮማን እንዲህ ጨክና አውላላ ሜዳ ላይ ጥላኝ ትሔዳለች ብዬ በልቤ አላመንኩም ። ተከትያት እንዳልሔድም እልከ ያዘኝ ። ሰው የሚጣላበትና የሚለያይበት ጥቃቅን ምክንያቶች አናደዱኝ ። አዘንኩኝ ። ሰው ቢደማመጥ አሁን ምናለበት? ከስንቱ ስቃይና ስጋት ራሳችንን ከደን ነበር!.......... እና ፊያሜታ ጊላይን ከልቤ ረገምኳት ።



ሞኝ በመሆኔም ራሴን ጠላሁት ። ለመጮህም ሆነ እንባ አውጥቼ ለማልቀስ አልቻልኩም ። መፈንዳትም አልሆነልኝም ። እንዲህ ሲኮን ምን ይሰማል? እንደተጠመደ የጊዜ ቦምብ ትር ፣ ትር ሲሉ ከመዋል ሌላ ምን ይደረጋል? ልትፈነዳ ትፈልጋለህ ፣ ግን አትፈነዳም ። ንዴቴንና ቁጭቴን ፊያሜታ ጊላይ ላይ ለመወጣት ፈልጌ ነበር ። ሔጄ እሷ ላይ ከመፈንዳት ሌላ ምኞትና አሳብ አልነበረኝም ። ኰሎኔል በትሩ ቢሮ አሥሬ ይሆናል ስልክ የደወልኩት ። ከምጽዋ አልተመለሰም ። ያገኘሁትን መረጃ ልነግረው አሁን በቸኮልኩበት ጊዜ እሱን በማጣቴ ነደደኝ ። ከመረጃው ጋር የምሞት ወይም የምፈነዳም መስሎ ተሰማኝ ። የተረገመ እድል! እንደምንም መሸልኝ ። እንደዚያን ቀን ጊዜ ረዝሞብኝ አያውቅም ።

ኒያላ ሆቴል አካባቢ ፊያሜታን መጠበቅ ጀመርኩ ። አንድ ሰዓት ሆነ ። ቀጠሮ አክባሪ ነበረች ። ግን በቀጠረችኝ ሰዓት አልመጣችም ። ደቂቃዎች አለፉ ። ደቂቃዎች መጡ ። ሴቶችን አምስት ደቂቃ መጠበቅ ግዴታ ነው ፣ ይገባል ። አሥር ደቂቃ መስጠት ጨዋነት ነው ። ከዚያ በላይ መቆየት ግን ሞኝነት ነው የሚል መርሆ ቢኖረኝም እንደሞኝ መንገድ መንገዱን እያየሁ ጠበቅኳት ። አንድ ሰዓት ከሐያ ደቂቃ ሆነ ፊያሜታ ባገሩም የለችም ። አሁንም ተስፋ አልቆረጥኩም ። በተጨማሪ አሥር ደቂቃ ያህል ጠበኳት ። አሁንም አልመጣችም ። ይቺ ውሻ ነቅታብኝ ይሆናል የጠፋችው ፣ ቆይ ግድ የለም በማለት እየዛትኩና እየተናደድኩ ሮማንን ፍለጋ ወደ ክረን ሆቴል ሔድኩ ። ከሮሚ ጋር ለመታረቅ የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ፈልጌ ነበር ፤ መቸም ጊዜ የማይለውጠው ነገር የለም በማለት አንዳችን የግድ የልብ ኩራታችንን ውጠን ካልተሰበርን ፍቅራችን ይበጠሳል ። ለፍቅር ማጎንበስ ያስፈልጋል ። እኔና ሮማን ስንጣላ የመጀመሪያ ጊዜአችን አይደለም ። አንድ ጊዜ ተጣልተን የተኳረፍንበት ሁኔታ ከሁሉም ትዝ ይለኛል ። ጠጉር ሠሪ ቤት ወስጃት ነበር ። በተባባልነው ሰዓት ተመልሼ ልወስዳት አልቻልኩም ። በጣም ዘገየሁባት ። አጣዳፊ ሥራ ነበረኝ ። ወንድ ልጅ ብዙውን ጊዜ የራሱ ጊዜ የለውም ። ልወስዳት ስመጣ አኩረፈችኝ ። አንድ ግብዣ ላይ መገኘት ነበረብን ። መኪናዬ ላይ አልወጣም አለች ። ብላት ፣ ብሠራት አሻፈረኝ ብላ ቀረች ። «ታዲያ ለዚህ ከሆነ መጀመሪያውኑ እስካሁን ለምን ጠበቅሺኝ!» አልኳት ።

«እንጃልህ!» ብላ ታክሲ ይዛ ጭልጥ አለች ። በጣም ስላና
ደደችኝ ለሣምንት ያህል ጠፋሁባት ። የትግል ሣምንት ነበር ።
ከልቤ ጋር ስሚገት ጥርሴን ነክሼ ሣምንቱን አሳለፍኩት ። ቅዳ
ሜ ማታ ስልክ ደወለችልኝ ። ያለችኝ ሁሉ ትዝ ይለኛል......
«አንተ ኩራተኛ አሰህ? ዛሬ ከቤት ባጣህ ኖሮ ዳግመኛ አልደው
ልም ነበር ። ጨካኝ ። መጥፎ ጨካኝ ነህ......እሺ እኔስ ካንተ መኪና
ላይ አልወጣም ብዬ ታክሲ ይዤ ልሒድ ። ይገባኛል ። አንተ
ተከትለኸኝ እንዳትመጣ ያደረገህ ነገር ምንድነው? ቤቴን ታውቀ
ዋለህ ። ኩራት ፤ ንቀት ፤ እብሪት ነው ያስቀረህ አይደለም? ስለ
ቤት ምኑም ነገር አይገባህም ። የቤት አያያዝ አታውቅም ። ፍቅር
ምን እንደሆነ አይገባህም ። በእውነት የምትገርምና የምታሳዝን
ፍጡር ነህ......»

ተመሳሳይ የሆነ ጥፋት በመድገሜ ራሴን ታዘብኩት ።
ልሒድ ብላ በተነሳችበት ጊዜ በግድ ይዤ ማስቀረት ነበረብኝ።
ዝም ብዬ መልቀቅ አልነበረብኝም ። ያውም በማታውቀውና
አስታራቂ በሌለበት አገር ።

ሮማን ከረን ሆቴል አልነበረችም ። ወደዚያ እንዳልተመ
ለሰች ተነገረኝ ። የት ገብታ ይሆን? በማለት ኒያላና እምባሦይራ
ሒጄ ጠየኩ ። ሁለቱም ቦታ አልነበረችም ። ሌሎች ሁለት ሆ
ቴል ቤቶች ሞከርኩ ። የትም አልነበረችም ። ሌላ የማደርገው
ነገር አልነበረኝም ። ተስፋ አልቆረጥኩም፤ ምናልባት ወደ ቤት
ተመልሳ ይሆናል በማለት ወደ ቤቴ አመራሁ ።

ግቢውን ከሚጠብቁት ወታደሮች አንዱ በኢንቬሎፕ
የታሸገ ወፍራም ደብዳቤ በሩ ላይ ሰጠኝ ። ስምና አድራሻ አልተ
ጻፈበትም ። የሮማን ደብዳቤ መስሎኝ ይዤ ወደ መኝታ ቤቴ
ገባሁ ። የፊያሜታ ጊላይ ደብዳቤ ነበር ። ወረቀቱ ወጥ ወጥ
ይሸታል ። ገረመኝ ። ፊያሜታ የነካችው ነገር ቀርቶ ያለፈች
በትም መንገድ ሽቶ ሽቶ ነበር የሚሸተው ።

«ጺጋዬ ፤ ይህ የመጨረሻ ቃሌ ነው ። የተገናኘንበትን ቀን
እረግመዋለሁ ። ቀይ ኮከብ ነው ጉድ የሠራኝ አባቴ ይሙት ።
ቀይ ኮከብ አንተን ባያመጣብኝ ኖሮ ጣጣ ውስጥ አልገባም ነበር ።
እኔ የተፈጠርኩት ለደስታ ነው ብዬህ የለም? ቀይ ኮከብ አንተን



ባያመጣብኝ ኖሮ ደስ ካለኝ ወንድ ጋር እየገባሁና እየወጣሁ በደ
ስታ እኖር ነበር ። አሁን ግን ደስታ የለኝም ። ደስታን አጥቼ
ዋለሁ ። ሕይወት ስቃይ ሆናብኛለች ፤ ዕድሜ ላንቴ ። ስካሮኛ
ነህ አባቴ ይሙት ።

«አሁን ሳስበው አንተን ከማወቄ በፊት ያሳለፍኩትም ሕይ
ወት የደስታ ጊዜ ነበር ለማለት አልችልም ። የምወደውና የሚ
ወደኝን ልጅ ስፈልግ ነበር የኖርኩት ። እንዳጋጣሚ አንቴን አገ
ኘሁህ ፡ ያለ ዕድል ሆኖ አጣሁህ ፤ ወይም ላጣህ ነው ።

«ለምን ወደድኩህ? የሚያከብረኝ ፤ የሚግባባኝና የሚወደኝ
ወንድ ስፈልግ ኖሬአለሁ ። አንተ ሦስቱንም ታሟላለህ ። የራስ
ከን ደስታ ብቻ በማሰብ ወደ መኝታ የምትጎትተኝ ሆነህ አላገኘ
ሁህም፡ እንደሌሎቹ የመሐል አገር ወንዶች የቱሪስት ጠባይ የለህ
ም ። ወደድኩሽ ፤ ሞትኩልሽ ሲሉ ከርመው በመጨረሻ መሔጃ
ቸው ሲቃረብ ይክዱሀል ። አባቴ ይሙት ባለጌ ናቸው ። አይገር
ምም ። ድሮውንም ከቱሪስት ምን ይጠበቃል ። አንተ ግን እንደሱ
አይደለህም ። ስለሆነም ፤ ካንተ ጋር ስሆን መላ ሰውነቴ ይዝናና
ናል ። ነፍሴ በደስታ ባሕር ውስጥ ትዋኛለች ። የምደብቅህ
ወይም የምቆጥብብህ ነገር የለኝም ። ካንተ ጋር ስሆን ሰውነቴን
እረሳዋለሁ ። ይሉኝታ የለኝም ። እፍረት አይሰማኝም ። እወድ
ሀለሁ ። ጠረንህ ጠረኔ ሆኗል ። ሰውነቴ ሰውነትህ ። ከሚወዱት
ሰው ጋር ፤ ከሚግባቡት ሰው ጋር አንዲት ደቂቃም ብትሆን
ማሳለፉ ዓቤት ደስ ሲል! ያለ ፍቅር አንድጣራ ስር አብሮ መኖር
ኮ ቁም ነገር የለውም ። ግን አንተም ብትቆይ ያው የቱሪስት
ጠባይ ሳታሳየኝ አትቀርም ነበር ። ይህን ከማየቴ በፊት መሞቴ
ደስ ይለኛል ። እንዴት አዝን ነበር? አባቴ ይሙት ።

«የሚያሳዝነው የሚወዱትን ፤ ሲፈልጉት የኖሩትን ሰው
አግኝቶ ማጣት ነው ። አጣሁህ ። ምነው ባላወቅሁህ? ለደስታ
ነው የተፈጠርኩት ብዬ አስብ ነበር ። ግን አይደለም ። ለመከራ
የተፈጠርኩ መሆኔ ገብቶኛል ፤ ዕድሜ ላንቴ ። አንተ ከእጮኛህ
ጋር ተደሰት ። መጥታልህ የለም? እንኳን ደስ ያለህ ። እስቲ
ባባትህ ንገረኝ ፤ እንደኔ ትሆንልሀለች? እንደኔ ትወድሀለች?
ከኔ የበለጠ አንቴ ላይ ምን መብት አላት? የተለዋወጣችሁት
ቀለበት ነው ቁም ነገሩ? ባታውቀው ነው እንጂ እኔ ሕይወቴን
ልለውጥልህ ነው ። ደደብ ። አባቴ ይሙት ደደብ ነህ ። ግን

ለምንድነው? ምን ዓይነት ሴት ነኝ? እስቲ ንገረኝ? ግን ልትነግረኝ አትችልም ። ከእንግዲህ አታየኝም ፤ በሕይወት አታገኘኝም ።

«ጸግዬ ፣ ስለኔ ሁሉን ነገር አጫውቼሀለሁ ። ላንተ ግልጽ እንደሆንኩ ለማንም ሆኘ አላውቅም ። አንድ ነገር ብቻ አልነገርኩህም ። ለምን ሳልነግርህ እንደቀረሁ ምክንያቱ አይገባኝም ። ከዛሬ ነገ እነግረዋለሁ እያልኩ አስብ ነበር ። ሳልነግርህ የቀረሁት ምናልባት አጣዋለሁ በማለት ይሆናል ። አትፍረድብኝ ። የወደደ ሰው እውር ነው ። አሁን ልንገርህ ።

«ከኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይ ጋር ሰባት ዓመት አብረን ወጥተናል ። አከብረዋለሁ ፣ ያከብረኛል ። ደግ ነው ። የዋለልኝ ውለታ ብዙ ነው፣ግን ይሉኝታና አክብሮት ብቻቸውን ለፍቅር መሠረት ሊሆኑ አይችሉም ። የሚያስታውሰኝና የሚጠራኝ በፈለገኝ ጊዜ ብቻ ነበር ። ሌላ ጊዜ ትዝ የምለው አይመስለኝም ። በሕይወቱ ውስጥ አልነበርኩም ። እሱም በሕይወቴ ውስጥ አልነበረም ። እና አንተን መውደዴ ኃጢአት ይሆንብኛል? የፈለኩትን ለመውደድ መብት የለኝም ወይ? ከሰው የተፈጠርኩ አይደለሁም ወይ? የፈለኩትን ለመውደድ መብት አለኝ ። የሠራሁት ኃጢአት የለም ። ባል ወይም እጮኛ የለኝም ። ያልነገርኩህ ትቀናለህ ብዬ አይደለም ። ጦር ሜዳ ከሚዋጋ ሰው ወዳጅ ጋር እንዴት እወጣለሁ? የምትል ስለመሰለኝ ነው ። ስለወደድኩህ በዚህ ምክንያት ላጣህ አልፈለኩም ። ይህን እንዴት ለማወቅ ቻልሽ? ትለኝ ይሆናል ። ተስማኝ ። አብዛኛውን የሴት እውቀት የሚመነጨው ከስሜት ነው ። እውቀቷ ቀጥተኛ ነው ። አትፍረድብኝ እሺ? ደደብ ።

«እኔ ያለ ፍቅር የማውቀው ነገር የለኝም ። ወንዶችን ፍቅር ማስያዝ ደስ ይለኛል ። ወንዶችን ፍቅር ማስያዝ ቀላል ነው ። እንዴት መሰለህ? መጀመሪያ ሳገኘው ልክ ስፈልገው የኖርኩት ሰው አስመስዬ የልብ ልብ እሰጠዋለሁ ። ግልጽ እሆንለታለሁ ። ፍቅር አሳየዋለሁ፣ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለጥቂት ሣምንታት አልለየውም ። ሳላየው ውዬ አላድርም ። ሌላ ሴት እንዲያይ ወይም አሳብ እንዲኖረው ጊዜ አልሰጠውም።እንዲለምደኝ አደርገዋለሁ ፤ ደሙ ውስጥ እገባለሁ ። ወንድ ሞኝ ነው ፤ ውሻ ነው ። ቶሎ



ይለምዳል ። የለመደኝና ደሙ ውስጥ የገባሁ መሆኔን ካወቅሁ በኋላ ገሸሽ ሳደርገው እጀምራለሁ ፣ ዛሬ አይመቸኝም ፣ ነገም አይሆንልኝም ማለት እመጣለሁ ፣ ካመረረ እሔድለታለሁ ። ብሔድለትም የመንፈስ እረፍት አልሰጠውም ። በፊት የማውቃቸውን ወዳጆቼን ስም እየጠራሁና ዝናቸውንና ደግነታቸውን ፣ ኃይላቸውንና ወንድነታቸውን እያነሳሁ አስቀናዋለሁ ። ከእንግዲህ የፍቅርና የቅናት እሳት ተማረ ማለት ነው ። አንተንም እንዲህ ሳደርግህ ጀምሬ ነበር ። ግን አሳዘንከኝ ። ለምን እንደሆነ እንጃ ልጫወትብህ አልቻልኩም ። አታላይ ስላልሆንክ ላታልልህ አልፈለኩም ። የልማድና የቅናት እሳት በሚማርበት ጊዜ ልዩ ልዩ ወዳጆች የተለያየ ርምጃ ይወስዳሉ ። አንዳንድ ወንዶች እልክ ይገቡና ጢት ማታ ዱላ ይጀምራሉ ። የባሰባቸውም ይገድላሉ ። ሚስቴን ፈትቼ ካላገባሁሽ ሞቼ እገኛለሁ የሚሉም ይገኛሉ ። ታውረዋል በቃ ። በሆዴ እስቃለሁ ። ጅልነታቸው ያስቀኛል ። እታዘባቸዋለሁ ፣ እንቃቸዋለሁ ። እስቲ ባባትህ እየው ፣ ስንት ዘመን ትዳር ይዞ የኖረ ፣ ልጆች ያለው ሰው ፣ ድንገት እዚህ ለሥራ መጥቶ አገባሻለሁ ፣ ጠብቂኝ ፣ አትለይኝ ሲልህ ምን ትለዋለህ? ውሸቱን ነው ፣ የሚፈልገው የለመደውን ሰውነቴን ብቻ ነው ። እስካለ ድረስ ሌላ ወንድ እንዲነካበት ስለማይፈልግ ብቻ ነው ፣ ቅናት ስለሚያሳርረው ብቻ ነው ። አባቴ ይሙት ፣ ወንዶች ስትባሉ በመሠረቱ ከአውሬ አትሻሉም ። ሴቶችን ውሻ ትላላችሁ እንጂ ከወንዶች የባሰ ውሻ የለም ።

«ሌሎች ወንዶች ደግሞ ቅናት ይዟቸው እልክ ሲገቡ ያለ የሌለ ገንዘባቸውን በላዬ ላይ ማፍሰስ ይጀምራሉ ። ጢት ማታ ፣ ዘወትር ግብዣውና ስጦታው ይጎርፋል ። በቀን እስከ መቶ ብር መመንዘር ይመጣል ። ከየት ነው ይህን ሁሉ ገንዘብ የሚያመጡት? እዚህ አገር የሚመጡት አብዛኛዎቹ ወንዶች ግፋ ቢል ደመወዛቸው ከስምንት መቶ እና ወይም ከሺህ ብር አይበልጥም ። በዚያ ላይ ሚስት ፣ ልጆች አሏቸው ። አንድም ፣ ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን እያስራቡና እያስጠሙ ፣ ቤታቸውን እያራቆቱና ልጆቻቸውን ካሳማማ እያስቀሩ መሆን አለበት ። እየተበደሩና እየተለቀቱ መሆን አለበት።ይህ አልበቃ ሲል ምን ይኮናል? ጉቦ መብላት ፣ ማጭበርበርና በሥልጣን ተጠቅሞ መበዝበዝ ይመጣል ። እንዲህ ዓይነት ወንዶች በመሠረቱ ያልሆኑትን ሆነው መታየት የሚፈልጉ ጉረኞች ናቸው ። በየምሽቱ መቶ ብር በመ

ምዘዝ ፥ ውስኪ እንደ ውሀ በመጠጣትና በመጋበዝ ፡ ስጦታ
በማዥጎድጎድ የሴትን ልብ ለመማረክ የሚጥሩ ርካሾች ስለሆኑ
በሆዴ እስቅባቸዋለሁ ፣ በልቤ እንቃቸዋለሁ ። ግን እንዲህ
ዓይነቱ ወንዶች ይሻሉኛል ። ከተደሰትኩ ምን ቸገረኝ? የምፈ
ልገውም ይህንኑ ነው ። አሁን ባባትህ ስታስበው እንዲህ የማጌ
ጠውና የምሽቀረቀረው በማገኛት ደመወዜ መሰለህ? የማገኛት
ደመወዝ ለሽቶም አትበቃኝም ።

«እኔ የምጠላው የሚደባደቡትን ወንዶች ነው ። አንዳንድ
ወንዶች ከአህያ ፍቅር ሌላ አያውቁም ። ፍቅር በግድ ይሆናል?
አይሆንም ። ሴት ደብድበህና አድምተህ ፣ ደም አስተፍተህ በግድ
ብትተኛት ኃጢአትም ወንጀልም ነው ፣ ሴትን ልጅ ያለውዴታዋ
በግድ ፣ በጉልበት መድፈርና ጧት ማታ «ዶሮ ጠባቂ አድርጌ
ባላስቀርሽ እኔ ወንድ አይደለሁም» እያሉ ማስፈራራት በርግጥ
ወንጀል ነው ። ይህን ስለምፈራ ነው ባለሥልጣኖችን የምመር
ጠው ። አንድ ሰው ባለሥልጣን ከሆነ ክብሩን ስለሚጠብቅ ከነ
ውር ሥራ ይቆጠባል ። አይደባደብም ፡ ሌሊት ስክሮ መጥቶ
ቤት ሰብሮ ልግባ አይልም ፣ ወይም በየመንገዱ በመኪና እያሳደደ
ነይ ውረጂ በማለት አምባጓሮ አይፈጥርም የሚል ግምት ነበረኝ ።
አሁን አሳቤን ለውጫለሁ ። አንድ ባለሥልጣን ነው አሳቤን ያስ
ለወጠኝ ። በጠፋሁበት ቁጥር ቤቴ ቀርቶ ቢሮዬ ድረስ እየመጣ
ከሥራ ጓደኞቼና ከአለቃዬ ፊት ደም ያስተፋኝ ነበር ። ምን
ይደረጋል? ባለሥልጣን ስለሆነ የሚናገረውና የሚደፍረው የለም፣
ሁሉም ወገኑ ነው ። ከባለጊዜ ጋር ማን ተጋፍቶ ይችላል? ቤት
እየመጣ እናት አባቴና ወንድሞቼ ፊት ይደበድበኝ ነበር ። ወን
ወንድሞቼ እሳት የላሱ ጎረምሶች ቢሆኑም ምንም ሊያደርጉት
አይችሉም ነበር ። ቢናገሩትና ቢደበድቡት ምናልባት ጸረ
አብዮትና ጸረ አንድነት ናቸው ተብለው ስምበል ይገባሉ ። ይህን
ውርደት ማየት ጠልተው በመጨረሻ አንዱ አበደ ፣ ሌላው
አዲስ አበባ ሔዶ የት እንዳለ አይታወቅም ፣ ቤታችን ላይ የደረሰ
ርግማን ሆኘ ቀረሁ ። ነው ደግሞም ። በገዛ ራሴ ያመጣሁባቸው
ውርደት ነው ። ሲያዝኑብኝ ይኖራሉ ።

«እኔ መውጣት የምወደው ሚስት ካላቸው ወንዶች ጋር ነው
ብዬህ ነበር ። ታስታውሳለህ? ከሴትም ጋር እልክ መግባት ደስ
ይለኛል ። ግን ዋናው ምክንያት ሚስት ያለው ወንድ ጧት ማታ



አያስቸግረኝም ፣ እንደ ልቤ ለመሆን እችላለሁ በማለት ነበር ።
አሁን ሚስት ያላቸውንም ወንዶች መሸሽ ጀምሬአለሁ ። አንዳ
ንዶቹ ከወንደላጤዎች ይበልጥ ያስቸግራሉ ፣ ይሉኝታ አያው
ቁም ። ከሚስቶቻቸው ጋር በተጣሉ ቁጥር መጥተው ያስቸግራሉ ።
በር ይደበድባሉ ። በሰከሩ ቁጥር አያስቀምጡም ፣ አያስተኙም ፣
ሰው ምን ይለኛል አይሉም ። መጥኔ ለሚስቶቻቸው! ይህን
እያየሁ እንዴት ባል ላገባ እችላለሁ? እንዴት ልወሰን እችላለሁ?

«ከአዲስ አበባ የመጣ አንድ አባወራ ያደረገኝን ልንገርህ ።
ግን ለምንድነው የምናዘዝልህ? እዚህ አገር የተመደበ ባለሥል
ጣን ነው ። ስሙ ምንም አያደርግልህም ። አዲስ አበባ ቆንጆ
ሚስትና አበባ የመሰሉ ልጆች አሉት ። ባለሥልጣንም ባለ
ትዳርም ስለሆነ አያስቸግረኝም ብዬ እንደልማዴ አጠመድኩት ።
ሊለቀኝ መሰለህ! ኩርፊያው ፣ ዱላው ፣ ጭቅጭቁ አላስቆም አላስ
ቀምጥ አለኝ ። መግቢያ መውጫ አሳጣኝ ። የተፈጠርኩበትን
ቀን አስረገመኝ ። እንዴት ልገላገለው ብዬ ሳስበው ስጨነቅ
አንድ ሌላ ባለሥልጣን አጋጠመኝ ። እብድ ነው ። ጨርሶ
የለየለት እብድ ነው ። ይኸኛውም የባሰ መዥገር ሆነብኝ ።
ምሳና ራቴ ጥፊ ሆነ ። ከመጥበሻ ወደ እሳት እንዲሉ ፣ ከበፊተ
ኛው ሰውዬ ተገላገልኩ ስል የባሰ አጋጠመኝ ። ነፍስና ሥጋዬ
ተሰበሰበ ። ሰበሰበኝ ፣ አቃጠለኝ ፣ መኝታው እሳት ሆነብኝ ።
ስለዚህ ሰውዬ ኋላ አጫውትሀለሁ ። ግን አሁን ልነግርህ የም
ፈልገው ሌላ ነገር ነው ።

«ይህ ሁሉ ችግር የሚደርስብኝ ለምን መሰለህ? ግፍ ውያለሁ ።
አንድ ሰውዬ ነበር ። ቤቱ ሲወስደኝ ልጃገረድ ነኝ ብዬ አለቀስ
ኩበት ። ውሸቴን ነበር ። ለምን እንዲህ እንዳልኩት አላውቅም ።
በውሸቴ ጸናሁ ። አመነኝ ። ሁለት ዓመት ሙሉ አብረን ወጣን ፣
ያበላኛል ፣ ያጠጣኛል ፣ ያስጌጠኛል ፣ ያንሸራሽረኛል ። አንድ
ቀን እንዳጋጣሚ በኮምቢሽታቶ በእግሩ ሲዘዋወር ካንድ ፎቶ
ቤት በሼሎ የተነሳሁትን የሠርጌን ፎቶግራፍ አየ ። ይገርምሃል
ምንም አላለኝም ። በራሱ ሞኝነት ሲስቅ ቆየና «ምናለ በይኝ ፣
የዋልሽብኝ ግፍ ደም ሲያስለቅስሽ ይኖራል» ብሎኝ ሔደ ።
እውነትም ደም ሳለቅስ እኖራለሁ ። ወንዶች ላይ የምዘረጋው
ወጥመድ እኔን መልሶ ያጠምደኛል ፣ ያሰቃየኛል ። ግን ለምንድነ
ነው እንዲህ የምሆነው? ምን ዓይነት ሴት ነኝ?

«ግን አባቴ ይሙት ፤ ለምንድነው ክብራቸውን የሚጠብቁ ፤ ያልሆኑትን ሆነው ሙታየት የማይፈልጉ ፤ ሲወዷቸው የሚወዱ ፤ ሲጠሏቸው የሚተው ፤ በየመጠጥ ቤቱ የማይዞሩ ፤ ሥራቸውን አክብረው የሚያስከብሩ ፤ ትግሬ ሲባል ሁሉም ወንበዴ ነው ብለው የማያምኑ ፤ በአነጋገራቸውና በተግባራቸው እንደ ምሳሌነት የሚታዩ ፤ አጉል ኩራት ፤ ትዕቢትና ጉራ የማያጠቃቸው ፤ አስተዋይና ትሁት የሆኑ ምርጥ ፤ ምርጥ ሰዎች እዚህ የማይመደቡት? ጥሩ ነበር አባቴ ይሙት ። እኔ የፖለቲካ ሥራ ነው የምለው ይህን ነው ። ፍትወት ፤ ፍቅረንዋይ ፤ ጉራ ፤ አጉል ትዕቢትና የሥልጣን ጉጉት የሚያጠቃቸውን ሰዎች ሥልጣን ላይ ማስቀመጥ ፖለቲካ ያበላሻል ። ቀይ ኮከብ ዘመቻ ነገሩን ቢያስብበት ጥሩ ይመስለኛል ። እኔ ፖለቲካ አላውቅም ። ማወቅም አልፈልግም፤ እኔ የማውቀው ፍቅር ብቻ ነው ። ቢሆንም የፖለቲካ ሥራ በመሠረቱ አመራር ላይ ያሉ ሰዎች ያላቸው ጥንካሬና በሕዝብ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነትና እምነት ይመስለኛል ። አንዳንዶቹ ደግሞ ከጸሐይ በታች ያለውን ነገር ሁሉ ቃል ይገባሉ ። ሥራ አስገባሻለሁ ፤ ደመወዝ አስጨምርልሻለሁ ፤ ውጭ አገር እልክሻለሁ ፤ የታሰረውን ወንድምሽን ወይም ዘመድሽን አስፈታልሻለሁ ወዘተ... የማይገቡት ቃል የለም ። አንዳንዶቹ ያደርጉታል ። ይህ ምን ፍትሕ ይባላል አባቴ ይሙት ። ደህና ባለሥልጣን የያዘች ሴት የፈለገችውን ስታደርግ ሌሎቹ ምን ያድርጉ? ምን ይበሉ? ምን ይሥሩ?

«ምርጥ ምርጥ ሰዎች ሥልጣን ላይ እንዲቀመጡ ቢደረግ የአሥመራ ሴቶችም ያርፉ ነበር አባቴ ይሙት ። ፍትሕም ይገኝ ነበር ። አሁን የአሥመራ ሴቶች ከኔ ጀምሮ ፤ የመሐል አገር ወንዶች ለሴት ሟች ስለሆኑ በቀላሉ ይሞኛሉ ፤ ይታለላሉ ፤ ይራገፋሉ ፤ በቀላሉ ለሴት ተገዢ ይሆናሉ የሚል እምነት አለን ። ደግሞም እውነት ነው ። ከመሐል አገር የሚመጡት ወንዶች ልክ እንደ ጣልያን ናቸው ። ሴቶችን ማክበርና መንከባከብ ይወዳሉ ። ያሏቸውን ያደርጋሉ ። ጉራ አላቸው ። የትግሬ ወንድ ረግጦ ነው ሴቶችን የሚገዛው ። ለሴት ደንታ የለውም ፤ ክብር አይሰጣትም ። ከፈለገ ሚስቱን አስቀምጦ ሌላ ያገባል ። እና በዚህ እምነት የተነሳ የመሐል አገር ወንዶችን ሆን ብለው አሳደው የሚይዙ ፤ የሚቀበሉና የሚሸኙ ልዩ ሴቶች አሥመራ ውስጥ ተፈጥረዋል ። በጣም ብልጦች ናቸው ። ዓላማቸው አማርሶ ቶሎ ዞር ማለት ነው ። አንዳንድ መጥፎ መኸገር ካላጋጠ



ሟቸው በስተቀር ለምን? ከመሐል አገር የመጣው ወንድ ባለትዳር መሆኑንና ለትዳርና ለነገር የማያፈልጋቸው መሆኑን ያውቃሉ ። ገንዘብ እንዳለው ያውቃሉ ፤ አብዛኛዎቹ ፍትወተ ሥጋ የሚያጠቃቸው መሆናቸውንም ያውቃሉ ። ወንዱ ሊጠቀምባቸው ይፈልጋል ፤ እነሱም ይጠቀሙበታል ። ይረባረቡበታል ። የምትግጠውና የምታራግፈው የሚያወጣት ቤት ብቻ አይደለችም ። ጓደኞቿንም ጭምር ትጋብዛለች ። የመሐል አገር ሰው ጉረኛ ነውና ታከተኝ ፤ ደከመኝ አይልም ። ገንዘቡን ይከሰክሳል ፤ ማታ ማታ ሠርግና ምላሽ ይሆናል ። እንደ መዥገር ተጣብቀው በት ደሙን መጠው ሳይጨርሱ አይለቁትም ። ሂ.... ያሥመራ ሴቶ ሳጤዎች ደም ውስጥ ለመግባት ጊዜ አይፈጅባቸውም ። ከደባበሱትና የወደዱት መስለው ከታዩት የመሐል አገር ወንድ በሬ ነው ፤ ቶሎ ልቡ ይማረካል ። በመሐል አገር ወንዶች ጉዳይ ከኔ የበለጠች ኤክስፐርት በአሥመራ ከተማ አትገኝም ። ብዙ ተቀብያለሁ ፤ ብዙ ሸኝቻለሁ ። ብዙ ተምሬአለሁ ። ታሳታውስ እንደሆን እንደተዋወቅን ሰሞን እኔም ጓደኞቼን እየጠራሁ ላማርስህ ተነስቼ ነበር ። ግን አሳዘንከኝ ። አንተ እንደሌሎቹ ወንዶች የራስክን ጊዜያዊ ደስታ ብቻ የምትፈልግና የምትሞኝ ሰው አይደለህም ፤ ወይም አትመስለኝም ። የምታደርገው ነገር ሁሉ ከንጹህ ፍቅርና ከቀና አስተሳሰብ ስለሚመነጭ ነው መሰለኝ ፤ ፍቅርህንና ግብዣህን ፤ ስጦታህንና ደግነትህን ማራከስ ይከብዳል ። ሌሎች ወንዶች ግን በገንዘብ ወይም በማታለል ወይም በጉልበት ጊዜያዊ ስሜታቸውን ብቻ ለማርካት ስለሚፈልጉ ፤ ደማቸውን መምጠጥ ቀርቶ አጥንታቸውንም ቢግጡ አይቆጭም፤ አያሳዝንም ። ብዙዎቹ ከሚስቴ ጋር የምኖርም አይመስለኝም ሲሉ የከረሙ አዲስ አበባ በገቡ ማግስት መፈጠሬን ጭምር የረሱ ብዙ ወንዶች አውቃለሁ ። አብዛኛዎቻችሁ ርካሾች ናችሁ ። ግን እኔ እንደ አሥመራ ሴቶች ፍቅር ቶሎ አይዘኝም፤ አባቴ ይሙት ። የአሥመራ ሴቶች ይግረምህና ፍቅር ቶሎ ይገድላቸዋል ፤ ባንድ ጊዜ ሙትት ይላሉ ፤ ባንድ ጊዜ ነው ሙትት ፤ ፍርክርክ ፤ ብትንትን የሚሉት ። በተለይማ የሚያከብራቸውን ፤ የሚወዳቸውንና የሚንከባከባቸውን ወንድ ካገኙ በቃ ልባቸው እንደ ቅቤ ይቀልጣል ። የመሐል ሀገር ወንዶችን የሚወዱት ለምን መሰለህ? ፍቅር ያውቃሉ ፤ ሴቶች ያከብራሉ ስለሚሉ ነው ። ደብረ ዘይት ብትሄድ የአየር ኃይል የመኰንኖች ሚስቶች መሳ ለመሳ የአሥመራ ሴቶች ናቸው ። ከባሕር ኃይሎችም ጋር

በብዛት ተጋብተናል ። ከመሐል ሀገር የመጣው መለዮ ለባሽና
ሚሊሺያ ፣ አባት ጦሮችም ሳይቀሩ አንዳንድ እየያዙ በመመለስ
ላይ ናቸው ። ጥሩ ምልክት ነው አባቴ ይሙት ። ጥቂት ወንዶ
ቻችን እንገንጠል ቢሉም ፣ ሴቶቻችን አንድነትን እያጠበቁ
ናቸው ። የአንድነት መሠረቱ ፍቅር ነው ፣ አይመስልህም? እኔ
ግን የመሐል ሀገር ሰዎችን አልወድም ነበር ። ከቱሪስቶች ጋር
ፍቅር መውደቅ ምን ያደርጋል? ብዙዎቻችሁ ቱሪስቶች ናችሁ።
ጊዜው ሲደርስ ሻንጣችሁን እንጠልጥላችሁ ፈትለክ ከማለት
ሌላ ምን ታደርጋላችሁ? ስትሔዱ እንኳን ደህና ሁኑ አትሉም ።
አንተም ያው እንደሌሎቹ ቱሪስት ነህ ፣ አይደለህም? ቢሆንም
ካንተ ጋር ፍቅር ይዞኛል ። ለምንድነው ግን? ምን ዓይነት ሴት
ነኝ? እስቲ ንገረኝ ባባትህ? ይህን እዚህ ላይ ላቁምና ስለኔ ላጫ
ውትህ ።

«አታውቅም እንጂ በጣም ቀናተኛ ነኝ።አይገርምህም?ባንድ
በኩል ከአንድ ወንድ ጋር ብዙ ጊዜ መቆየት አልወድም ፣
በግድ ካልሆነ በቀር ። ይሁን እንጂ የማልወደው ወንድ ቢሆንም
ከሌላ ሴት ጋር ሲወጣ ካየሁ ደግሞ ቅናት ይይዘኛል ፣ እታመ
ማለሁ ፣ እስቃለሁ ፣ ልቤ የኃዘን ሙዚቃ ሲዘፍን ይውላል ፣
እንጀቴ ይቃጠላል ። ያንን ወንድ ካላገኘሁት ይለኛል ሆዴ ።
እና እሱን ማሳደድ እጀምራለሁ ። ካላገኘሁት አላርፍም ። በእው
ነት የሸርሙጣ ልብ ነው ያለኝ ። ግን ለምንድነው? እንዴት ልበ
ልህ ? ወንዶች እንደ ውሻ ሲናከሱብኝና ሲጣሉብኝ በቃ ደስ ይለ
ኛል ። እሷን ወደው ተጣሉባት ሲባል አቤት ደስታዬ! በወንዶች
መጫወት ደስታ ይሰጠኛል ። ለራሴ ጥቅምና ውስጣዊ ፍላጎት
ስል እጫወትባቸዋለሁ ። ግን እንዲህ ዓይነቱ ግንኙነት አንዳ
ንዴ በመጨረሻ ያሳዝነኛል ። ያስቃየኛል ። አንዳንድ ጊዜ
በውድም ሆነ በግድ ፍቅር ይይዘኛል ። ግን መወሰን አይሆን
ልኝም ። ሸርሙጣ ልብ እንዴት ሊወስን ይችላል ። ይግረምህና
የሚለማመጠኝን ወንድ ብዙውን ጊዜ አልወድም ። ኮስተር ሲል
ብኝ ይስበኛል ። አልፎ አልፎም ዱላ አልጠላም ። ኃይለኛ
ወንድ እወዳለሁ ። ብዙ ሴቶች ወንድ ይወዳሉ ። ምናልባት ተፈ
ጥሮአችንን ስለሚያካክስ ይሆናል ። አይገርምህም? ለኃጢአቴ
የምከፍለው ዋጋ ስለሆነ ነው መሰለኝ ።

«ምን ልነግርህ ፈልጌ ነበር? ረሳሁት ልጄ........ አዎን ፣
ወንዶች እንደውሻ ሲጣሉብኝ ደስ ይለኛል ብየሀለሁ ። እኔና



አንተ በፍቅር መተሳሰር የጀመርን ሰሞን ፣ ያ በገባሁበት እየገባ
ደብድቦና አሰቃይቶ ይወስደኝ የነበረው ሰውዬ እዚህ መጥቶ
ነበር ። ስሙን አልነግርህም ። የአሥመራ ሴቶች ወንድ ሁሉ የኔ
ነው ፣ ወይም ነበር ማለት ይወዳሉ ። ለማንኛውም ነገር ሰውዬው
እብድ ነው ። ከመምጣቱ በፊት ደወለልኝ ። እዚህም ከደረሰ
በኋላ ቢሮና ቤት እየደወለ ክዛቻ ጭምር ያስፈራራኝ ጀመር ።
አንተ ሰላለህ ከእሱ ጋር ፈጽሞ ለመውጣት አልፈለኩም ። ባንድ
ፊት ደግሞ እይው ፣ እይው የሚል በሽታ መጣብኝ ። እዚህ
መጥቶ እኔ እያለሁ እንዴት ከሌላ ሴት ጋር ይሄዳል? የሚል
ቁጭትና ቅናት አደረብኝ ። እሱ እዚህ መጥቶ ከሌላ ሴት ጋር
መሔዱ ውርደት መስሎ ታየኝ ። በአሥመራ ከተማ የኔንና
የሱን ታሪክ የማያውቅ መቸም የለም ። አንቀዠቀዠኝ ፣ ሆዴ
ተቃጠለ ። ቢቃ ላየው ፈለኩ ። አልገባህም እንጂ አንተን ይዤ
እሱን ፍለጋ ያልዞርኩበት ቦታ የለም ። ከተማው ውስጥ ያለውን
ቡና ቤት ሁሉ እየዞርክ ካላሰየኸኝ ብዬ ያስቸገርኩህ ምሽት
ትዝ ይልሃል ? ደደብ ፣ ግን አንተ አልገባህም ። ምንም አይገባ
ህም ። ደደብ የምልህ ለዚህ ነው ። ከዚያ በኋላ የሆነውን ነገር
አልነግርህም ። ብቻ ይቅር በለኝ ። ምን ላድርግ? ሸርሙጣ ልቤ
ነው እንዲህ የሚያደርገኝ ። አንተ ሰው ታምናለህ ። ቅናት አታ
ውቅም ። በእልክ አታምንም ። ማንኛውንም ነገር በውይይትና
በመግባባት ለመፍታት ከልብ ትጥራለህ ። መግባባት ከሌለ
ቆራጥ ርምጃ ለመውሰድ የምትችል ሰው ትመስለኛለህ ። በአጠ
ቃላይ ንጹህ ልብ ቀና ስሜትና አስተሳሰብ ያለህ ሠላማዊ ሰው
ነህ ። በጉልበቱ የሚመካ ኃይለኛ አይደለህም ። ግን ጉልበትና
ኃይል የሚበግርህ ፍጡር እንዳልሆንክ ደግሞ አውቃለሁ ። ፍር
ሀት የሚባል ነገር አታውቅም ። ምናልባት ደደብ ስለሆንክ
ይሆናል ፣ አላውቅም ። ግን የተለየ ኃይል አለህ ። ግን ለምንድነው
የወደድኩህ? ከሥልጣን ሥልጣን ፣ ከገንዘብ ገንዘብ የለህም ፣
መልክም ቢሆን ይህን ያህል አይደለህም።ያለህ ነገር ቢኖር ምላስ
ብቻ ነው ፣ ለዚያውም ቢሆን ቲሺ ላይ ካልሆነ ዝግ ነህ ። ጨዋታ
አታውቅም ። ድንግል ነህ ። ምናልባት ለዚህ ይሆናል የወደድ
ኩህ ። ከነክብርናዋ የተገኘች ልጃገረድ ትወደድ የለ? እንደሱ ነህ
አንተ ለኔ ። እንዲህ ባይሆንማ ኖሮ ይህን ጊዜ ሁለት ቀንድ አስ
በቅልህ ነበር አባቴ ይሙት ። ግን ምን ያደርጋል? አሁን ነገሩ
ሁሉ አልፎአል ።

«አሁን ይህ ሁሉ ምንም አይደለም ። ሌላም ያልነገርኩህ ነገር አለኝ ። እየተለወጥኩ መሔዴን አይተህ ምን ሆነሻል? እያልክ ብዙ ጊዜ ጠይቀኸኛል ። በጊዜው እንዳልነግርህ ለሕይወቴ ፈራሁ ። መወሰንም ተሳነኝ ። መወሰን አይሆንልኝም አባቴ ይሙት ። አሁን ግን ወስኛለሁ ። ለምን? ግን ምን ዓይነት ሴት ነኝ? አሁን ምክንያቱን ልንገርህ ።

«ከጥቂት ሳምንታት በፊት አንድ ሰው ቤቴ መጥቶ ከጸጋዬ ኃይለማርያም ወይም ካንቺ ሕይወት አንዱን ምረጭ አለኝ ። ምን እንዳደርግ ነው የምትፈልገው? አልኩት ። ሰውዬው የሚፈልገው ነገር ግልጽ ነበር ። አንተን ከተፈለገበት ቦታ በተወሰነ ሰዓት ይዤ እንድመጣ ነበር የፈለገው ። ቦታውንና ቀኑን ወደፊት እነግርሻለሁ ብሎኝ ሔደ ። ሰውዬው ማን እንደሆነና የት እንደሚሠራ ደርሼበታለሁ ። የሚሠራው አርሚ አቪዬሽን ነው ። ስሙ ሁቄጎይ ሲላ ይባላል ። እንዳልነግርህ ፈራሁ ። እንደሚገድሉኝ እርግጠኛ ነበርኩ ። ነፍሴ ከፉኛ መጨነቅ ጀመረች ። ካንተ ወይም ከራሴ አንዳችንን መምረጥ ነበረብኝ ። በተጠየቅሁት መሠረት አሳልፌ ከሰጠሁህ ምንም ችግር ሳይገጥመኝ ካርቱም እንደሚያደርሱኝና ከዚያም ወደፈለኩበት እንድሔድ እንደሚያደርጉልኝ ቃል ተገብቶልኛል ።

«እንዳጋጣሚ ሆኖ ጊዜውንና ቦታውን ሳይነግሩኝ አንተ ተነስተህ ወደ ጦር ግንባር ሔድክ ። ለጊዜው ከጭንቀትና ከመከራ ተገላገልኩ ። አንተ ከመመለስህ በፊት ተነስቼ ለመጥፋት ፈልጌ ነበር ። አልሆነልኝም ፤ መወሰን አልቻልም ። በሔድኩበት ቦታ ሁሉ እንደሚከተሉኝ ይሰማኛል ። የማላውቃቸው ሰዎች እንደጥላ ይከተሉኛል ። በየጊዜው ቤቴና ቢሮዬ እየደወሉ መኖር እለመኖሬን ያረጋግጣሉ ። ሠላም አይሰጡኝም ። እንቅልፍ ካጣሁ ቆይቻለሁ ።

«እና በመጨረሻ እጮኛህ መምጣቷን ሰማሁ ። መምጣቷን የነገረኝና ወስዶ እሷን ያሳየኝ አንድ የማላውቀው ሰው ነው ። አንድ ወቅት ላይ ለኔ ካልሆነ ለማን አባቱ ይሆናል? ከሕይወቴ የሚበልጥብኝ ምን ነገር አለ? አሳልፌ ሰጥቼው ለምን አልኖርም? ከሚል አሳብ ላይ ደረስኩ ። በዚሁ አሳብ ጸንቼ ሳለሁ ዛሬ አንድ ሰው ደውሎ መምጣትህን ነገረኝ ። ታስታውስ እንደሆነ ከአምስት



ደቂቃ በኋላ እደውልልሀለሁ ብዬህ ነበር ። በዚያ ጊዜ ውስጥ የተሰጠኝን ስልክ ቁጥር ተጠቅሜ ደወልኩ ። አንድ ሰዓት ላይ ወደ አይሮፕላን ማረፊያ እንዳመጣህ ታዘዝኩ ። የማደርገው ነገር ጠፋኝ ። መቁረጥ አቃተኝ ። አንድ የማላውቀው ሰው እንግዳ መስሎ መጥቶ ቢሮዬ ቁጭ አለ ። ምን እንደማደርግ ለመከታተል የመጣ ሰው መሆኑ ገባኝ ። እና የመሥሪያ ቤቱን ሥራ የምሠራ አስመስዬ ይህን ደብዳቤ ከመጻፍ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም ። ይህንኑ ደብዳቤ ስጽፍ ነው የዋልኩት ። ከልብ የሚጽፉት ነገር አያስቸግርም አባቴ ይሙት ። ደብዳቤውን እንዴት እንዳወጣሁት ይገርምሀል ። የሚጠብቀኝ ሰውዬ እንዳያየኝ በምሳ ሣህኔ ውስጥ አድርጌ ነው ያወጣሁት ። ምን ያህል እንደምወድህ የገባኝ ዛሬ ነው ። እወድሀለሁ አባቴ ይሙት ። ደደብ ። ግን ምን ዓይነት ሴት ነኝ? አንድ ነገር በሕይወቴ ወስኜ አላውቅም ። እርሜን ዛሬ አንድ ነገር ብወስን ይኸውና ችግር ላይ ወደቅሁ ።

«ለምን ለፖሊስ አትነግሪም ነበር? ትለኝ ይሆናል ። እስቤው ነበር ። ግን እንዳልኩህ ሰው አጠገቤ ነበር ። ይህን ሳልነግርህ ብሞት አንተም አትተርፍም ። የነበረኝ አማራጭ ይህን ደብዳቤ ጽፌ በሰው መላክ ነበር ። ይህ ደብዳቤ ይደርስህል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ። ከዚህ በኋላ ምን ታደርጊያለሽ? ትለኝ ይሆናል ። በእውነት አላውቅም ። ተማቶብኛል ። ምንም እንደማልሆን ተስፋ አደርጋለሁ ። እንደገና እንገናኛለን? አይመስለኝም ። አገኝሁህ ፤ አጣሁህ ። ቻው እምበእር...... ጸጋዬ ።»

ወደ ኰሎኔል በትሩ ቢሮ ደወልኩ ።

ጸሐፊው ፤ «መጥተዋል ። ሳገናኝዎት ፈልጌ አጣሆዎት ። ቢሮም ቤትም አልነበሩም» አለኝ ።

«እሺ አሁን አገናኚኝ.....»
«ቤት ደርሼ እመለሳለሁ ብለው አሁን ወጡ ። እሳቸውም በጣም ነው የሚፈልጉዎት .........»
«እሺ የቤቱን ቁጥር ስጠኝ ።»
የቤቱን ስልክ ቁጥር ሰጠኝ ። ቤቱ ደወልኩ ። አሁን ወጡ ተባልኩ ።

ጊዜ አላጠፋሁም ። ተነስቼ ወደ ማይተማናይ እንደ እብድ በረርኩ ። አሳቤ ፣ ቶሎ ደርሼ በሕዝብ ደኅንነት ሰዎች ጥበቃ ሥር ለጊዜው እንድትቆይ ለማድረግ ነበር ። ማይተማናይ ተናው ጠቆየኝ ። የሠፈሩ ሕዝብ ይራወጣል ፣ ጩኸት በርክቷል ። እንዴ ትና የት እንዳቆምኩ አላውቅም ። ብቻ እንደሮጥኩ ሔጄ ፊያሜታ ቤት ጥልቅ አልኩ ። ግቢው በሚጮሁ ሰዎች ተሞልቷል ። አልጋዋ ላይ አጋድመዋታል ።

«ፊያሜታ! ፊያሜታ! ጸጋዬ ነኝ።ትሰሚኛለሽ? ፊያሜታ!» ቤቱ ላንዳፍታ ጸጥ አለ ።

«ደብዳቤው ደረሰህ?» አለች በተዳከመ ድምጽ ።
ልብሷ በደም ተበክሏል ።

«አዎን ፊያሜታ ። አይዞሽ ። አሁን ደህና ትሆኛለሽ.....»
«እሞታለሁ?»
«ኖኖ .......... ፊያሜታ አትሞችም..........»
«ግን ለምንድነው የምሞተው? ምን አጠፋሁ? እግዜር ለምንድነው የሚገድለኝ? ምን አደረኩት?»
«አይዞሽ ፣ ምንም አትሆኝም.....»
«ታስታውሰኛለህወይ?»
«እባክሽን ፊያሜታ ዝም በይ..........»
«አዎን ፣ አዎን ፊያሜታ..........»
«ሁልጊዜ?»

«ሁልጊዜ..... ኖኖ ፊያሜታ ። እባክሽን በርቺ.......... ማነው የሚያግዘኝ? ሰዎች ለምን ዝም ትላላችሁ? ወደ ሆስፒታል እን ውሰዳት እንጂ..........»
«የሰጠሁህን መረጃ ቶሎ ተጠቀምበት ። ሰዎቹ አደገኞች ናቸው.....»
«እሺ..........»
«እኔም የቀይ ኮከብ ዘመቻ አባል ነኝ ፣ አይደለሁም? ፍቅር የቀይ ኮከብ ዘመቻ አካል አደረገኝ ። አንተ ደደብ..........»
«ፊያሜቴ! ፊያሜታ!»
ቆንጆ ፈገግታ ብቻ ከቆንጆ ፊቷ ላይ ቀርቶ ነበር ። ትንፏ ነበልባል ጠፋች ።





# ኦ ሮ ማ ይ

ደራሲው ነኝ እንደገና ። ጸጋዬ ኃይለማርያም ከእንግዲህ በራሱ ቃላትና ስሜት ታሪኩን ለመግለጽ አይችልም ። ከባድ ኃዘን በድን አድርጎታል ። ምንም ነገር አያይም ፣ አይሰማም ። ምንም ነገር አይሰማውም ። ኃዘኑ ከአቅሙ በላይ ሆኖበታል ። ደራሲ ኃዘን አይሰማውም? ስለሰው ልጅ ያዝናል ። የራሱ ኃዘን ግን የለውም።እግዜር ሰውን በራሱ አምሳል ፈጠረ ይባላል። ግን ስለሰው ልጅ ያዝናል ። አይገርምም? ይገርማል ። ደራሲም እንደዚሁ ነው ። ግን ስለእግዚርም ሆነ ስለደራሲ ማን ደንታ አለው? አሁን ስለእሱ ግድ የለም ። ወደ ጸጋዬ እንመለስ ።

ፊያሜታ ጠፍታለች ። ይህ ሕይወት ባንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያስኬድ መንገድ ነው ። ከእንግዲህ ተመልሳ አትመጣም ። ሕይወት እንቆቅልሽ ሆነበት — ለጸጋዬ ኃይለማርያም ። ለጥል የፈለጋት ሴት ሕይወቷን ለእሱ ብላ አሳልፋ ሰጠች ። የእሷ ሞት ለእሱ ሕይወት ሆኗል — የብድር ሕይወት ። ሞቷ ከልቡ ውስጥ የበጠሰው ነገር የመኖሩን ያህል የሰወጠውም ነገር ነበር ። አዲስ እምነት አግኝቷል ። በሰው ልጅ ላይ አዲስ እምነት እንዲ ኖረው አድርገዋለች ። ኰሎኔል በትሩ ቢሮ ደወለ ።

ወደ ኰሎኔል በትሩ ቢሮ ሔዶ ስለ ሥዕላይ ያገኘውን መረጃ ሰጠውና ፣ «በጊዜ ባገኝህ ኖሮ ይህ ሁሉ አይደርስም ነበር» በማለት እድሉን አማረረ ።

ኰሎኔል በትሩ መልስ እስኪሰጠው ድረስ አልጠበቀውም ። በተጨማሪ «ስለ ፓራዲዞ ቡና ቤት ጠቃሚ የሆነ መረጃ ሰጥ ቼህ ነበር ። እስካሁን ርምጃ ያልተወሰደበት ምክንያት ምንድ ነው? በእናንተ ቸልተኛነት ምክንያት ነው የዚች ልጅ ሕይወት የጠፋው ። በእውነት አዝናለሁ» በማለት ጮኸበት ።

ኰሎኔል በትሩ ስለ ሥዕላይ ያገኘውን መረጃ ትኩር ብሎ ሲመረምር ከቆየ በኋላ ከወንበሩ ላይ ተነስቶ ቆመ ። ፊቱ ላይ የድል ስሜት ይነበብ ነበር — «ጓድ ጸጋዬ» አለ — «ቸል ያልን በት ጊዜ የለም ። ፓራዲዞን ሀያ አራት ሰዓት ሙሉ በዓይነ ቁራኛ ስንጠብቅ ነው የከረምነው ። ሰብሮ መግባት ቀላል ነገር ነው ። ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብን ። ያልሆነ ሥራ ሠርተን ሌሎቹ እንዲነቁ ምክንያት መሆን ትርፉ ድካም ነው ። የምንወስደው ርምጃ ካለ የእነሱን የስለላ ድርጅት የጀርባ አጥንት የሚሰብር መሆን አለበት ። ብዙ «ሴሎች» እንዳሏቸው ይገመታል ። ዋና ሴላቸውን ካልሰበርን ጥቃቅኖቹን መስበር ጥቅም የለውም ። አንዱ ሴል ስለሌላው አያውቅም ። ዋናውን ሴል ከሰበርን ግን ሌሎቹን መስበር ቀላል ነው ። እርግጠኞች መሆን ነበረብን ። አሁን እርግጠኛ የሆንኩ ይመስለኛል ። አሁን የሚያጠራጥር ነገር የለም ። ፓራዲዞ ። ሥዕላይ ። ዋናው የእሮማይ ሴል ።»

ፊቱ ላይ የሚታየው ፈገግታ ብሩህ እየሆነ ይሔድ ነበር ። ስልኩን አንስቶ ተኽላይን ጠራው ። ተኽላይ እንደልማዱ ሽክ ብሎአል ።

«ሰዎችህ ዝግጁ ናቸው?»
«ዝግጁ ነን ጓድ ኰሎኔል ። የምንሠራው ሥራ አለ?»
ተኽላይ ድርጊት የጠማው ይመስላል ።
«ስለፓራዲዞ ቡና ቤት አዲስ ወይም ተጨማሪ መረጃ አለህ?
«እስካሁን ምንም የለንም!»

«እሺ ። ቡና ቤቱ እንዲሰበር እፈልጋለሁ ። አሁን! እዚያ ውስጥ የሚሠሩትን ሰዎች አንዳቸውም እንዲያመልጡ አልፈልግም ። ግልጽ ነኝ ። እና ሥዕላይን ከነሕይወቱ ነው የምፈልገው ። ጊዜ የለንም!» አለው ።

ተኽላይ ፊት ላይ ይነበብ የነበረው ደስታ ልዩ ነበር ። ወጥቶ ሔደ ።

ከምሽቱ አራት ሰዓት ከአርባ ደቂቃ ሲሆን የፓራዲዞ ቡና ቤት ባሬስታ ቡና ቤቱን ዘግቶ ሲወጣ ተያዘ ። ተኽላይ ዘድንግል ለሰውዬው ጊዜም ሆነ እድል አልሰጠውም ። ኩላሊቱን እንዴ



በመርገጥ እናገረው ። ሰውዬው ወደ ተከስተ ገብራይ መራው ። ተከስተ ዓለም ጤና ነው ብሎ ቤቱ ተኝቶ ነበር ። ተኽላይ ቤቱ ዘው ብሎ ገብቶ ከተኛበት ድንገት ያዘው ። ተከስተ ራቁቱን ነበር። እጆኖቹ መሐል በጉልበቱ መታው ። በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች እቁባይ ሲላ ከሁለት ሌሎች ሰዎች ጋር ቤቱ መጠጥ እየጠጣ ሲጫወት ተኽላይ ዘድንግልና ረዳቶቹ እንደመብረቅ ወረዱበት ። ሦስቱም ሰዎች ሰክረው ነበር ። ከእቁባይ ጋር የነበሩት ሁለት ሰዎች ያን ምሽት በመረዳዳት ፊያሜታ ጊላይን በሯ ላይ ጠብቀው በጥይት የመቷት ፣ አጥፍተው ለመጥፋት የተሰለፉ ቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ነበሩ ። ወዲያውኑ ለፈለፉ ።

ፊያሜታ ጊላይን ሲከታተሉ ነበር የዋሉት ። እንደነገረቻቸው ወደ ኒያላ በመሔድ ፈንታ ወደ ቤቷ በታክሲ ሔደች ። በመኪና ተከተሏት ። ቀድመው በሯ ላይ ጠበቋትና ከውጭ በር ላይ መንገድ ዘግተው ያዟት ።

«ምንድነው?» አለች ።
«እንደተነገረሽ ለምን አላደረግሽም?»
«አላደርግም ።»
«አንቺ የመንግሥት ሰላይ!»
«አይደለሁም.....»

በሁለት ጥይት ልቧ ላይ መተዋት ሮጡ ። ተኽላይ ራሱን ለመቆጣጠር አልቻለም ። ረዳቶቹ ባይዙት ኖሮ እዚያው ሊጨርሳቸው ፈልጎ ነበር ።

«ወዲበራኺ ተያዘ አይደለም?» አለ ዕቁባይ ደሙን ከፉ ላይ እየጠረገ ።
«ሥዕላይ ማለትህ ነው!? አለ ተኽላይ ።»
«ድሮውኑም እሱ ላይ እምነት አልነበረኝ! የውሻ ልጅ!» አለ ።

ተኽላይ ተነስቶ ወደ ቻው ሆቴል በረረ ። ሰዓት ቢያልፍም የሆቴሉ ቤቱ ባር ገና አልተዘጋም ። ሥዕላይ በራኺ ከቀይ ኮከብ ዘማቾች ጋር ተዝናንቶ እያወራ ቢራ ይጠጣ ነበር ። ተኽላይ መጥቶ እጎኑ በርጋታ ቁጭ ካለ በኋላ ቢራ አዘዘ ። ጠምቶታል ። ጉሮሮው ተቃጥሏል ።

ሥዕላይ «ዛሬ እደኑ እንዴት ነው?» ብሎ ተኽላይን በቀልድ ጠየቀው ።

«ዛሬ ሴቶች ሁሉ ባጊዜ ተኝተዋል ። እግዜር ይይላቸውና!» ብሎ መለሰለት ።

ተኽላይ ቀስ ብሎ ቢራውን ጨለጠና ፤ «ፈያሜታ ጊላይ የሆነችውን ሰምተሀል?» አለው ።

«ምን ሆነች?»

«የሆነችውን የምታውቅ መስሎኝ ነበር?»

«ምን ለማለት ፈልገህ ነው?»

«ሞታለች ። እና መሞቷን ታውቃለህ እይደለም? እንደሷ ያለች ቆንጆ ልጅ አሁን ጨካኖ ማን ይገድላል? ታውቀዋለህ ፤ እኔም እውቃለሁ ። ሁለታችንም እናውቀዋለን......»

«እንዴት እውቃለሁ?»

«አርማይ የማያውቀው ምን ነገር አለ?»

ሥዕላይ አልተደናገጠም ። ተኽላይን ላንዳፍታ እተኩሮ ተመለከተው ።' ዞር ፤ ዞር ብሎ ቡና ቤቱን በዓይኑ ቃኘ ። የሚያውቃቸው እንዳንድ የሕዝብ ደኅንነት ሰዎች ነበሩ ። ነገሩ ገባው ። እ'ሶን ወደ ኪሱ ሊከት ሲል ተኽላይ እንቆ ያዘው ። ሌሎች የሕዝብ ደኅንነት ሰዎችም ተረባረቡበት ። ሥዕላይ ኪስ ውስጥ ከሳይናይድ መርዝ ሌላ ምንም ነገር አልተገኘም ።

«ተከሰተን ያዛችሁት? እሱ መሆን አለበት ወደኔ የመራችሁ ።»

«እንሒድ?» አለው ተኽላይ ።

«ምን ምርጫ ይኖረኛል? ሳልቀድምህ ቀደምከኝ አይደለም?»

«ምን ይጠቅመኛል?» አለ ተኽላይ ጥርሱን ነክሶ ።

«እንዴት? ራስ፡ን እንኳን ደስ ያለህ ማለት አለብህ......»

«እዎ ፤ በእጄ ብገድልህ ኖሮ ራሴን አመሰግን ነበር ። ግን ምን ያደርጋል? እድለኛ አይደለሁም» አለው ።

«አሁን ጸጋዬ የት ነው?»

«ኃዘን ላይ ነው ። ምነው?»



«የሱ ጦስ ሳይሆን አይቀርም ለዚህ ያበቃን ። እና ደግሞ ያቺ ሽርሙጣ!»

ተኽላይ ዘድንግል እየተቆጨ ሥዕላይ በራኺን ይዞ ወጣ ። የታናሽ ወንድሙ ምስል እየመጣበት በለው ፤ በለው ይለው ነበር ። ግን ሥዕላይ እድል አልሰጠውም ። እንደ በግ እየተነዳ ሔደ ። በሚቀጥለው አንድ ሰዓት ውስጥ ፓራዲዞ ቡና ቤት ሥር የሚገኝ «ሴል» ተከፈተ።ኰሎኔል በትሩ ተሰማ ራሱ በቦታው ላይ ተገኝቶ ነበር ። እንቅልፉን ጠግቦ ገና የነቃ ወጣት መስሏል ። ጥርጣሬው ልክ ሆኖ በመገኘቱ በጣም ደስ ብሎታል ። በሌላ በኩል የጠላቶቹን ዝግጅትና ድርጅት በልቡ እያደነቀ ባንድ ፊት ደግሞ ይህ ሁሉ አፍንጫው ሥር ሲሠራ በመቆየቱ ውስጥ ውስጡን ይበሽቅ ነበር ።

በስለላና በግድያ ተግባር ላይ የተሰማሩ ፤ በቁጥር ከአምስት መቶ በላይ የሆኑ የሰዎች ስም ዝርዝርና እንዲሁም ለግድያ የሚፈለጉ የሲቪልና ወታደራዊ ባለሥልጣኖችና ኃላፊዎች ፤ የሕዝባውያን ድርጅቶች ተወካዮች ስም እንዳለ ተገኘ ። የአርማይን ተልእኮ በቅጥረኛነት የሚያስፈጽሙ ሰዎችም ስም ነበር ። ኰሎኔል በትሩ የሻለቃ ታደሰ ቆሪቾን ስም ሲያይ ራሱን ይዞ ቀረ ። ይህ የመጨረሻ እንዳልሆነ ያውቃል ። ሥራው ገና መጀመሩ ነበር ። ክትትሉ ወዴት እንደሚያመራው ላንዳፍታ አሳሰበው ። እስከምን ድረስ ወደ ላይ ይሔድ ይሆን? የት ይሆን ነገሩ የሚቆመው?» የሚሉ ጥያቄዎች አእምሮው ላይ ተመላለሱበት ።

የሥዕላይን ርጋታና ድፍረት በሆዱ እየደነቀ ፤ «ታዲያስ ሚስተር አርማይ?» አለው ።

«አለና......» የሚል ነበር መልሱ

«እንደምትተባበረን ተስፋ ላደርጋለሁ......»

«በምን?»

«ቢሮክራሲ ማነው?»

ሥዕላይ በራኺ መተባበር ነበፈበት ። ሞቱን ቢመርጥም የሚገድለው ሰው አልነበረም ። መሰቃየት ደግሞ አልፈለገም ። በጆብሐ እሥር ቤት ያየው መከራና ፍዳ ፀቅቶታል ። በሚቀጥ

ለው ሰዓት ውስጥ ከተከላይ ዘድንግል ጋር በልዩ አይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ እንዲበር ተደረገ ። በዚያኑ ወቅት ምናልባት ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ኢንተሌጀንስ አገልግሎት ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ፣ ሰዎችን በያሉበት አድኖ የመያዝ ሥራ ተጀምሮ ነበር ። ኰሎኔል በትሩ ምቹ ወንበሩ ላይ ወደኋላ ተለጥጠ ተቀመጠ ። ሲጠብቀው የነበረ ሽልማት ደረሰለት ። ግን፣ ክትትሉ ወዴት ያመራ ይሆን ? የሚለው ጥያቄ ከአእምሮው ላይ አልጠፋም ። ለጸጋዬ ኃይለማርያም የከፈለው ሦስት መቶ ብር በከንቱ አልነበረም ፣ የተፈለገውን ትርፍ አስገኝቷል ። ምስጋናውን ሁሉ ለራሱ አድርጎ ፈገግ አለ ። ንጋቱም ፈገግ ማለት ጀምሮአል ። ዓይኖቹን ሊከድን ሲል የስልክ ጥሪ መጣለት።

«ጸጋዬ ነኝ»
«እሺ ጸጋዬ ። የት ነህ?»
«ፈያሜታ ቤት ነኝ ። የምትረዳኝ ነገር አለኝ......»
«ደስ እያለኝ ። ምን ኖሮአል?»
«የሬሣ ሣጥን እፈልጋለሁ ።»

«ያውም በጣም ግሩም የሆነ ሣጥን ነው የምልክልህ ። ከዚህ የበለጠ ነገር በተገባት ነበር ። የጀግና ሰው ቀብር ። ጎዳዮ ቿም ተይዘዋል ። አይዞህ» አለው ።

ከጧቱ ሦስት ሰዓት ገደማ ግሩም የሆነ የሬሣ ሣጥንና አራት ትላልቅ ጉንጉን አበባዎች ተጭነው ከኃዘኑ ቤት ደረሱ ። ጸጋዬ ደረቱ ላይ የሰካውን ቀይ ኮከብ አውጥቶ ፈያሜታ ጊላይ ደረት ላይ አደረገላት ። በአገር ልብስ አሸብርቃ የመላክ ሞት ውብ ሙሽራ በመምሰል ጸጥ ብላ ተኝታለች ።

የፈያሜታ ጊላይ ቀብር ከቀትር በኋላ በአሥር ሰዓት ተፈጸመ ። ኰሎኔል በትሩ ፣ ሰለሞን በትረና ሌሎችም ከፍተኛ ሰዎች ቀብሩ ላይ ተገኝተው ነበር ።

«አይዞህ» አለው ሰለሞን ።
«ደስታና ሕይወት ገንዘቦቼ ነበሩ......»



«በ'ውነት መጽናናት አለብህ ። ሁላችንም በእሷ ሞት መጽናናት ይኖርብናል ። አንዱ ለሌላው ደስታና ሕይወት ራሱን አሳልፎ ሲሰጥ ማየት አያሳዝንም ፣ ያበረታታል እንጂ ። ለሌሎች ጥፋት ሳይሆን ለሌሎች ደስታና ሕይወት ብዙዎቻችን መስዋእት የምንሆንበት ቀን ሲመጣ ይታየኛል ። ጥሩ ምሳሌ ትታልን ነው የሔደችው ። ጥሩ አጀማመር ነው» አለው ።

ቀጥሎ ያነጋገረው ኰሎኔል በትሩ ነበር ።
«እንዲህ ዓይነቱ ነገር ሲደርስ ብርታት ይጠይቃል» አለው።
«ስለማጥኑ አመሰግናለሁ» አለ ጸጋዬ ።

«እንዳልኩት ሌላም ይገባት ነበር ። የእሷ ሞት ለብዙዎች ሕይወት ሆኗል ። ብዙ ነገር ከብዙ ጥፋት አድኗል ። ያንተንም ጥንቃቄ አደንቃለሁ......»

«ኦፕሬሽኑ እንዴት እየተካሔደ ነው? » ብሎ ጠየቀው ።

«በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው ። ያሥመራን ሴል ሰብረናል ። ያዲሳባ ሴላቸውንም ዛሬ ወይም ነገ እንሰብረዋለን ። ለጊዜው ቢሮክራሲ አምልጦናል ። ግን የጊዜ ጉዳይ ነው ። ድሬዳዋ መሆኑን ፍንጭ አግኝተናል ። የገባበት ገብተን እንይዘዋለን ። በሕዝባዊ አሠራር ላይ እምነት ማሳደር ይሽውልህ ጥሩ ነው — ይከፍላል» ብሎ ቀጠለና ፣ «ቀደም ብላ ብትነግረን ኖሮ ሕይወቷ አይጠፋም ነበር ። ያሳዝናል» አለው ።

«መወሰን አልቻለችም ። ድሮውንም ውሣኔ ማድረግ ያስቸግራታል ። ታመነታለች ። ምናልባት በሕይወቷ ያደረገችው ትልቅ ውሣኔ ቢኖር እኔን አሳልፋ ላለመስጠት ያደረገችው ውሣኔ ይሆናል ። እና ለሞቷ ምክንያት ሆነ» ብሎ ዝም አለ ።

ሰው ሁሉ ሔዷል። ትቢያ ። ዐፈር ። ጥርኝ ዐፈር-ሕይወት ። ጸጋዬ ኃይለማርያም ብቻውን ወደኋላ ቀረ ። የሚያደርገው ነገር አልነበረውም ። ግን ፈያሜታ ጊላይን እዚያ ብቻዋን ጥሎአት መሔድ አንጀቱ እምቢ አለው ።

ከላይ እስከ ታች ጥቁር በጥቁር የለበሰች አንድ ሴትም እን ዲሁ ወደኋላ ቀርታ ነበር ። እንዲያውም ከሴት ኀዘንተኞች ውስጥ ጥቁር በጥቁር የለበሰች እሷ ብቻ ነበረች ። የሐማሴን ሴቶች ለኀዘን ጥቁር የመልበስ ልማድ የላቸውም ።

ወደ ቀብር ሲሔዱ ነጭ በነጭ ለብሰው ነው ። ልቅሶ ቤት ሲደርሱ ያሸርጣሉ ፣ ወጣ እንዳሉ ሽርጡን ይፈታሉ ። ጌጣ ጌጥም አይቀራቸውም ። አጊጠው ሙታንን ይሸኛሉ ። ታዲያ ምን ይሁን? የሞተ ሞቷል ፣ የቀረው መኖር አለበት ። ሕይወት መቀጠል ይኖርባታል ። ሕይወት አጭር ናት ። ከሰው ረጅም ነገር ምንድነው? ምናልባት ጥላው ብቻ ነው ። ጺጋዬ ዞር ሲል አያት ። ሮማን ኀለተወርቅ ነበረች ። ወደ እሷ ሔደና ፣ «ማታ ብዙ ፈለኩሽ የት ጠፋሽ» አላት ።

ለጥያቄው መልስ ሳትሰጠው ፣ «እግዜር ያጥናህ» አለችው ። የሚለው ነገር አልነበረውም ። ዝም አለ ።

«ልብህ ወደ መቃብሯ አብሮአት ወርዶአል አይደለም?» አለች ። እንደገና ሊነዳት አልሞከረም ወይም አልፈለገም ። ታስታውሰኛለህ?...... አዎን በለኝ...... ሁልጊዜ?...... ምን ዓይነት ሴት ነኝ? እስቲ ባባትህ ንገረኝ...... ደደብ...... አባቴ ይሙት ደደብ ነህ...... የፈያሜታ ጊላይ ቃላት ትዝ አሉት ።

«ቀለበት መለዋወጥ ምንድነው? ባታውቀው ነው እንጂ እኔ ሕይወቴን ልለውጥልህ ነው...... ብላ በደብዳቤዋ ላይ ያሰፈ ረችው ቃል ባሳቡ ተነበበው ።

«ካልሽ ፣ አዎን» አላት ።
«እና ሁልጊዜ ስታስታውሳት ትኖራለህ አይደለም?»

«ሮሚ ፣ ሕይወቷን የሰጠችኝ ልጅ መሆኗን አትርሺ ። አዎን አስታውሳታለሁ ። አሳቤ ውስጥ ትኖራለች ። ሌላ ምን ላደርግላት እችላለሁ? አብሬአት ወደ መቃብር አልወርድ ነገር......»

«ግን ልብህ ወደ መቃብሯ ወርዷል ። ከመቃብር በታችና በላይ የሆነ ልብ ምን ያደርጋል!» ካለች በኋላ ፣ የቃል ኪዳናች



ውን ቀለበት ከጣቷ ላይ አውልቃ እግሩ ሥር ወረወረችለት ። ወርቅ ። ዐፈር ። ዐፈርና ወርቅ ። ሕይወት ።

«ፍርድሽ ይህ ነው?» አላት ።
«ይኸው ነው» ብላ ለጠቀችና ፣ «መጥፎ እድል እቴ!» አለች ።
«ምኑ?»

«የምወዳቸው ወንዶች ለምን እንደሚከዱኝ አላውቅም! እግኘቹ ማጣት ያርባ ቀን እድሌ ነው መሰለኝ ። ቻው» ብላው እቆመበት ጥላው ሔደች ።

ሮማን ከፊቱ ፣ የፈያሜታ ጊላይ መቃብር ከኋላው ፣ በመካ ከላቸው ቆሞ ቀረ ። በመጨረሻ ሰው ብቻውን ነው ፣ብቸኛ ነው ። ብቸኛነት ተሰማው ። ልቡ የኀዘን እንጉርጉሮ አንጎራ ጎረ ። ልቡ የኀዘን እንጉርጉሮ የማያንጎራጉር ሰው አለ ይሆን? ግን ልናዳምጠው አንፈልግም ። ለምን ? ደስተኞች መሆን እን ፈልጋለን ። ተስፋ ከመቁረጥ ተስፋ ማድረግ ይሻላልና ባናገኘ ውም ቅሉ ዘላለም እንሻዋለን ። ዘላለማዊ ተስፋ ፣ የኀዘንና የእንጉርጉሮ። ሰው ያለተስፋ ምንድነው? ተስፋ በልባችን ማሳደር አለብን ፣ ተስፋ በሌለበት ቦታም ቢሆን ።

እንባ እንባ ይለኛል
ይተናነቀኛል
ግን እንባ ከየት አባቱ!
ደርቋል ከረጢቱ
ሳቅ ሳቅም ይለኛል
ስቆ ላይስቅ ጥርሴ
ስቃ እያለቀሰች
መከረኛ ነፍሴ ።

ጀምበሯ ለመጥለቅ አቆልቁላለች ። አድማሱ ቀልቷል ። ቀለበቷን በማማው ረግጦ ለጋት ። እንደ እውነቱ ከሆነ ቀለበቷን አልነበረም በማማው ረግጦ የለጋው ፣ የገዛ ሕይወቱን ነበር እንጂ ። ቻው ፊያሜታ አለ በልቡ ። መቃብሯ ጸጥ ብሎአል ።

ከመቃብር ጸጥታ ባሻገር የናቅፋ ተኩስ ተሰማው ፣ የጀግኖችን ደምጩኸት  እየሰማ ልቡ ወደዚያ ሔደ ። ሁሉን ትወዳለህ ፣ በመጨረሻም ሁሉን ታጣለህ ። ሴ ላ ቪ ! አሮማይ ።



. . . . ባሬስታው ከፊት መታጠቢያው ግህን ሥር ያለውን የውሀ ቧንቧ መዘውር ሔዶ ጫን ሲለው . . . በኮንክሪት የተቀበረ መስሎ ይታይ የነበረው ትልቅ ባኞ ተነስቶ ቆመ ። ሥዕላይ ባኞው አርፎበት የነበረበትን ጉድጓድ ተመለከተ ። የኤሌክትሪክ ብርሃን ኩሬ ጉድጓዱን ሞልቶታል ። ወደ ውስጥ የሚወስዱ ከብረት የተሠሩ ደረጃዎች ይታያሉ ። ሥዕላይ ወደ ውስጥ ዘለቀ ። ባኞው ቦታው ተመለሰ . . .

. . . «የመረጃ ሥራ የመረጃ ሰዎች ብቻ የሥራ ክልል አይደለም፤ ባሁኑ ጊዜ ሕዝባዊ ባሕርይና መሠረት ሊኖረው ይገባል ። ሁሉም ለአብዮቱና ላገሩ አንድነት ሰላይ መሆን አለበት ። አብዮተኛ ነኝ ማለት አይበቃም . . . ጓድ ፣ መለኪያው ተግባር ነው» . . .

. . . ካሌብ ካዶሊስ የቀይ ባሕርን ሞገድ ሲገዛ ፣ ልብነ ድንግል በዱር ሲንከራተት ፣ ዮሐንስ መተማ ላይ አንገቱን ለሠይፍ ሲሰጥ ፣ አሉላ አባነጋ ፣ «ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ ተፈጥሮ በር ነው» እያለ ዶጋሊ ላይ ቆሞ በለው ሲል ፣ ቴዎድሮስ ፣ «የቱ ወንድ ክንዴን ይይዛል!» ብሎ መቅደላ ላይ የመጨረሻ ጥይቱን ሲጠጣ፤ ምኒልክና ጣይቱ አድዋ ላይ «ድሉ ያንተ ነው ያገሬ ጀግና!»ሲሉ . . .

. . .ሳመችኝ ። ትንፋሿ እንደ ዱር ጽጌረዳ ሁልጊዜ ደስ ይላል። እየተነጫነጨች የግዷን ተነሳች ። ለመልበስ ጊዜ አልፈጀባትም ። በቀላሉ የማጌጥና የመዋብ ችሎታ አላት ። ወይም የወጣትነት ዕድሜዋ ይሆናል የሚረዳት ። መኳኳል አታበዛም ። . . .

ከመጽሐፉ ውስጥ የተወሰዱ ።

ዋጋው ብር 10·